

**የጥገኝነት መብት ለማግኘት እና ከአገር**
**እንዳይባረሩ ለመከላከል እንዴት ማመልከት ይችላሉ**

**እንዲሁም/ወይም**

**በስምምነቱ አንቀጽ 3 መሰረት፡**
**የሥቃይ ቅጣትን በመቃወም አገርን ለቀው እንዳይወጡ ለመከላከል**

ማስጠንቀቂያ፥ ይህ አጭር መጽሐፍ፡ የኢሚግሬሽን ሕግ በተመለከተ አጠቃላይ መረጃ የያዘ ሲሆን፡ ስለ የእያንዳንዱ ግለሰብ ጉዳይ መግለጫ አይሰጥም። ብዙ ጊዜ የኢሚግሬሽን ሕግ ስለሚቀየር፡ በቅርቡ የወጣ መረጃ ለማግኘት፡ የኢሚግሬሽን ጠበቃ ወይም ሕጋዊ የሆነ ኤጀንሲ ማነጋገር ይኖርብዎታል። እንዲሁም ደግሞ፡ በኢሚግሬሽን አሰራር ሂደት ላይ ራስዎን ወክሎ መቅረብ ይችላሉ፤ ነገር ግን ከተቻለ ከጠበቃ ወይንም ሕጋዊ ከሆነ ኤጀንሲ እገዛ እንዲያገኙ መጠየቅ የተሻለ አማራጭ ነው።

ማስታወቂያ፥ ከመጋቢት 1፡ 2003 ዓ.ም እ.ኤ.አ ጀምሮ፡ የኢሚግሬሽን ኢና የዜግነት አገልግሎት (Immigration and Naturalization Service) (INS) የውስጥ ጉዳይ ሚኒስተር ክፍል (Department of Homeland Security) (DHS) አካል ሆነዋል። የኢሚግሬሽን ሕግ አፈጻጸም ስርዓት፡ የኢሚግሬሽን እስር ቤት እና አገርን እንዲለቁ የማድረግ ውሳኔዎች በሙሉ፡ በ**U.S. Immigration and Customs Enforcement (ICE)** ስር ይካሄዳል። **የዩኤስ የዜግነት እና የኢሚግሬሽን አገልግሎቶች (U.S. Citizenship and Immigration Services) (USCIS)**፡ ሌሎች የኢሚግሬሽን ጉዳዮችን፡ እንደ የዜግነት፣ የጥገኝነት፣ እና የስደተኛነት አገልግሎቶችን ያስተዳድራል።

## <u>አጠቃላይ መረጃ</u>

- ይህን አጭር ጽሑፍ የጻፈው ማን ነው? ለምንስ ተጻፈ?

ይህን አጭር ጽሑፍ ያዘጋጀው፡ ለትርፍ የማይሰራ እና፡ የሰዎችን ሰብአዊ መብት የሚደግፍ፡ የFlorence Immigrant and Refugee Rights Project ተብሎ የሚጠራ የሕግ ድርጅት ነው። ተሻሽሎ የተጻፈውን የዚህ አጭር ጽሑፍ ክፍል ለማዘጋጀት የተቻለው የገንዘብ ድጎማ ከFord Foundation ከሚባለው ድርጅት በመገኘቱ ነው።

ይህን አጭር ጽሁፍ፡ በDHS፡ ወይም በአሜሪካ መንግስት አልተዘጋጀም። ይህ አጭር ጽሑፍ፡ ለብዙ ዓመታት በኢሚግሬሽን እስር ቤት ያሉ ሰዎችን መበርዳት ያገኘው ልምድ መሰረት በማድረግ በFlorence Project የተዘጋጀ ነው። ነገር ግን የኢሚግሬሽን ሕግ ብዙ ጊዜ ግልጽ አደለም፤ ስለሆነም በሕጉ ላይ ያለን አስተያየት፡ DHS ካላቸው አስተያየት ጋር አንድ ላይሆን ይችላል። እዚህ ላይ የተሰጠውን መረጃ ትክክል መሆኑን እና ጠቃሚም እንደሚሆን እናምናለን። ነገር ግን ይህ አጭር ጽሑፍ በኢሚግሬሽን የታሰሩት ሰዎች እንዲያነቡት ተብሎ በእስር ቤቶቹ ያሉት ቤት መጻሕፍት ውስጥ ቢገኝም፡ DHS ወይም ደግሞ ሌላ የዩኤስ መንግስት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፡ ከይዞቱ ጋር ይስማማሉ ማለት አይደለም።

ይህ አጭር ጽሑፍ የተዘጋጀው ለሁለት ምክንያቶች ተብሎ ነው። አንደኛ፡ ጥገኝነት ለማግኘት እና/ወይም አገርን እንዳይለቁ ለመከላከል ብቁ መሆንዎን ለማየት እና፡ መልሶ ወደ አገርዎ እንዳይላኩ ለመከላከል እንዲችሉ ተብሎ ነው። ሁለተኛ ምክንያት ደግሞ፡ እርስዎን ወክሎ የሚቀርብ ጠበቃ ከሌልዎት፡ እንዴት ማመልከት እንዳለብዎት ለመርዳት ወይም፡ ጠበቃ ካልዎት ደግሞ ጠበቃዎን ለመርዳት ተብሎ ነው።

- ይህ አጭር ጽሑፍ ለማን ነው የተዘጋጀው?

ይህ አጭር ጽሑፍ የሚያገለግለው፡ በDHS ስር እስር ቤት ውስጥ ለሚገኙ እና አገር እንዲለቁ ጉዳያቸው በሂደት ላይ ያለው ግለሰቦች ነው። "አገርን ለቆ መውጣት" ማለት ድሮ "ማባረር" ተብሎ ይጠራ የነበረው ነው። <u>ይህ አጭር ጽሑፍ፡ ጉዳያቸው በማባረር አሰራር ሂደት ያለው ግለሰቦችን አያጠቃልልም።</u> ጉዳይዎ በኢሚግሬሽን አሰራር ሂደት የገባው ከሚያዝያ 1፡ 1997 በኃላ ከሆነ "በአገርን ለቆ መውጣት" ሂደት ይመደባል። የእርስዎ ጉዳይ የትኛው ሂደት እየተከተለ መሆኑን ለማወቅ፡ ከDHS የተላከልዎትን ዶኩመንት ማየት ይችላሉ፤ ምክንያቱም በዛ ላይ ምን ዓይነት ክስ እንደተከሰሱ (ወይም ደግሞ አሜሪካን ለቀው እንዲወጡ የተሰጡ ምክንያቶች) ማየት ይችላሉ።

- ዶኩመንቱ ላይ <u>"**በአካል እንዲቀርቡ ምልክታ**"</u> **(Form I-862)** የሚል ርእስ የተጻፈበት ከሆነ፡ ጉዳይዎ "**በአገር ለቆ መውጣት**" ሂደት ላይ ነው።
- ዶኩመንቱ ላይ <u>"**በፍርድ ቤት እንዲገኙ ትእዛዝ**"</u> **(Form I-221)** የሚል ርእስ የተጻፈበት ከሆነ፡ ጉዳይዎ "**በማባረር**" ሂደት ላይ ነው።
- ዶኩመንቱ እታች ላይ "Form I-110" እና "Form I-122" የሚል ቁጥር የተጻፈበት ከሆነ፡ ጉዳይዎ በእገዳ ሂደት ላይ ነው።

> ጉዳይዎ "በማባረር" ወይም "ከአገር በማውጣት" ሂደት ላይ ከሆነ፡ ይህ አጭርጽሑፍ እርስዎን አይመለከትም፤ ስለሆነም በተቻለ መጠን የሕግ አመካሪን ማነጋገር ይኖርብዎታል።

ይህ አጭር ጽሑፍ የተጻፈው፡ ጉዳያቸው አገርን ለቆ የመውጣት ሂደት ላይ ያለው ሰዎች የተዘጋጀ ነው። እነዚህ ሰዎች ጥገኝነት፣ በኢሚግሬሽን እና የዜግነት ሕግ (INA)፡ አንቀጽ 241(b)(3) መሰረት፡ አገርን ለቆ ከመውጣት ለመከላከል፣ ወይም ደግሞ በስምምነቱ አንቀጽ 3 መሰረት የስቃይ ቅጣትን የሚቃወም (CAT) ስምምነት መሰረት አሜሪካን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል ብቃት ያሳዩ ሰዎች ናቸው።

## <u>NACARA & HRIFA</u>

ስለ አገርን ለቆ መውጣት የመከላከል ዜዴዎች በተመለከተ በዝርዝር ከመወያየታችን በፊት፡ በ1997 መጨረሻ ላይ እና በ1998 ዓ.ም ሸንጎ ያጸደቃቸው ሁለት ሕጎች በተመለከተ ልናሳውቃችሁ እንወዳለን። እነዚህ ሁለት ሕጎች የሚከተሉት ናቸው፥ (1) የNicaraguan Adjustment እና Central American Relief Act of 1997፡ ብዙ ጊዜ "NACARA" ተብሎ የሚጠቀሰው እና (2) የHaitian Refugee Immigration Fairness Act of 1998፡ ብዙ ጊዜ "HRIFA" ተብሎ የሚጠቀሱት ናቸው።

- **ከጓቲማላ፣ ኢል ሳልቫዶር፣ በምስራቅ አውሮጳ የሚገኙ አንዳንድ አገሮች፣ ኒኳራጓ፣ ኩባ፣ ወይም ደግሞ ሄይቲ የመጡ ከሆነ፡ ከአሜሪካ አገር እንዳይባረሩ የመከላከል መንገድ ሊኖር ይችላል።**

በእነዚህ ሕጎች መሰረት፡ በNACARA እና HRIFA፡ አንዳንድ እላይ ከተጻፉት አገሮች የመጡ ሰዎች፡ በአሜሪካ አገር ሕጋዊ የሆነ ቋሚ የመኖርያ ፍቃድ ሊሰጣቸው ይችላል። ከየት አገር እንደመጡ መሰረት በማድረግ የሚያስፈልገው መመዘኛ ይለያያል። ስለዚህ ጉዳይ እርግጠኛ ካልሆኑ፡ የኢሚግሬሽን ዳኛ ወይም ደግሞ DHS በመጠየቅ፡ በNACARA እና HRIFA ሕግ መሰረት የአሜሪካ አገር የመኖርያ ፍቃድ ለማግኘት እንደሚችሉ እና እንደማይችሉ ለማወቅ ይችላሉ። እንደዚህ አይነት ፍቃድ የተሰጠውን ሰው ባለቤት ወይም ልጅ ከሆኑ፡ እርስዎም በአሜሪካ አገር የመቆየት መብት ሊኖርዎት ስለሚችል፡ ዳኛው ወይም DHS ያነጋግሩ።

- <u>**ስለ ጥገኝነት እና አገርን ለቆ ላለመውጣት ስለ መከላከል መረጃ በተመለከተ**</u>

ይህ አጭር ጽሑፍ ጥገኝነት እና አገርን ለቆ ላለመውጣት መከላከል ማለት ምን ማለት መሆኑን መግለጫ ይሰጣል፤ እንዲሁም ለጉዳይዎ እንዴት መዘጋጀት እንዳለብዎት መረጃ ይሰጣል።

• ጥገኝነት ምንድን ነው?

በዩናይትድ ስቴት ሕግ መሰረት፡ በአገራቸው ሊደርስባቸው ከሚችል መሰቃየት በመሸሽ የመጡ ሰዎች፡ በ INA አንቀጽ 208 መሰረት "ለጥገኝነት" ማመልከት ይችላሉ። **ጥገኝነት** በአሜሪካ አገር እንደ ስደተኛ የደህንነት ከለላ ይሰጣል። **መሰቃየት** ሲባል፡ በእርስዎ ወይም በቤተሰብዎ፣ ወይም ደግሞ እርስዎን በሚመስሉ ሰዎች ላይ ሊደርስ የሚችል ጉዳት ወይም ማስፈራራት ሊሆን ይችላል። እንዲሁም አንድ ግለሰብ በአገሩ መሰቃየት የደረሰበት ከሆነ፡ እና በ INA ሕግ አንቀጽ 101(a)(42) መሰረት የ "ስደተኛነት" መመዘኛዎች ያሟላ ከሆነ የጥገኝነት መብት ሊሰጠው ይችላል። የጥገኝነት መብት የሚሰጥዎት፤ እላይ ከተዘረዘሩት የመሰቃየት ምክንያቶች፡ በዘር፣ በሀይማኖት፣ በትውልድ፣ በፖለቲካ አስተያየት (ወይም ሌላ ሰው እንደዚህ የፖለቲካ አስተያየት ነው ያለዎት ብሎ ካሰበ) ወይም ደግሞ የአንድ ህብረተሰብ ብዱን አባል በመሆንዎ ብቻ የደረሰብዎት ከሆነ ነው።

የጥገኝነት ፈቃድ የተሰጥዎት ከሆነ፡ ህጋዊ በሆነ መንገድ በአሜሪካ አገር እንዲኖሩ እና የስራ መስራት ፍቃድም እንዲሰጥዎት ይደረጋል። ባለቤትዎ ወይም ሚስትዎ እና እንዲሁም ያላገቡ ዕድሜአቸው ከ21 ዓመት በታች የሆኑ በአሜሪካ አገር የሚኖሩ ልጆችዎ፡ ስማቸውን በጥገኝነት ማመልከቻዎ ላይ ያስገቡት ከሆነ፡ ሕጋዊ የሆነ የጥነኝነት ፍቃድ ሊሰጣቸው ይችላል። የሚኖሩት ከዩኤስ ውጭ ከሆነ፡ ደግሞ እርስዎ የጥገኝነት ፍቃድ ከተሰጡ በኃላ፡ ስለ እነርሱ ማመልከቻ ሊያስገቡ ይችላሉ። የጥገኝነት ፍቃድ ከተሰጥዎ በኃላ፡ ሕጋዊ ቋሚ የመኖርያ ፍቃድ እንዲሰጥዎ ማመልከት ይችላሉ፤ በመጨረሻም ቀስ ብለው የዜግነት መብት እንዲሰጥዎት ለማመልከት ይችላሉ።

• አገር ለቀው እንዳይወጡ መከላከል ማለት ምንድን ነው?

አገር ለቆ እንዳይወጡ መከላከል፡ የሚባለው በINA ሕግ አንቀጽ 241(b)(3)(A) እና (B) በተገለጸው መሰረት፡ አንዳንድ ሰዎች የጥገኝነት ፍቃድ ከማግኘት ይልቅ ይህን ዓይነት ሕጋዊ ከለላ ያገኛሉ። በኃላ በዝርዝር በሚገለጹ ምክንያቶች - ለምሳሌ፡ ወደ አሜሪካ ከገቡ ከአንድ ዓመት በላይ ከቆዩ በኃላ ልዩ የሆን ምክንያት ሳያቀርቡ ለጥገኝነት በማመልከታቸው፡ ወይም ደግሞ የወንጀል ተግባር ላይ በመገኘታቸው - አንዳንድ ሰዎች የጥገኝነት ፍቃድ ለማግኘት ብቁ አይሆኑም። እንዲሁም ደግሞ፡ አንዳንድ የወንጀል ስራዎች ወይም መጥፎ የሆኑ ድርጊቶች ለጥገኝነት ከማመልከት ባያግድዎትም፡ የኢሚግሬሽን ዳኛ የእርስዎ የጥገኝነት ጥያቄ ላይቀበለው ይችላል። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ፡ አገርን ለቀው እንዳይወጡ አንዱ መንገድ "መከላከል" ብቻ ሊሆን ይችላል።

ልክ እንደ የጥገኝነት ፍቃድ አገር ለቀው እንዳይወጡ መከላከል፡ ደግሞ ወደ አገርዎ መልሶ እንዳይላኩ የሚከላከል ሲሆን፤ በአሜሪካ አገር ሕጋዊ ሆነው ሊኖሩ እና ሊሰሩ ይችላሉ ማለት ነው። የጥገኝነት ፍቃድ ለማግኘት፡ እና ላለመልቀቀ ለመከላከል የሚያመልክቱበት መንገድ አንድ አይነት ስለሆነ አንድ አይነት የማመልከቻ ፎርም ነው የሚሞሉት። ነገር ግን፡ አስፈላጊ የሆነ ልዩነት አሉዋቸው። አንደኛ፥ አገር ለቀው እንዳይወጡ የመከላከል ፍቃድ ለማግኘት ከባድ ነው። ወደ አገርዎ ቢመለሱ፡ በዘር፣ በሀይማኖት፣ በትውልድ፣ በፖለቲካ አስተያየት (ወይም ሌላ ሰው እንደዚህ የፖለቲካ አስተያየት ነው ያለዎት ብሎ ካሰበ) ወይም ደግሞ የአንድ ህብረተሰብ ቡድን አባል በመሆንዎ ሊደርስብዎት የሚችለው ስቃይ እና ከዛም በላይ ምክንያት ማቅረብ መቻል አለብዎት። <u>ህይወትዎ ወይም ነጻነትዎ</u> በአደጋ ላይ እንደሚወድቅ ማሳየት አለብዎት፤ እንዲሁም ደግሞ ይህን ዓይነት አደጋ እንደሚደርስ ማሳየት አለብዎት (ሊደርስ ይችላል ማለት ብቻ በቂ አይደለም)። ሁለተኛ፥ ይህን ዓይነት ከለላ ከተፈቀደልዎት፡ አደጋ እንዳይደርስብዎት በማለት ወደ አገርዎ እንዲላኩ ለማድረግ አይቻልም ማለት ነው። ሌላ አገር እንዲቀበልዎት ፍቃደኛ ከሆነ፡ የተባበሩት የአሜሪካ መንግስታት ወደዛ አገር እንዲላኩ ሊያደርግ ይችላል። ሶስተኛ፥ አገርዎ ውስጥ ያለው ሁኔታ ከተቀየረ እና DHS ወደ አገርዎ ቢመለሱ አደጋ የለውም ብሎ ካመነ፡ DHS ሌላ ጉዳይ በመክፈት ዳኛው ወደ አገርዎ እንዲልክዎት ለማሳመን እንደገና ወደ የኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት ያመለክታል። በመጨረሻ፥ አገርን ለቀው እንዳይወጡ መከላከል ቋሚ የሆነ የመኖርያ ፍቃድ እንዲሰጡ አይፈቅድም፤ እንዲሁም ደግሞ የበተሰብዎ አባሎች እንዲያስመጡ አይፈቀድም፤ የዩኤስ ዜግነትም እንዲሰጥዎት አይፈቅድም።

• የሥቃይ ቅጣትን በመቃወም አገርን ለቀው እንዳይወጡ መከላከል ወይም ጉዳዩን ማዘገየት ምን ማለት ነው?

የሥቃይ ቅጣትን በመቃወም አገርን ለቀው እንዳይወጡ የመከላከል ስምምነት (Convention Against Torture) (CAT) አንዳንድ ሰዎች፡ ወደ ሌላ አገር ከተላኩ በዛ አገር መንግስት ወይም ህዝብ፤ ወይም ደግሞ በመንግስት ውስጥ የሚሰሩ

ሰዎች፡ ስቃይ ሊደርስባቸው እንደሚችል የሚያሳይ ማስረጃ ካቀረቡ የሚሰጣቸው ሕጋዊ የሆነ ከለላ ነው። "መሰቃየት" ሲባል ትርጉሙ በየስቃይ ቅጣት የመቃወም ስምምነት በአንቀጽ 1 እንዲሁም የፌደራል ስርዓቶች (Federal Regulations) (CFR) ኮድ 8 አንቀጽ 208.18(a) እና 1208.18(a) ተገልጸዋል። በCAT የተገለጸው መከላከል ልክ በINA ሕግ አንቀጽ 241(b)(3) የተጻፈው መከላከል አንድ ዓይነት ሲሆን፤ ይህን ዓይነት ከለላ ከተሰጥዎት፡ አደጋ የሚደርስብዎት ከሆነ ወደዛ አገር እንዲላኩ ለማድረግ አይቻልም ማለት ነው። ነገር ግን፡ የጥገኝነት ፍቃድ ለማግኘት ወይም ደግሞ በ INA ሕግ አንቀጽ 241(b)(3) እንደተገለጸው ማባረር ለመከላከል የሚገቡ ማመልከቻዎች ሳይሆን እንዳይደርስ የተፈራውን ስቃይ፡ የተለየ ምክንያት እንዲሆም አያስፈልግም። ሌላ አገር እንዲቀበልዎት ፍቃደኛ ከሆነ፡ የተባበሩት የአሜሪካ መንግስታት ወደዛ አገር እንዲላኩ ሊያደርግ  ይችላል። እንዲሁም ደግሞ በአገርዎ ውስጥ ያለው ሁኔታ ከተቀየረ እና DHS ወደ አገርዎ ቢመለሱ አደጋ የለም ብሎ ካመነ፡ DHS ሌላ ጉዳይ በመክፈት ዳኛው ወደ አገርዎ እንዲልክዎት ለማሳመን እንደገና ወደ የኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት ያመለክታል። በመጨረሻ፥ በCAT ሕግ መሰረት አገርን ለቀው እንዳይወጡ መከላከል ቋሚ የሆነ የመኖርያ ፍቃድ እንዲሰጡ አይፈቅድም፤ እንዲሁም ደግሞ የበተሰብዎ አባሎች እንዲያስመጡ አይቀድም፤ የዩኤስ ዜግነትም እንዲሰጥዎት አይፈቅድም።

የኢሚግሬሽን ዳኛ፡ ከአገር ከተባረሩ ስቃይ እንደሚደስብዎት ካመነ እና፡ ነገር ግን በአንዳንድ የወንጀል ስራ ወይም ሌላ የብቃት ማነስ ጉዳይ፡ በCAT ሕግ መሰረት የመከላከል ፍቃድ ሊሰጥዎ አይገባም ብሎ ካመነ፡ ዳኛው የማስወጣቱ ሂደት እንዲዘይ የማድረግ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል። መሰቃየትን የመቃወም ስምምነት መሰረት የማስወጣቱ ሂደት መዘግየት በ8 CFR ሕግ አንቀጽ 208.17(a) እና 1208.17(a) ተጽፎ ይገኛል። የማስወጣት ሂደት መዘግየት ውሳኔ፡ ማንኛውም ዓይነት የመኖርያ ፍቃድ እንዲያገኙ አያደርግም፤ እንዲሁም ደግሞ እስር ቤት ውስጥ እንዲቆዩ ሊያደርግ ይችላል። ጉዳይዎ እንደገና ከታየ እና ወደ ሌላ አገር ቢላኩ ስቃይ አይደርብዎትም ተብሎ ከተወሰነ ወይም ደግሞ፡ የመዘግየቱ ውሳኔ እንዲነሳልዎት ራስዎ ከጠየቁ፤ የማስወጣት ሂደት የመዘግየት ውሳኔ ሊሻር ይችላል።

በ CAT ሕግ መሰረት፡ አገርን ለቀው እንዳይወጡ ማመልከት ከፈለጉ፡ ልክ በ INA ህግ መሰረት፡ ለጥገኝነት ወይም እንደ አንቀጽ 241(b)(3) መሰረት፡ ለቀው እንዳወጡ ለመከላከል ለማመልከት አንድ ዓይነት ተመሳሳይ ፎርም ይሞላሉ።

አገርን ለቀው እንዳይወጡ መከላከል አስመልክቶ በ CAT መሰረት የተገለጸው ሕግ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፡ "የስቃይ ቅጣትን የሚቃወም ስምምነት (CAT) መሰረት ከለላ ለማግኘት ማን ማመልከት ይችላል" በሚለው ርእስ የተጻፈውን ይመልከቱ።

- ለጥገኝነት ወይም አገርን ለቆ እንዳይወጣ ለመከላከል እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

I-589 የሚለው ለጥገኝነት እና አገር ለቆ እንዳይወጡ መከላከል የማመልከቻ ፎርም መሙላት አለብዎት፤ በዚህ ፎርም ላይ፡ በትውልድ አገርዎ ምን ዓይነት ግፍ እንደደረሰብዎት እና አሁን ለመመለስ ለምን እንደሚፈሩ በዝርዝር ይጽፋሉ። በፍርድ ቤት ቀጠሮ ላይ፡ ዳኛው ጥያቄ በሚጠይቅዎት ጊዜ፡ ዝርዝር መግለጫ መስጠት መቻል አለብዎት። ዳኛው እውነት ተናገሩ ወይም አልተናገሩም ብሎ ውሳኔ ይሰጣል። እንዲሁም ዳኛው፡ በአገርዎ ግፍ እንደደረስዎ እና እንዳልደረስዎ እንዲሁም ወደ አገርዎ ቢመለሱ አደገኛ ነው ወይስ አይደለም ብሎ የራሱ ውሳኔ ይሰጣል። በ INA እና በ CAT የሕግ ስርዓት አንቀጽ 241(b)(3) መሰረት ከአገር እንዳይባረሩ ለከመላከል የሚያስፈልገው የማመልከቻ ፎርም ከዚህ ጋር አንድ አይነት ነው።

- **የጥገኝነት ፍቃድ እንዲሰጠኝ ወይም ደግሞ አገርን ለቅቄ ላለመውጣት፡ ከእስር ቤት ውጭ በመሆን፡ መከራከር እችላለሁኝ ወይ?**

ጉዳይዎ "አገርን ለቆ የመውጣት ሂደት" ላይ ካለ እና በDHS እስር ቤት ቁጥጥር ከሆኑ፡ የኢሚግሬሽን ዳኛ የገንዘብ ዋስትና በማስያዝ እንዲለቅዎት የመጠየቅ መብት አለዎት። ዋስትና ሲባል፡ ገንዘብ በመክፈል፡ ከእስር ቤት ይወጡ እና የፍርድ ቤት ወይም የቃለ መጠይቅ ቀጠሮ ካለዎት በዛ ይገኛሉ፡ ጉዳይዎ ካለቀ በኃላ ደግሞ መመለስ መቻል አለብዎት። እንዲሁም ደግሞ ዳኛው አገሩን ለቀው እንዲወጡ ትእዛዝ ካስተላለፈ፡ ለቀው መውጣይ ይኖርብዎታል። ጉዳይዎ በጣም ጥሩ በሆነ ማስረጃ የተመሰረተ ከሆነ እና እንዲሁም ደግሞ፡ በአሜሪካ አገር ጽኑ የሆነ የቤተሰብ ወይም የማህበረሰብ መተሳሰር ካልዎት፡ ዳኛው ምንም ሳይከፍሉ ከእስር ቤት እንዲወጡ ሊፈቅድልዎት ይችላል፤ ይህን የሚያደርገው ግን

በፍድ ቤት ቀጠሮ እንደሚገኙ ቃል ሲገቡ ብቻ ነው። ይህ "በታዋቂነትዎ" መሰረት ከእስር ቤት መልቀቅ ይባላል። ነገር ግን፡ ከአሁን በፊት ማንኛውም አይነት ወንጀል የፈጸሙ ከሆነ፡ የዋስትና መብት እንዲያገኙ ወይም ደግሞ ከእስር ቤት እንዲወጡ አይችሉም። የገንዘብ ዋስትና በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፡ በዚህ ጽሑፍ ላይ "የገንዘብ ዋስትና ማግኘት" በሚል ርእስ የተጻፈውን ክፍል ይመልከቱ።


በኤርፖርት ወይም በድንበር በኩል ወደ አሜሪካ አገር ሲገቡ፡ ድሮ በነበረው የINS ወይም የDHS የሕግ ስርዓት፡ ተይዘው ወደ እስር ቤት የገቡ ከሆነ፡ በሕጉ መሰረት የኢሚግሬሽ ዳኛው በዋስትና ወይም ደግሞ "በታዋቂነትዎ" መሰረት እንዲለቀቁ ሊፈቅድ አይችልም። ነገር ግን፡ እንደዚሁ ዓይነት ከእስር ቤት የመውጣት መብት DHS ሊሰጥዎት ይችላል።

ከእስር ቤት ከወጡ በኃላ ደግሞ፡ ወደ ፍርድ ቤት (ወይም በአቅራቢያ ወደሚገኘው የኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት) እየሄዱ ጉዳይዎን መከታተል ይኖርብዎታል። ከእስር ቤት ከወጡ በኃላ በሚፈለጉበት ጊዜ ወደ ፍርድ ቤት ካልሄዱ፡ ዳኛው አገርን እንዲለቁ ትእዛዝ ያስተላልፋል። ከእስር ቤት ከወጡ ደግሞ ምን ማድረግ እንዳለብዎት በኃላ እንገልጸልዎታለን።

- **ከእስር ቤት መውጣት ካልተፈቀደልኝ እና እስር ቤት ውስጥ መቆየቱ ከመረረኝ ምን ማድረግ እችላለሁኝ? አገሩን ለቅቄ እንድወጣ ወይም ደግሞ በፈቃደኝነት እንድመለስ መጠየቅ እችላለሁኝ ወይ? ከዛ በኃላስ ወደ አሜሪካ አገር የመመለስ እድል አለኝ ወይ?**

ለረጅም ጊዜ በእስር ቤት መቆየት በጣም ከባድ ስለሆነ፡ ሊፈሩ፣ ሊያዝኑ፣ እና ሊጨነቁ ይችላሉ። ብዙ ሰዎች የሚያዝኑት ሰርተው ቤተሰቦቻቸውን ልመርዳት ስለማይችሉ፤ ወይም ደግሞ፡ ጊዜያቸው በከንቱ እየባከነ እንዳለ ስለሚሰማቸው ነው። የገንዘብ ዋስትናው ለመክፈል ካልቻሉ፤ መብትዎን ሳይጠቀሙበት ተስፋ በመቁረጥ፡ እስር ቤት ውስጥ ብዙ ጊዜ እንዳያባክኑ በመፍራት፡ የአሜሪካ አገርን ለቆ የመውጣት ውሳኔ እንዲወሰን ይፈልጋሉ።

ወደ አገርዎ ለመመለስ የማይፈሩ ከሆነ፡ ወይም ደግሞ፡ ይህ አጭር ጽሁፍ ከነበቡ በኃላ የጥገንነት ወይም አገርን ላለመልቀቅ የመከላከል መብት ለማግኘት ብቃት እንደሌልዎት ካስተዋሉ፡ እንዲሁም ደግሞ ሌላ ዓይነት የመከላከል መብት የለልዎት ከሆነ፡ አገርን ለቀው እንዲወጡ መወሰን ወይም ደግሞ "በፈቃደኛነት እንዲመለሱ" መወሰን ትክክለኛ ውሳኔ ይሆናል።



**ነገር ግን፡ ተመልሰው ለመሄድ የሚፈሩ ከሆነ፡ በዚህ ጊዜ ላይ ተስፋ መቁረጥ ትልቅ ስህተት ሊሆን ይችላል። በመጀመርያ ደረጃ ስለህይወትዎ እና ከተመለሱ በኃላ ሊደርስባቸው ስለሚችል አደጋ ማሰብ ይኖርብዎታል።**

ሁለተኛ፡ ለወደፊቱ ወደ አሜሪካ ተመልሶ ለመምጣት የሚያስቡ ከሆነ፡ አገርን ለቆ የመውጣት ወይም በፈቃደኝንነት ለመመለስ መወሰን ስህተት ነው። አገርን ለቆ እንዲወጡ ወይም በፈቃደኝነት እንዲመለሱ ከተደረገ በኃላ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ወደ አሜሪካ አገር ተመልሰው ከመጡ፡ የስራ ፍቃድ አይሰጥዎትም፡ እንዲሁም ደግሞ ሁል ጊዜ DHS እንዳያገኛቸው በፍርሃት ይኖራሉ። ከተያዙ ደግሞ፡ አገርን እንዲለቁ ከተደረገ በኃላ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ በመመለስዎ ይከሰሳሉ። ይህ ወንጀል እስር ቤት የሚያስገባ ነው። ድሮ የፈጸሙት የወንጀል ታሪክ ካለ ደግሞ፡ በሕገወጥ መንገድ ወደ አሜሪካ ስለተመለሱ ሕጉ አንዳንድ ጊዜ፡ 20 ዓመት እንዲታሰሩ ሊፈርድ ይችላል!

እንዲሁም ደግሞ፡ ወደ አሜሪካ ሲመለሱ ከተያዙ እና የጥገኝነት ፍቃድ እንዲሰጥዎት ካመለከቱ፤ በመጀመርያ ጊዜ ለጥገኝነት ወይምን ደግሞ አገርን ለቆ ላለመውጣት ለመከላለክ ስላልፈለጉ፡ ዳኛው፡ ወደ አገርዎ ቢመለሱ ምንም የሚያስጋ አደለም ብሎ ይወስናል።

በመጨረሻ ላይ፡ አገርን ለቆ የመውጣት ውሳኔ መቀበል ወይም "በፈቃደኝንነት መመለስ" የሚባለው ውሳኔ መወሰን፡ በኃላ በሕገወጥ መንገድ ወደ አሜሪካ አገር ለመመለስ፡ በጣም ከባድ ወይም ደግሞ ፈጽሞ የማይቻል ጉዳይ ያደርገዋል። እዚህ

አገር በሕጋዊ መንገድ የሚኖሩ ቤተሰብ ቢኖርዎትም አይጠቅምም። አገርን ለቆ እንዲወጡ ከተደረገ በኃላ ወደ አሜሪካ አገር በህገወጥ መንገድ ከተመለሱ፡ DHS ጉዳይዎ ወደ “እንደገና አገርን ለቆ መውጣት” የሚባል ሂደት እንዲተላለፍ ያደርጋል፤ ይህም ማለት አገርን ለቀው እንዲወጡ የተሰጠው ትእዛዝ "እንደገና" ይደረጋል ማለት ነው። በዚህ ጊዜ DHS ከአገር ያባርርዎታል እና በቃለ መጠይቁ ላይ ወደ አገርዎ ቢመለሱ የሚያሰጋ ወይም የሚያስፈራ መሆኑን በደምብ ካልገነጹ እና በቂ ምክንያት ካልሰጡ በስተቀር፤ ወደ የኢሚግሬሽን ዳኛ ሳይደርሱ እንዲወጡ ይደረጋል።

በዚህ ፅሁፍ ውስጥ እንደሚያዩት፡ መከራከር የሚችሉበት ጉዳይ ካለ አሁኑ መከራከር እንዳለብዎት የበለጠ መንገድ መሆኑን ብዙ ምክንያቶች ያብራራሉ። ነገር ግን በአሜሪካ አገር ለመቆየት የማያስቡ ከሆነ እና፡ አሜሪካ አገር ለቀው እንዲወጡ ከተደረገ፡ ለወደፊት በጉዳይዎ ላይ ምን ለውጥ እንደሚያመጣ የበለጠ ማወቅ ከፈለጉ፡ በዚህ የማብራርያ ጽሁፍ ላይ "በፈቃደኝነት ለመመለስ ማሸነፍ" በሚል ርእስ የተጻፈውን ክፍል ይመለከቱ።

• **ለጥገኝነት ወይም አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላል መብት እንዲሰጠኝ ካመለከትኩኝ፡ በትውልድ አገሬ ያሉትን ቤተሰቦቼ አደጋ ሊደርስባቸው ይችላል ወይ?**

አንዳንድ ሰዎች፡ ለጥገኝነት በሚያመለክቱበት ጊዜ የሚሰጡት መረጃ ወደ የትውልድ አገራቸው ተመልሶ እንዳይደርስ እና እዛ የሚኖሩት ቤተሰቦቻቸውን አደጋ ላይ እንዳይጥሉ ይፈራሉ። በትውልድ አገርዎ በጣም የታወቁ ግለሰብ ካልሆኑ እና ጉዳይዎ በይፋ እንዲታወቅልዎት ካልፈለጉ በስተቀር፡ ይህን ነገር ሊሆን አይችልም። ለጥነኝነት ወይም አገርን ለቆ ላለመውጣት ያመለከቱበት ማመልከቻ ቅጂ ወደ የአሜሪካ አገር የመንግስት ክፍል ይላካል፤ ነገር ግን የመንግስት ክፍሉ ጉዳዩ በተመለከተ የእርስዎ መንግስትን ማነጋገር የለበትም። የጥገኝነት ጥያቄዎች በተመከለተ ምስጢርን በደምብ እንዲጠበቅ የሚያደርግ አሰራር አለ። እንዲሁም ደግሞ፡ በዚህ ነገር የሚያስቡ ከሆነ፡ የኢሚግሬሽን ዳኛውን ማሳወቅ ይችላሉ፤ የፍርድ ቤት ቀጠሮው ደግሞ ለህዝብ ክፍት እንዳይሆንና እንዲዘጋ እንዲሁም የሚሰጡት ማንኛውም መረጃ በሚስጢር እንዲያዝ ማሳሰብ ይችላሉ።



• **የእንግሊዘኛ ቋንቋ በደምብ መናገር እና መስማት የማልችል ከሆንኩኝ፡ ምን ማድረግ ይኖርብኛል?**

በፍርድ ቤት ቀጠሮ ጊዜ የሚጠየቁት ጥያቄዎችን በሙሉ፡ እንዲገባዎት ያስፈልጋል፤ የሚባለውን አንዳንዱ ብቻ ሳይሆን በሙሉ እንዲረዱት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ከዳኛው ጋር በሚነጋገሩ ጊዜ ደግሞ፡ ለዳኛው የሚነግሩትን ነገር በሙሉ ዳኛው በደምብ መስማት እና መረዳት እንዲችል ማድረግ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ስለዚህም፡ የእንግሊዘኛ ቋንቋ በደምብ መናገር እና መስማት የማይችሉ ከሆነ፡ ዳኛውን ማሳወቅ ይኖርብዎታል። ፍርድ ቤቱ ደግሞ ቋንቋዎ መናገር የሚችል አስተርጓሚ እንዲቀርብ ያደርጋል።

> የእንግሊዘኛ ቋንቋ መናገር የማይችሉ እና በደምብ የማይገባቸው ከሆነ፡
>
> ☞ ዳኛውን ይንገሩት።

• **ይህንን አጭር መጽሐፍ እንዴት መጠቀም እችላለሁኝ?**

ለጥገኝነት ወይም አገርን ለቆ ላለመውጣት መከላል መብት ብቁ መሆንዎን ለማወቅ፣ የማመልከቻ ፎርሙ ለሞሙላትና ለፍርድ ቤት ቀጠሮ ለመዘጋጀት ምን ማድረግ እንዳለብዎት ለማወቅ፤ ይህን አጭር ጽሑፍ በሙሉ ማንበብ አለብዎት። ጉዳይዎ እንዲጀምሩት እና ለዳኛው የሚሰጡት አስፈላጊ ማስረጃ (ማረጋገጫ) ካለ ደግሞ በሙሉ ማቅረብ የእርስዎ ፍቃድ እና ሀላፊነት መሆኑን እንዲያውቁ በጣም አስፈላጊ ነው። ለፍርድ ቤት ቀጠሮ ያልተዘጋጁ ከሆነ፡ በቀላሉ ሊሸነፉ ስለሚችሉ፡ ዝግጁ ቢሆኑ በጣም ጠቃሚ ነው።



**• በ INA የሕግ አሰራር አንቀጽ 241(b)(3) መሰረት፡ የጥገኝነት ወይም አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ለማግኘት ምን ዓይነት መማመዘኛዎች ማቅረብ ያስፈልጋል?**

*የጥገኝነት ወይም አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ለማግኘት፡ ሶስት ነገሮች ማሟላት ይሆርብዎታል፥*

1 *የሚፈሩበት በቂ ምክንያት እንዳለ*

2 *ስለ ሚስቃዩ ወይም ደግሞ ለህይወትዎ ወይም ነጻነትዎ የሚያሰጋ ስለሆነ*

3 *በዘርዎ፣ ሀይማኖትዎ፣ የትውልድ አገርዎ፣ የፖለቲካ አስተያየትዎ ወይም በአንድ የህብረተሰብ ክፍል አባል በመሆንዎ ምንንያት።*

*ለእያንዳንዱ መመዘኛ፡ ማብራርያ እንሰጣለን።*

**• እንደምፈራ ለማሳየት ምን ዓይነት ምክንያት ማቅረብ ይኖርብኛል?**

*የጥነኝነት ፍቃድ ለማግኘት፡ በአጠቃላይ ወደ አገርዎ ለመመለስ እንደሚፈሩ እና እንደዛ ሲሉ ደግሞ በቂ የሆነ ምክንያት ማሳየት ይኖርብዎታል። በINA ሕግ አንቀጽ 241(b)(3) መሰረት አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት እንዲሰጥዎት ደግሞ የሚያስቡት ምክንያት ብቻ ሳይሆን፡ ቢመለሱ የስቃይ ቅጣት ሊደርስብዎት እንደሚችል ማሳየት ይኖርብዎታል፤ ነገር ግን የስቃይ ቅጣት ሊደርስ ይችላል ብቻ ሳይሆን <u>እንደሚደርስ የታወቀ ጉዳይ</u> መሆን አለበት። ስቃይ ሊደርስ ይችል ይሆናል የሚል ብዙ የማይታመን ምክንያት ካቀረቡ፡ ዳኛው አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ላይሰጥዎት ይችላል።*

*ከአሁን በፊት የስቃይ ቅጣት የደረሰብዎ ከሆነ፡ እንደገና ቢመለሱ ስቃይ ሊደርስብዎ እንደሚችል ማሳየት ቀላል ይሆናል፤ ነገር ግን የደረሰው ስቃይ መንሲኤው እላይ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች አንዱ መሆኑን ማሳየት ይኖርብዎታል። ይህን ነገር በማመልከቻው እንዲገልጹት እና በፍርድ ቤት ቀጠሮ ጊዜ ደግሞ በሙሉ በዝርዝር ለዳኛው መንገሩ በጣም አስፈላጊ ነው።*

**• "የስቃይ ቅጣት" ምንድን ነው?**

*የጥገኝነት ፍቃድ ለማግኘት፡ በትውልድ አገርዎ የስቃይ ቅጣት እንደ ደረሰብዎት ማሳየት ይኖርብዎታል፡ ወይም ደግሞ እላይ ከተዘረዘሩት አምስት ምክንያቶች አንዱ ወይም ከአንድ በላይ ስለሚመለከትዎ ወደ አገርዎ ቢመለሱ ለህይወትዎ የሚያሰጋ መሆኑን፤ እንዲሁም፡ እነዚህ የተጠቀሱት አምስት ምክንያቶች ለደረሰብዎት ስቃይ ዋና ምክንያት እንደነበሩ ማሳየት ይኖርብዎታል። ይህ ማለት የማስፈራራት፣ የማሰቃየት፣ የማፈን፣ ቁጥጥር ስር የመግባት፣ እስር ቤት የመግባት፣ የአካል ጉዳት የመድረስ፣ በጾታዎ ምክንትያት ተገቢ ያልሆነ አድራጎት የመድረስ፣ ወይም የመግደል ሙከራዎች በእርስዎ ላይ እንደደረሱ እና አሁኑም ሊደርሱ እንደሚችሉ፤ እንዲሁም ደግሞ ነጻነትዎ ከአሁን በፊት እንደተነፈጉ ወይም ወደፊትም ሊደርስ እንደሚችል ማለት ነው። ሌሎች ዓይነት ጉዳቶችም እንደ "የስቃይ ቅጣት" ሊታዩ ይችላሉ፤ እነዚህም አንድ ጊዜ ብቻ ከደረሱ ቀላል የሚመስሉ ነገርግን ከተደጋገሙ ከጊዜ በኃላ፡ የስቃይ ቅጣት ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው። በተጨማሪም፡ ስራ ለማግኘት እና ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ የማይችሉ ከሆነ፡ እንዲሁም ደግሞ በአገርዎ ያሉት ብዙ ሰዎች የሚያንቋሽሽዎት ከሆኑ፡ እነዚህ በሙሉ በአንድ ላይ እንደ የስቃይ ቅጣት ሊታዩ ይችላሉ።*

**• ባለኝ የፖለቲካ አስተያየት፣ የአንድ ማህበረሰብ ክፍል፣ ዘር፣ ሀይማኖት፣ ወይም ትውልድ አባል በመሆኔ፡ የስቃይ ቅጣት ደርሶብኛል ስል ምን ማለት ነው?**



*በትውልድ አገሩ አደጋ የደረሰበት ሰው በሙሉ፡ የጥገኝነት ወይም አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ያገኛል ማለት አይደለም። ጉዳዩ በአሸናፊነት የሚያልቀው፡ በእርስዎ ላይ የስቃይ ቅጣት ያደርሳሉ ወይም ሊያደርሱ ይፈልጋሉ የተባሉትን ሰዎች ወይም ህዝብ፡ ቀጥሎ ከተዘረዘሩትን በአንዱ*

ምክንያት መሆን አለበት፥

--<u>**የእርስዎ የፖለቲካ አስተያየት።**</u> ብዙ ሰዎች ባላቸው የፖለቲካ አስተያየት የተነሳ፡ የስቃይ ቅጣት ይደርስባቸዋል። መንግስቱን ይደግፋ ወይ ይቃወሙ። የፖለቲካ አስተያየታቸው ምክንያት በማድረግ የጥገኝነት ፍቃድ የተሰጣቸው አንዳንዱ ሰዎች እንደሚከተሉ ናቸው፥ በሰለማዊ ሰልፍ ወይም ደግሞ መንግስትን የሚጻረር የተቃውሞ ሰልፍ ያስተባበሩ እና የተሳተፉ ተማሪዎች፣ ማህበርን የሚመሩ፣ የአንድ የፖለቲካ ማህበር አባል የሆኑ፣ ወይም ደግሞ የመንግስት አባል የሆኑ።

አንዳንድ ጊዜ፡ ምንም የፖለቲካ አስተያየት ባይኖርዎትም፡ ሌሎች ሰዎች፡ የአንድ ወገን የፖለቲካ አስተያየት ይኖርብዎታል ብለው ስለ <u>አሰቡ</u> ብቻ፡ ሊበድልዎት ይችላሉ። ይህን ነገር ለማሰብ ያስቻላቸው ደግሞ፡ እርስዎ የሚኖርበት ከተማ፣ የእርስዎ የቤተሰብ አባሎች፣ ወይም ሌላ ምክንያቶችን በማየት ሊሆን ይችላል። በእንደዚህ አይነት ሁኔታ፡ የጥገኝነት ፍቃድ ወይም አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት እንዲሰጥዎት ሊጠይቁ ይችላሉ።


በተጨማሪ ሕጉ የሚለው፡ ጽንስን ለማስወረድ፡ ወይም ደግሞ እንዲገረዙ የሚገደዱ ከሆነና ይህንን ድርጊት የሚፈሩ ከሆነ፡ ወይም ደግሞ ህዝብን በአንድ ላይ አሰባስቦ ቁጥጥር ስር የማስገባት ወይም ደግሞ የፖለቲካ አስተያየትዎ በተመለከተ የስቃይ ቅጣት ልደርስብዎት ይችላል።

 --<u>**የእርስዎ የህብረተሰብ ክፍል።**</u> ብዙ ሰዎች የአንድ "ህብረተሰብ አካል" አባል በመሆናቸው፡ የስቃይ ቅጣት ይደርስባቸዋል። የህብረተሰብ አካል ሲባል፡ የጋራ የሆነ ሊቀይሩት የማይችሉት ወይም የማይገባቸው አስተያየት እና የአኗኗር ዜዴ ያላቸው ሰዎች፡ ማለት ነው። ለምሳሌ፡ የአንድ ቤተሰብ፣ ጎሳ ወይም ብሄር፣ የብሄር ብዱን አባል ሊሆኑ ይችላሉ፤ ወይም ደግሞ አንድ ዓይነት የጾታ ባህርይ ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ።

ለምሳሌ፡ የአንድ አገር መንግስት አንድ ባህል እንዳለ በሙሉ ሊያጠፋው ይፈልጋል እና የባህሉ ተከታይ ዘሮች ደግሞ ይገድላቸዋል። እነዚህ ልዩ ዘር ያላቸው ሰዎች እንግዲህ የአንድ "ማህበረሰብ ክፍል" አባል በመሆናቸው የስቃይ ቅጣት ይደርስባቸዋል ማለት ነው። ወይም ሌላ ምሳሌ ደግሞ፡ የአንድ አገር የሽምቅ ተዋጊዎች፡ የአንድ ማርቲነዝ የሚባል ቤተሰብ አባሎች አፍኖው ይወስዳሉ። እነዛ የሽምቅ ተዋጊዎች፡ የማርቲነዝ ቤተሰቦችን ላይ እየበደሉ ከሆነ፡ የማርቲነዝ ቤተሰብ እንደ አንድ የማህበረሰብ ክፍል ሊታዩ ይችላሉ።

የግብረሰዶም ተግባር የሚፈጽሙ ሰው በመሆንዎ፡ የጉዳት፣ የማስፈራራት፣ ወይም የማንቋሸሽ ድርጊት በእርስዎ ላይ ከተፈጸመ፡ የስቃይ ቅጣት እየደረሰብዎት ነው ሊባል ይቻላል። ለምሳሌ፡ የአገርዎ መንግስት፡ ሰዎች የግብረሶዶም ተከታዮምች በመሆናቸው የሚበድላቸው ከሆነ፡ እና እርስዎ ደግሞ የግብረሰዶም ተከታይ ከሆኑ፡ የጥገኝነት ፍቃድ ወይም አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

በአንዳንድ አገሮች ደግሞ በሴትነታቸው ብቻ የሚጎዱ ከሆኑ እና ለዛ ድርጊት ደግሞ የሚቃወሙ ከሆኑ፡ የአንድ ማህበረሰብ ክፍል ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ። ለምሳሌ፡ በአንዳንድ ሀገሮች፡ ሴቶች የተለየ የእድሜ ክልል በሚደርሱበት ጊዜ የእፍረተ ስጋቸው እንዲቀረጥ ይደረጋል። ይህን የመሰለ ድርጊት ስለሚፈሩ ወደ አገርዎ ለመመለስ የማይፈልጉ ከሆነ ወይም ደግሞ ሴት በመሆንዎ ብቻ ሌላ ዓይነት ተገቢ ያልሆነ ድርጊት እንዳይደርስባቸው የሚፈሩ ከሆነ፡ የጥገኝነት ፍቃድ ወይም አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

 --<u>**ዘርዎ።**</u> ብዙ ሰዎች በዘራቸው ምክንያት የተነሳ ግፍ ይደርስባችዋል። የቆዳዎ ቀለም፣ የትውልድ ዘርዎ፣ ወይም ታሪክዎ በተመለከተ አደጋ የደረሰብዎት ከሆነ፡ የጥገኝነት ፍቃድ ወይም አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

--**<u>ሀይማነትዎ</u>።** ብዙ ሰዎች በሀይማኖታቸው ምክንያት የተነሳ ግፍ ይደርስባችዋል። ሀይማኖትዎን በደምብ ለመከታተል ካልቻሉ፡ ወይም ደግሞ በሚያምኑት እምነት ምክንያት የተነሳ ግፍ ከሰረሰብዎት፡ የጥገኝነት ፍቃድ ወይም አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

--**<u>የትውልድ ዘርዎ</u>።** የትውልድ ዘር ሲባል፡ መጀመርያ የመጡበት አገር ወይም የዜግነት ያገኙበት አገር ሊሆን ይችላል። አንድ ምሳሌ ለመጥቀስ ፡ የኢል ሳልቫዶር ዜጋ ከሆኑ፡ ነገር ግን በሁንድራስ የሚኖሩ ከሆነ፡ ሳልቫዶሪያን በመሆንዎ ግፍ ይደርስብዎታል ማለት ነው።

የጥገኝነት ፍቃድ ለማግኘት ብቁ የሚሆኑ፡ በዘርዎ፣ በሀይማነትዎ፣ በትውልድ አገርዎ፣ ልዩ የሆነ የህብረሰብ አባል በመሆንዎ፣ ወይም ደግሞ የፖለቲካ አስተያየትዎ ምክንያት ስቃይ እንደደረሰብዎ ወይም ለወደፊት ሊደርስብዎት እንደሚችል ምክንያት መሆናቸውን ማሳየት ይኖርብዎታል።

**• ለህይወቴ የሚያሰጋኝ ሰው ወይም ህዝብ የመንግስት አካል መሆን አለበት ወይ?**

አይደለም። አደጋ ያደርስብኛል ብለው የሚፈሩት ሰው፡ የጦር ሀይል፣ የፖሊስ፣ ወታደር፣ የተመረጡ ባለስልጣኖች፣ ወይም የግብረ አሸባሪዎች አባል ሊሆን ይችላል፤ እንዲሁም ደግሞ መግስት ሊቆጣጠራቸው የማይችል ወይም የማይፈልግ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ፡ የሽምቅ ተዋጊዎች፣ ወይም ሌሎች ተቋዋሚ ብድኖች ወይም ሌላ መንግስት ሊቆጣጠረው የማይችል ወይም የማይፈልግ ብዱን ሊሆን ይችላል።

**• በግላዊ ጉዳይ የተነሳ ማስፈራራት ወይም ግፍ የደረሰብኝ ከሆነስ?**

አንድ ሰው ግላዊ በሆነ ጉዳይ የተነሳ <u>ብቻ</u> ካስፈራራዎት፡ የጥገኝነት ፍቃድ ወይም ደግሞ አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ማግኘት አይችሉም። ለምሳሌ፡ በእዳ የተያዙ ከሆነና በዛ ምክንያት የተነሳ ገንዘቡን የወሰዱበት ሰው ካስፈራርዎት፡ ይህ ጉዳይ የጥገኝነት ፍቃድ ወይም አገርን እንዳይለቁ የመከላከል መብት ለማግኘት ምክንያት ሊሆን አይችልም። ገንዘቡን ያበደረ ሰው ወታደር ቢሆንም፡ ጉዳዩ በእርስዎ እና በእርሱ መካከል የሚቀር የግል ጉዳይ ነው።

ነገርግን አንድ ሰው በተለያየ ምክንያት እርስዎን ሊጎዳ ከፈለገ፡ እና ያቀረበው ምክንያት ሁሉ የግል ጉዳይ ካልሆነ፡ብቁ ሊባሉ ይችላሉ። ለምሳሌ፡ ገንዘብ ያበደርዎት ሰው ወደ የጦች ሀይሉ በመሄድ፡ እስርዎ መንግስትን ለመገልበጥ የሚፈልግ ሰው እንደሆኑ አስመስሎ መክሰስ የሚፈልግ ከሆነ፡ በፖለቲካ አስተያየት ምክንያት ነው የተሰቃዩ ለማለት ይቻላል (ምክንያቱም መንግስትዎ የአመራሩ ጠላት እንደሆኑ ብሎ ስለሚያስብ)፡ ስለሆነም የጥነኝነት ፍቃድ ወይም አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ያገኛሉ።

**• ከእነዚህ ምክንያቶች አንዱ በተነሳ ድሮ ስቃይ ደርሶብኝ ከነበረ እና አሁን ግን ወደ አገሬ ብመለስ በነዚህ ምክንያት የተነሳ የስቃይ ቅጣት የማይደርስብኝ ከሆነስ?**

የጥነኝነት ፍቃድ ማግኘት የሚችሉበት መንገዶች ሁለት ናቸው።

1. የኢሚግሬሽን ዳኛ ወይም DHS በጣም አሰቃቂ የሆነ ግፍ ስለደረሰብዎት፡ ወደ አገርዎ ለመመለስ እንደማይችሉ ካረጋገጡ። ድሮ የሰረሰብዎት መከራ በሙሉ ለ DHS እና ለኢሚግሬሽን ዳኛ በዝርዝር መንገር በጣም አስፈላጊ ነው!
2. እላይ ከተዘረዘሩት አምስት ምክንያቶች አንዱ በተነሳ ድሮ የግፍ ወይም የመከራ ጊዜ አሳልፈዋል፤ እንዲሁም አሁን ወደ አገርዎ ቢመለሱ በጣም አሰቃቂ ሁኔታ ሊደርስብዎት ይችላል። ለምሳሌ፡ ባለፈው ጊዜ የተሰቃዩበት ምክንያት በሀይማነትዎ የተነሳ ነው። አሁን ለውጥ መጣ እና በአገርዎ ያሉ የእርስዎ ዓይነት ሀይማኖት ተከታዮች ምንም ችግር አይደርስባቸውም። ነገርግን ወደ አገርዎ ለመመለስ ይፈራሉ፡ ምክንያቱም ከተመለሱ በሌላ ምክንያት የተነሳ አሰቃቂ ጉዳት ሊደርስብዎት ይችላል። በዚህ የተነሳ የጥገኝነት ፍቃድ ሊሰጥዎት ይችላል።

እባክዎን፡ እላይ በተጻፉት ሁለት ሁኔታዎች ምክንያት በማድረግ፡ አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ሊያገኙ

እንደማይችሉ ያስተውሉ። የጥነኝነት ፍቃድ ብቻ ሊያገኙ ይችላሉ።

- **ከአገሬ የወጣሁት ምክንያት በጦርነቱ ላይ ለመሳተፍ ስላፈለግኩኝ ከሆነስ?**

አንደኛ፡ ለምን ለመሳተፍ እንዳልፈለጉ ወሳኝ ምክንያት ይሆናል። የውትድርና አገልግሎትዎ ለመፈጸይ ያልፈለጉ ከሆነ ወይም ደግሞ ከቤተሰቦችዎ ጋር ለመቆየት ስለፈለጉ ወደ ጦር ኃይሉ ለመቀላቀል እምቢ ካሉ፤ በአጠቃላይ፡ ከህሊናዎ፣ ከህይማነትዎ፣ ወይም ከፖለቲካ አስተያየትዎ ጋር የሚጻረር ካልሆነ የጥገኝነት ፍቃፍ ለማግኘት መጣም ከባድ ይሆናል። በሌላ አባባል፡ የፖለቲካ አስተያየት ከሌልዎት፡ በዛ ምክንያት ነው የተሰደዱ ለማለት ያስቸግራል።

እንደገና ደግሞ፡ <u>ለምን ስቃይ ይደርስብዎታል</u> በሚል ጥያቄም የሚወሰን ይሆናል። የሀገራዊ አገልግሎት እንዳይፈጽሙ ስለተቃወሙ፡ መንግስቱ ወይም የሽምቅ ተዋጊዎቹ፡ ሌላ የፖለቲካ ማህበር ነው የሚደግፈው ብሎው ካመኑ፤ ወይም ደግሞ እንደ ጠላታቸው በማየት ካሰቃይዎት፤ መንግስቱ ወይም የሽምቅ ተዋጊዎቹ በፖለቲካ አስተያየትዎ የተነሳ ሊያስቸግርዎት ይችላሉ ለማለት ያስኬዳል (ወይም ደግሞ ልዩ የፖለቲካ አስተያየት አለዎት ብሎ ስለሚያስቡ)። ነገር ግን፡ ለምሳሌ፡ የሽምቅ ተዋጊዎች ስለሚደግፉ ብሎ ሳይሆን የሀገራዊ አገልግሎትዎ ስላልፈጸሙ፡ መንግስትዎ እስር ቤት እንዲገቡ የሚያደርግ ከሆነ፡ የፖለቲካ ጥገኝነት መብት ለማግኘት ብቁ ምክንያት አይሆንም። ምክንያቱ ከእርስዎ የፖለቲካ አስተያየት የሚያገናኝ አደለምና።

ሰዎች በጦርነቱ ላለመሳተፍ ከወሰኑ በኃላ ለጥገኝነት ሲያመለክቱ የሚነሳ በጣም የተለመደ ችግር አንዱ፡ ዳኛው እንዲህ ይላል፥ ስቃይ የደረሰብህ መንግስትህ ሕግን ማስፈጸም ስለፈለገ እንጂ የተለየ የፖለቲካ አስተያየት ያላቸው ሰዎች ሊቀጣ ስለፈለገ አይደለም። ነገር ግን እርስዎ ወይም ልክ እንደ የእርስዎ ሁኔታ ላይ ያሉ ሰዎች፡ እንደተሰቃዩ፣ እንደተገደሉ፣ ወይም እንደተገፉ ካሳዩ፡ ይህንን ነገር የተፈጸመ ደግሞ የመንግስቱ ሕግ እንደሚለው ካልሆነ፡ የጥገኝነት ፍቃድ ሊያገኙ ይችላሉ። ምክንያቱም፡ እርስዎ የተሰቃዩት ወይም በኃላ የሚሰቃዩ በፖለቲካ አስተያየት የተነሳ እንጂ የመንግስትዎ ሕግ ለማስፈጸም ብሎ እንዳልሆነ ስለሚያሳይ።

- **የተሰደድኩት በአገሬ ስቃይ ስለምፈራ ሳይሆን፡ የኑሮየ ሁኔታ ለማሻሻል ከሆነ፡ የጥገኝነት ወይም አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ለማግኘት እችላለሁኝ ወይ?**

ወደ አሜሪካ አገር የመጡ፡ ስራ ለማግኘት ወይም ደግሞ ከረሀብ ለመሸሽ <u>ብቻ</u> ከሆነ፡ ብቁ አይደሉም። ነገርግን ወደ አሜሪካ አገር የመጡ ድሀ ስለሆኑ እና <u>በተጨማሪም</u> በፖለቲካ አስተያየትዎ፣ የአንድ የህብረተሰበ ክፍል አባል በመሆንዎ፣ በጎሳዎ፣ የትውልድ ዘርዎ፣ ወይም ሀይማነትዎ የተነሳ በአገርዎ የሚሰቃዩ ከሆነ፡ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

- **በሌላ ምክንያት የተነሳ ስቃይ እንዳይደርስብኝ የምፈራ ከሆነስ?**

በ INA አንቀጽ 241(b)(3) መሰረት፡ የተሰቃዩበት ምክንያት እላይ ከተጠቀሱት አምስት ምክንያቶች አንዱ የተነሳ ካልሆነ በስተቀር፡ የጥገኝነት ወይም አገርን ለቆ መውጣት የመከላከል ፍቃድ አይሰጥዎትም። ነገርግን፡ <u>አገርዎ በሚገኘው የመንግስት ባለስልጣኖች እንዳይሰቃዩ የሚፈሩ ከሆነ፣ ወይም ደግሞ መንግስትዎ እንዲሰቃዩ ሆን ብሎ ከፈቀደ፣ ነገር ግን እላይ ከተጠቀሱት አምስት ምክንያቶች አንዱ መሆኑን ማስረጃ ለማቅረብ ካልቻሉ፡ በአሜሪካ አገር ከለላ ሊያገኙ ይችላሉ። ይህም "የስቃይ እና ሌላ ጨካኝ፣ ሰብአዊ ርህራሄ የሌለው፣ የሚያሳፍር ግፍ የሚቃወም የተባበሩት መንግስታት ስምምነት መሰረት ይሆናል"</u>። ስቃይን የሚቃወም ስምምነት ከለላ ለማግኘት እንዴት ማመልከት እንዳለብዎት ለማወቅ ይህ አጭር ጽሑፍ ማንበብ ይቀጥሉ።

## • <u>የጥገኝነት ፍቃድ ወይም አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ለማግኘት ብቁ ያልሆነ ማን ነው?</u>

**<u>ጉዳይዎ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ከሆነ፡ ለጥገኝነት እንዲያመለክቱ ሕጉ አይፈቅድም፥</u>**

1) የጥገኝነት ከማመልከትዎ በፊት በአሜሪካ አገር ከአንድ ዓመት በላይ የኖሩ ከሆነ (በዚህ ሕግ አንዳንድ ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል!)።

2) በአሜሪካ በኢሚግሬሽ ፍርድ ቤት ለጥገኝነት አመልክተው የጠፉ ወይም ያልተመለሱ ከሆነ (በዚህ ሕግ ደግሞ አንዳንድ ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል!)።

<u>ቀጥሎ ከተዘረዘሩት አንዱ የሚመለከትዎ ከሆነ፡ በሕጉ መሰረት የጥገኝነት መብት አያገኙም፥</u>

1) በሌላ አገር ውስጥ ጽኑ የሆነ ግንኙነት ወይም ዝምድና ካልዎት እና በዛ አገር ላይ "ተደላድለው መኖር" ይችላሉ ብሎ ከታመነ።

2) "አስከፊ ወንጀል" የፈጸሙ ከሆነ (እታች ተገልጸዋል)።

3) "በዓይነቱ ከባድ የሆነ ወንጀል" የፈጸሙ ከሆነ እና ለህብረተሰቡ አደገኛ ሰው ከሆኑ (እታች ተገልጸዋል)።

4) አንድ ሰው በዘሩ፣ ሀይማነቱ፣ በጎሳው፣ በትውልድ ዘሩ፣ ወይም የህብረትሰበ ክፍል አባል በመሆኑ እንዲሁም ልዩ የሆነ የፖለቲካ አስተያየት ስላለበት ስቃይ የደረሰበት ከሆነ እና እስርዎ ደግሞ ለዛ ሰው ስቃይ ምክንያት የተሳተፉ ከሆነ።

5) የፖለቲካ ወንጀል ሳይሆን ሌላ ወንጀል ከአሜሪካ ውጭ ፈጽመው ከሆነ።

6) ሽብርተኛ ከሆኑ ወይም ደግሞ ለአሜሪካ አገር ጸጥታ አደጋ የሚያመጡ ከሆነ።

<u>ቀጥሎ ከተዘረዘሩት አንዱ የሚመለከትዎ ከሆነ፡ በሕጉ መሰረት አገርን ለቀ እንዳወጡ የመከላከል መብት አያገኙም፥</u>

ከቁጥር 3 እስከ 6 ያሉት እላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ የፈጸሙ ከሆኑ።

"አስከፊ ወንጀል" ፈጽመዋል ብሎ የተከሰሱ ከሆነ፡ አገርን ለቀ እንዳይወጡ የመከላከል መብት <u>ሊያገኙ ወይም ላያገኙ ይችላሉ።</u> አንድ ወይም ከዛ በላይ አስከፊ ወንጀል የፈጸሙ ከሆነ እና ቅጣቱም ተደምሮ እስከ አምስት አመት እስራት የሚደርስ ከሆነ፡ አገርን ለቀ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ለማግኘት ብቁ አይሆኑም። አስከፊ ወንጀል የፈጸሙት ቅጣቱ ተደምሮ ከአምስት አመት እስራት የሚያንስ ከሆነ፡ አገርን ለቀ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ሊያገኙ ይችላሉ፤ ነገርግን የተፈጸመ ወንጀል ወይም ወንጀሎች "በዓይነቱ ከባድ የሆነ ወንጀል" አለመሆናቸውን ማሳየት መቻል አለብዎት። ይህን ለመሰለ ጉዳይ እንዴት መዘጋጀት እንደሚቻል በኃላ እንገልጸዋለን።

- **ወደ አሜሪካ ከመጡ በኃላ የጥገኝነት ፍቃድ የሚያመለክቱት በአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ መሆን አለበት የሚል ሕግ ምንድን ነው?**

እ.ኤ.አ ከሚያዝያ 1፡ 1998 ዓ.ም ጀምሮ፡ በአሜሪካ አገር ከአንድ ዓመት በታች ጊዜ የኖሩ መሆንዎን ካላሳዩ በስተቀር፡ የጥገኝነት ፍቃድ እንዲሰጥዎት ማመልከት አይችሉም። እዚህ አገር ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆዩ ዳኝውን ማስረዳት እና ማሳመን አለብዎት። በዚህ ሕግ ችላ የሚባሉ አንዳንድ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ።

<u>ወደ አሜሪካ ከመጡ በኃላ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ሁለት ነገሮች አንዱ እንደተፈጸመ ማሳየት የሚችሉ ከሆነ፡ የሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ አይመለከምትም፥</u>

1) **አስፈላጊ የሆኑ ለውጦች ተደርገዋል** – እንደ በትውልድ አገርዎ ውስጥ፣ በህይወትዎ ላይ፣ ወይም በአሜሪካ የጥገኝነት ሕግ – እነዚህ ደግሞ በጥገኝነት ጉዳይዎ ለውጥ ካስመጡ። ለምሳሌ፤ በአሜሪካ አገር ለ 2 ዓመት የኖሩ ከሆነ፡ እንደእርስዎ የመሰሉ ሰዎች የሚያሰቃይ መንግስት በአገርዎ ስልጣን ከያዘ፤ ከዚህ በፊት ለጥገኝነት ያላመለከቱ ብቁ ምክንያት እንዳለ ለማሳየት ይችላሉ (ምክንያቱም ከዚህ በፊት የሚያስጋ አደጋ አልነበረምና)።

**ወይም ደግሞ**

2) **"ከቁጥጥር በላይ የሆነ ሁኔታ"** ካጋጠመ እና ምንም ማድረግ ካልቻሉ፡ (ማለትም፡ ባልተለመደ ሁኔታ ላይ ስለነበሩ)፡ በዚህም ምክንያት ወደ አሜሪካ አገር ከገቡ በኃላ በአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለጥገኝነት እንዳያመለክቱ እገዳ ከሆነብዎት። አንዳንድ ምሳሌዎች እታች ተዘርዝረዋል፥

- በጠና ታመው ከነበሩ
- ለረጅም ጊዜ የአእምሮ ወይም የአካል እና የስሜት ጉዳት ከደረሰብዎት ወይም ደግሞ ከአሁን በፊት የደረሰብዎት ግፍ ወይም ስቃይ የተነሳ አካልዎ የተጎዱ ከሆኑ።
- ያለቤተሰብ ወይም የሕግ አሳዳጊ የሚኖሩ ከ 18 ዓመት በታች ዕድሜ ከነበሩ
- ጠበቃ ካልዎት እና ጠበቃዎ ደግሞ፡ ወደ አሜሪካ ከገቡበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ማመልከት እንዳለብዎት ያልነገርዎ ከሆነ።
- አሜሪካ አገር ከገቡ በኃላ ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ገድብ ውስጥ ለጥገኝነት ሲያመለክቱ፡ በሆነ ምክንያት ማመልከቻው የተመለሰ ከሆነ፡ እንደገና ደግሞ መልተው የላኩት ከሆነ
- ጠበቃዎ ወይም ከቤተሰብዎ አባል አንዱ የሞተ ወይም በጠና የታመመ ከሆነ
- ልዩ በሆነ ሕግ መሰረት፣ ለጊዜው የሚሰጥ ቪዛ፣ ሕጋዊ የሆነ የስደተኞች ቪዛ፣ ወይም ደግሞ "parole" የሚባለው ስለተፈቀደልዎት፡ "ለጊዜው የከለላ ፍቃድ" ከነበርዎት።

ወደ አሜሪካ ከገቡ በኃላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እንዳያመለክቱ ያገዳቸው ምክንያት ቢኖርም፡ "ተገቢ" በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ማመልከትዎን ማሳየት ይኖርብዎታል። ለምሳሌ፡ ከሁለት ዓመት በፊት፡ በአገርዎ መንግስት ከተለወጠ እና፡ ያ መንግስት ለህይወትዎ የሚያሰጋ መሆኑን ካወቁ፡ ዳኛው ረጅም ጊዜ ስለጠበቁ አሁን ስለዛ ጉዳይ ማግመልከት አይችሉም ብሎ ለማለት ይችላል።

> ወደ አሜሪካ አገር ከገቡ ከአንድ ዓመት በላይ ከቆዩ በኃላ፡ የጥገኝነት ማመልከት ከፈለጉ፤
>
> ☞ ለምን እንደቆዩ፡ ለዳኛው ማብራርያ ለመስጠት ይዘጋጁ!

ሳያመለክቱ ለምን እንደቆዩ የሚያሳይ ማስረጃ ከጥገኝነት ማመልከቻዎ ጋር አያይዘው ይላኩ። ለምሳሌ፡ የአካል ወይም የአእምሮ ችግር ያጋጠመ ከሆነ፡ ከሐኪሙ ወይም የሕክምና አማካሪው የማስረጃ ደብዳቤ ያቅርቡ።

**ዳኛው የአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ ስላለፈ፡ ለጥገኝነት ማመልከት አይችሉም ብሎ ከወሰነ፡ አገርን ለቆ ላለመውጣት ለመከላከል ሊያመለክቱ እንደሚችሉ ያስታውሱ።**

**• ከአሁን በፊት በአመሪካ አገር ለጥገኝነት አመልክተው ካልተሳኩ፡ ሕጉ ምን ይላል?**

በአሜሪካ ከአሁን በፊት ያመለከቱት በጥገኝነት ጽሕፈት ቤት እንጂ በኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት ካልሆነ፡ ለጥገኝነት እንደገና ማመልከት ይችላሉ። በዚህ ዓይነት ጉዳይ፡ "የጥገኝነት ባለስልጣን" ተብሎ ከሚጠራ ሰው ጋር የቃለ መጠይቅ አድርገው ይሆናል። ነገር ግን ለጥገኝነት ካመለከቱ እና ጉዳይዎ በኢሚግሬሽን ዳኛ ወይም የኢሚግሬሽን የይግባኝ ቦርድ ተብሎ የሚጠራ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ካላገኘ፡ አሁን ለጥገኝነት ማመልከት አይችሉም።

ነገር ግን፡ ጉዳይዎ ተቀባይነት ካጣ ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ አስፈላጊ የሆኑ ለውጦች ከተከሰቱ ወይም እነዚህ እላይ እንደገለጽነው "ከቁጥጥር በላይ የሆነ ሁኔታ" ከሆኑ ይህ ሕግ አይሰራም። **በተጨማሪም፡ ይህ ሕግ አገርን ለቆ ላለመውጣት ከማመልከት እንደማይከለክልዎት ማስታወስ አለብዎት።**

**• ወደ አሜሪካ ከመምጣትዎ በፊት ሌላ ቦታ "ተደላድሎ የኖሩ" ከሆነ ሕጉ ምን ይላል?**

ከአገርዎ ከወጡ በኃላ በሌላ አገር "ተደላድለው የኖሩ" ከሆነ የጥገኝነት መብት ለማግኘት ብቁ አይሆኑም። ይህ ማለት በሌላው አገር ሕጋዊ የሆነ ቋሚ የመኖርያ ፍቃድ፣ ዜግነት፣ ወይ ሌላ ዓይነት ፍቃድ አግኝተው እንዲኖሩ ፍቃድ አግኝተው ነበር ማለት ነው። ነገር ግን ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ነገሮች ማሳየት ከቻሉ፡ "ተደላድለው ኖሩ" አይባልም፥

1) ከስቃይ ለመሸሽ ወደ አሜሪካ ለመምጣት በሌላ አገር ማለፍ ከነበረብዎት እና፡ በዛ አገር የቆዩትም አስፈላጊ ዝግጅት በማድረግ መንገዱን እስከሚቀጥሉ ድረስ ከሆነ፤ እንዲሁም ደግሞ በዛ አገር ሕጋዊ በሆነ መንገድ ለመኖር የሚያስችልዎት ድርጊት ካላደረጉ (ንብረት መግዛት ወይም ትዳር መመስረት የመሳሰሉት)። ወይም ደግሞ

2) እዛ አገር በሚኖሩበት ጊዜ፡ በእርስዎ ላይ ብዙ የኑሮ እገዳ ከነበረ፤ ለምሳሌ፡ የመስራት መብት፣ የንብረት ባለቤትነት መሆን፣ ጥሩ በሆነ መኖርያ ቤት የመኖር፣ ከቦታ ወደ ቦታ የመዘዋወር፣ ወደ ትምህርት ቤት የመሄድ፣ በመጨረሻም የዜግነት መብት የማግኘት የመሳሰሉት።

አስከፊ የሆነ ወንጀል መፈጸም ማለት ምንድነው? እኔ የፈጸምኩት ከሆነስ?

| |
|---|
| ⚡ አስከፊ የሆነ ወንጀል ፈጽመዋል ተብሎው ከተከሰሱ፡ የጥገኝነት ፍቃድ ለማግኘት ብቁ አይደሉም፡ ነገር ግን፡ የተፈረደብዎት ከአምስት ዓመት በታች ከሆነ፡ አገርን ለቆ ላለመውጣት ለመከላከል ማመልከት ይችላሉ። |

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አንዳንድ በጣም የታወቁ አስከፊ ወንጀሎች ናቸው። የሂዝ ሙሉ ዝርዝር ለማንበብ ከፈለጉ፡ በዩናይትድ ስቴት ኮድ ቁጥር 8 አንቀጽ1101(a)(43) ወይም የኢሚግሬሽን እና የዜግነት ሕግ አንቀጽ 101(a)(43) የምልከቱ።

አስከፊ የሆኑ ወንጀሎች፥

አንዳንድ የአደንዛዥ እጽ ወንጀል ወይም የመሳርያዎች፣ ፈንጆች፣ ወይም የአደንዛዥ እጾች መነገድ፥ የአንደንዛዥ እጽ መነገድ ሲባል የሚከተሉትን ያጠቃልላል፥

- ማጓጓዣ፣ ማከፋፈል፣ ከውጭ ማስመጣት፤
- መሸጥ እና ለመሸጥ ማከማቸት፤
- የአንዳንድ የኮከይን እጽ ባለቤት ሆኖ የመገኘት ወንጀል (የእርስዎ ጉዳይ በየትኛው አቃቤ ሕግ እንደተፈረደ ይወሰነዋል)፤
- አንዳንድ ቀላል የሆኑ የአደንዛዥ እጽ ባለቤት ሆኖ የመገኘት ወንጀል

አንድ ዓመት ወይም ከዛ በላይ ቅጣት የሚያስጥዎት አንዳንድ ወንጀሎች፡ (ያገልግሉት ወይም አያገለግሉ) ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ያጠቃልላሉ፥

- ስርቆት (የተሰረቀውን ንብረት መቀበል የሚያጠቃልል)
- ቤት ሰብሮ የምግባት ወንጀል
- የአመጽ ወንጀል (ጉልበትን ተጠቅሞ ሰው ወይም ንብረትን አደጋ ላይ መጣል የሚያጠቃልል፡ ጉልበት ባይጠቀሙም ወንጀል ነው)
- ወረቀት ላይ ማጭበርበር (የውሸት ወረቀት መጠቀም፣ መስራት ወይም ባለቤትነት መሆን ያጠቃለለ) – የመጀምርያ ወንጀል ሆኖ ባለቤትዎ፣ ሚስትዎ፣ ልጅዎ፣ ወይም ቤተሰቦችዎ ለመርዳት ያደረጉት ካልሆነ በስተቀር
- ፍትህን፣ እና የፍርድ ቤት ውሳኔ ማበላሸት እንዲሁም ለምስክርነት ጉቦ መስጠት
- ንግድን በተመለከተ ጉቦ መስጠት፣ የውሸት ወረቀት መስራት፣ በውሸት ወረቀትን አስተካክሎ ማቅረብ፣ የተለወጠ መለያ ቁጥር ያላቸው ተሽከርካሪዎችን መላክ እና ማስመጣት
- አስገድዶ መድፈር
- ለአቅመ አዳም ባልደረሱ ልጆች ጋር ወሲብ መፈጸም
- መግደል
- የመሳርያዎች ወንጀል፣ የተከለከለ መሳርያ ባለቤትነት መሆንን የሚያጠቃልል

- የቁማርተኛነት ወንጀል፡ ለዚህም የአንድ ዓመት ወይም ከዛ በላይ የእስራት ቅጣት ሊያስከትል ይችላል።
- የውጭ አገር ሰዎችን የማስመጣት እና የመላክ ወንጀል (የመጀምርያ ወንጀል ሆኖ ባለቤትዎ፣ ሚስትዎ፣ ልጅዎ፣ ወይም ቤተሰቦችዎ ለመርዳት ያደረጉት ካልሆነ በስተቀር)
- በገቢ ግብር ማጭበርበር ወይም የግብር አመጽ፡ የደረሰበት ሰው ከ$10,000 በላይ ኪሳራ የደረሰበት ከሆነ
- ቀጥሎ በተዘረዘሩት ወንጀሎች <u>ከተከሰሱና፡</u> በአካል ሳይገኙ ቢቀሩ (1) በወንጀል ተከሰው፡ ቢያንስ ከ2 ዓመት ፍርድ መቀበል ሲገባቸው በፍርድ ቤት ቀጠሮዎ ቀን ላይ ሳይመጡ ቢቀሩ (የ2 ዓመት ፍርድ ባይሰጣቸውም) ወይም ደግሞ (2) እስከ 5 ዓመት እስራት ፍርድ መቀበል ሲገባቸው በቀጠሮው ቀን ሳይመጡ ሲቀሩ
- የገንዘብ ምንዛሬ (ከ$10,000 በላይ የሆነ)

እላይ የተዘረዘሩትን ወንጀሎች አንዱ እንኳን ለመፈጸም አቅደው ወይም ተባብረው የተከሰሱ ከሆነ፡ አስከፊ ወንጀል የፈጸመ ወንጀለኛ ይባላሉ።

አስከፊ ወንጀል በመፈጸም የተከሰሱ ከሆነ፡ እና ከኢሚግሬሽን ጠበቃ እርዳታ ለማግኘት ከቻሉ፡ ጠበቃዎ የተከሰሱበት ክስ በደምብ እንዲመረምረው ጠይቁት። አንዳንድ ጊዜ የኢሚግሬሽን ጠበቃ፡ ክሱ አስከፊ ወንጀል አይደለም ብለው ለመከራከር ይችላሉ። በተጨማሪም፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ፡ የወንጀል ጥበቃ የተከሰሱበት ክስ ፋይሉ እንደገና እንዲከፈት እና የክሱ ዓይነት እንዲቀየር ሊያደርጉ ይችላሉ።

ወንጀለኛ ነው ተብሎ አንዴ ከተወሰነ፡ የክሱ ጉዳይ እንደገና ለመክፈት ከባድ ስለሆነ፡ ለኢሚግሬሽን እንዲመች ተብሎ ክሱን የሚቀይሩበት የተወሰኑ መንገዶች ብቻ ነው ያሉት። ለውጡ የተፈለገበት ምክንያት፡ ከአሜሪካ አገር እንዳይወጡ ለማድረግ ብቻ ከሆነ፡ የተከሰሱበት ክስ ወይም የተወሰነው ፍርድ እንዳይቀየር DHS ሊቃወም ይችላል። በዚህ ጉዳይ የበለጠ መረጃ ከፈለጉ፡ ልምድ ያለው የኢሚግሬሽን ጠበቃ ያነጋግሩ።

**• የአስከፊ ወንጀል ክስ ከተከሰስኩኝ በኃላ የተሰጠኝ ቅጣት ከ5 ዓመት በታች ከሆነስ?**

በዚህ ሁኔታ ላይ፡ የጥገኝነት ፍቃድ እንዲሰጥዎት ማመልከት አይችሉም፡ ነገርግን አገርን ለቆ እንዳይወጡ ለማመልከት ይችላሉ። የፈጸሙት ወንጀል "በዓይነቱ ከባድ የሆነ ወንጀል" መሆኑን እና አለመሆኑን ዳኛው መወሰን አለበት፤ እንደዛ እንደሆነ ዳኛው ከወሰነ ደግሞ፡ አገርል ለቆ እንዳይወጡ የማመልከት ፍቃድ ለማግኘት ብቁ አይባሉም። ይህን ውሳኔ ለመስጠት ዳኛው የሚፈልጋቸው እውነቶች ምን እንደሆኑ በዝርዝር እንገልጻለን፤ አሁን መረዳት ያለብዎት ግን፡ አብዛኛው ጊዜ አስከፊ ወንጀል "በዓይነቱ ከባድ የሆነ ወንጀል" እንደሚሆን ነው። የፈጸሙት ወንጀል በተመለከተ ቀለል ያለ ጉዳይ የሚያደርገው ልዩ የሆነ ምክንያት መኖሩን ማሳየት ከቻሉ ብቻ ነው ዳኛው አገርን ለቆ እንዳይመጡ የመከላከል መብት የሚሰጥዎት።

**• አስከፊ <u>ያልሆነ</u> ወንጀል በመፈጸሜ የተከሰስኩኝ ከሆነ፡ የጥገኝነት ፍቃድ ወይም አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ሊሰጠኝ ይችላል ወይ?**

ምናልባት ይሰጥዎት ይሆናል፤ ነገርግን ዳኛው የእርስዎ ክስ "በዓይነቱ ከባድ የሆነ ወንጀል" ነው ብሎ ካልወሰነ በስተቀር ነው።የፈጸሙት ወንጀል "በዓይነቱ ከባድ የሆነ ወንጀል" መሆኑን እና አለመሆኑን ለማየት የሚያስችል ዝርዝር የለም። እያንዳንዱ ጉዳይ ልዩ ነው እና፤ ጉዳይዎ ከባድ መሆኑን ለመወሰን ዳኛው የሚያያቸው 4 ነገሮች አሉ። እነዚህ 4 ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፥

1) የወንጀሉ ባህርይ (ምን ዓይነት ወንጀል እንደሆነና ምን እንደተፈጸመ)፣

2) የተቀበሉት ቅጣት (ከባድ ወይም ቀላል ቅጣት መሆኑን)፣

3) ወንጀሉ የተፈጸመው በሰው ላይ ነበር ወይም በንብረት ላይ፣ እንዲሁም

4) የወንጀሉ ባህርይ ሲታይ፡ እርስዎ በህብረተሰቡ ውስጥ እንደ አደገኛ ሰው ይታያሉ ወይ።

ወንጀሉን ሲፈጽሙ፡ መሳርያ ተጠቅመው ከሆነ፣ የረጅም ጊዜ ቅጣት የተቀጡ ከሆነ፣ ሌላ ሰው የጎዱ ከሆነ፣ ወይም አደጋ ላይ የጣሉ ከሆነ፡ ዳኛው በዓይነቱ ከባድ የሆነ ወንጀል እንደተፈጸመ ሊወስን ይችላል፤ ስለዚህም የጥገኝነት ወይም አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት አይሰጥዎትም።

ወንጀሉን ለምን እንደፈጸሙ ዳኛውን የሚያስረዳ፡ ወይም ደግሞ ወንጀሉ ለምን ከሚመስለው ይልቅ የቀለለ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ካለ፡ ለዳኛው እና ለ DHS ማሳየት ይኖርብዎታል። ለምሳለ፡ ወንጀሉን ሲፈጽሙት በአእምሮ በሽታ የሚሰቃዩ ከሆነ፡ ይህም ችግር አስመልክቶ ደግሞ ወደ ሐኪም ወይም የሕክምና አማካሪ ሄደው ከነበሩ፡ ይህ ሁሉ ለዳኛው ለማሳየት፡ ከሐኪሙ ማስረጃ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርብዎታል። ወንጀሉን በተመለከተ አደገኛ ሰው እንዳልሆኑ የሚያሳዩ፡ ከወንጀል ጠበቃ ወይም ወንጀሉን ሲፈጽሙ በዛ ቦታ የነበረ ሰው የተገኘ ደብዳቤ የመሳሰሉት ማስረጃዎች ካሉ፡ ወደ ዳኛው እና DSH ማቅረብ ይኖርብዎታል። እነዚህ ማስረጃዎች ግን በተቻለ መጠን ቶሎ ብለው ማሳየት ይኖርብዎታል።

ዳኛው የፈጸሙት ወንጀል በዓይነቱ ከባድ ነው ብሎ ውሳኔ ስለሰጠ ከተሸነፉ፡ እና ከተሰጠው ውሳኔ ጋር የማይስማሙ ከሆኑና ይግባኝ ለማለት ከፈለጉ፡ በሚያስገቡት የይባኝ ማመልከቻ፤ ዳኛው የእርስዎ ወንጀል በዓይነቱ ከባድ ነው ብሎ ውሳኔ ሲያስተላልፍ ትክክል እንዳልነበረ እና ይህንን ማብራራት እንደሚችሉ መጻፍ ይኖርብዎታል። በዚህ አጭር ጽሑፍ ወደ የመጨረሻ ገጽ አከባቢ ስለ ይግባኝ ማብራርያ ጽፈናል።

- **በፈጸምኩት ወንጀል የተነሳ የጥገኝነት ፍቃድ ወይም አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ካልተሰጠኝ፤ ነገር ግን ከመንግስት ስቃይ ሊደርስብኝ እንደሚችል በቂ ምክንያት ካለኝ ምን ይከተላል?**

አስቀድመን እንደገለጽነው፡ መንግስት ወይም የመንግስት ባለስልጣን የሚፈሩ ከሆነ፡ በተባበሩት መንግስታት ጸረ ስቃይ ስምምነት ስር በመሆን ከአገር እንዳይባረሩ ለመከላከል ማመልከት ይችላሉ። ከባድ በሆነ ወንጀል የተከሰሱ ቢሆኑም፡ ማመልከቻዎ ተግባራዊ ይሆናል። ይህን ዓይነት ከለላ በተመለከተ እታች በዝርዝር እንገልጸዋለን።

- **አንድ ሰው ሌላ ሰውን ካሰቃየ ሕጉ ምን ይላል?**

አንድ ሰው በፖለቲካ አስተያየቱ፣ የአንድ ህብረተሰብ አባል በመሆኑ፣ በዘሩ፣ በትውልዱ፣ በሀይማኖቱ፣ የተነሳ ስቃይ በሚደርስበት ጊዜ እርስዎ ደግሞ ስቃይ እንዲደርስበት ያደረጉ ከሆነ፡ ለጥገኝነት ወይም አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ለማግኘት ብቁ አይሆኑም። የአለቃዎ ትእዛዝ የፈጸሙ ቢሆኑም እንኳን ይህን ነገር እንዳለ ይጸናል። ነገር ግን፡ በጦርነት ጊዜ ከሌሎች ወታደሮች ወይም የሽምቅ ተዋጊዎች ጋር መዋጋት ከሆነ ስቃይ አይደለም።

- **ዳኛው የጥገኝነት ፍቃድ ወይም አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ላለመውጣት የሚከለክሉት ሌሎች ወንጀሎች ወይም ድርጊቶች አሉ ወይ?**

በወንጀል ክስ የተከሰሱ ከሆነ፤ ከዚህ በፊት እንደገለጽነው፡ የጥገኝነት ፍቃድ ወይም አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ለማግኘት አይችሉም። ዳኛው እላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች አንዱ እንደተሳተፉ እና ከአሜሪካ አገር ውጭ የፈጸሙት ወንጀል ደግሞ "በዓይነቱ ከባድ የሆነ ወንጀል" ነው ብሎ ከወሰነ፡ ይህ አይነት ወንጀል የፖለቲካ ወንጀል አይደለም፡ ስለዚህም እርስዎ በአሜሪካ አገር ሽብር እንደሚያመጡ ወይም ደግሞ የአገሪትዋ ጸጥታ አስጊ እንደሆኑ ተብሎ ይወሰናል። በተጨማሪም፡ ሰዎችን በአንድ ላይ አሰባስቦ መግደል፣ መሰቃየት፣ ወይም ሌላ ከሕግ ውጭ የሆነ የመግደል ወንጀል ከፈጸሙ አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ለማግኘት ብቁ አይሆኑም። የጥገኝነት መብት በዳኛው ውሳኔ የሚወሰን ስለሆነ፡ ዳኛው የፈጸሙት ወንጀል "በዓይነቱ ከባድ የሆነ ወንጀል" አይደለም ብሎ ካመነ፡ ነገር ግን የተፈጸመውን ወንጀል የጥገኝነት ፍቃድ ለመስጠት በመወሰን ላይ ተራ ይጫወታል። እንዲሁም ስለእርስዎ ሌሎች ተገቢ ያልሆኑ ነጥቦች ካሉ ዳኛው ሊያየው ይችላል፡ ለምሳሌ ወደዚህ አገር ለመምጣት ወይም ስራ ለማግኘት የውሸት ወረቀት የተጠቀሙ

ከሆነ ዳኛው ያየዋል። እንዲሁም ዳኛው ሌሎች፡ እንደ ወደ አገርዎ ቢመለሱ የሚያጋጥም አደጋ፣ ጤንነትዎ፣ ዕድሜዎ፣ እንዲሁም በአሜሪካ ውስጥ ቤተሰብ ካልዎት የመሳሰሉት ነገሮች ማየት ይኖርበታል፡

በ INA ሕግ አንቀጽ 241(b)(3) መሰረት፡ አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት የሚያገኙ፥

- "በዓይነቱ ከባድ የሆነ ወንጀል" ካልፈጸሙ፣
- እላይ ከተጠቀሱት የሰዎች መሰረታዊ መብቶች ምክንያት በማድረግ፡ የሌሎች ሰዎች መሰቃየት ላይ ያልተሳተፉ ከሆነ፣
- የፖለቲካ ወንጀል ሳይሆን፡ ሌላ ከባድ የሆነ ወንጀል፡ ከአሜሪካ ውጭ የፈጸሙ ከሆነ፣
- ሽብር እንደሚያመጡ ወይም ደግሞ የአሜሪካ አገር ጸጥታ አስጊ እንደሆኑ ካልተባለ፣ እንዲሁም
- ሰዎችን በአንድ ላይ አሰባስቦ መግደል፣ ማሰቃየት፣ ወይም ሌላ ከሕግ ውጭ የሆነ የመግደል ወንጀል ያልፈጸሙ ከሆነ፣

በዘር፣ ሀይማኖት፣ ትውልድ፣ የፖለቲካ አስተያየት፣ ወይም የአንድ ህብረተሰብ ክፍል አባል መሆንዎ የተነሳ ወደ አገርዎ ቢመለሱ ህይወትዎ ወይም ነጻነትዎ አደጋ ላይ መጣል እንደመሆኑ ማሳመን ከቻሉ፡ ሌሎች ተገቢ ያልሆኑ ጸባዮች ቢታዩም፡ ዳኛው ያመለከቱትን ጥያቄ መስጠት <u>አለበት</u>። ነገር ግን አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ለማግኘት የጥገኝነት ፍቃድ ከማግኘት የከበደ መሆኑን ያስታውሱ፡ ምክንያቱም ወደ አገርዎ ከተመለሱ በህይወትዎ ወይም በነጻነትዎ ላይ <u>በእርግጥ አደጋ እንደሚደርስብዎት</u> ማስረጃ ማቅረብ አለብዎት።

## • <u>ስቃይን የሚቃወም የስምምነት (CAT) ከለላ ለማግኘት ማን ማመልከት ይችላል?</u>



### የ CAT ከለላ ለማግኘት ምን መመዘኛዎች ያስፈልጋሉ?

<u>በ CAT ሕግ መሰረት ከለላ ለማግኘት የሚከተሉትን ነገሮች ማሳየት አለብዎት፥</u>

አገርዎ ከተመለሱ፡ የመንግስት ባለስልጣኖቹ ወይም ሌላ ከመንግስት ጋር የሚስማማ ሰው በእርግጥ እንደሚያሰቃይዎት፡ ማረጋገጥ ይኖርብዎታል። በምን ምክንያት የተነሳ እንደሚሰቃዩ ለመግለጽ አያስፈልግዎትም። እንደሚሰቃዩ ብቻ ማሳየት ይኖርብዎታል።

እላይ ለተጻፈው ሕግ ሌላ መንገድ ወይም አማራጭ የለውም። እንደ የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ሳይሆን፤ የINA ሕግ አንቀጽ 241(b)(3)፡ ከአሁን በፊት በወንጀል እንደተከሰሱ፣ ከአሁን በፊት ሌላ ሰው አሰቃይተው ከሆነ፣ ሌላ ልዩ የሆነ ጸባይ ካልዎት፣ ወይም ደግሞ ለአሜሪካ ጸጥታ አስጊ ከሆኑ የሚባሉ ነገሮችን ማየት አያስፈልግም። እላይ የተዘረዘሩት መመዘኛዎች የሚያሟሉ ከሆነ የ CAT ከለላ ለማግኘት ብቁ ነዎት። በ INA ሕግ አንቀጽ 241(b)(3) መሰረት የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ማግኘት ግን እንደዚህ አደለም፤ በዚህ ጽሑፍ ላይ በኃላ እናያዋለንና። ስቃይ የሚፈሩ ከሆነ እና የጥገኝነት ፍቃድ ወይም አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ለመግኘት ብቁ ካልሆኑ፡ የCAT ከለላ ለማግኘት ያመለክቱ። ሶስቱም የማሳረፍያ/ከለላ ዓይነቶች ለማግኘት ብቁ ከሆኑ፡ ለእርስዎ ያለን ምክር ለሶስቱም እንዲያመለክቱ ነው።

**• ስቃይ ምንድን ነው?**

አንድ ሰው በእርስዎ ላይ ሆን ብሎ ከባድ የህይወት ጉዳት ለማድረስ ሲሞክር ማለት ነው። የሚደርሰው የአካል ወይም የአእምሮ ስቃይ ወይም ጉዳት ሊሆን ይችላል። ይህን ዓይነት ስቃይ በሚደርስብዎ ጊዜ ሙሉ በሙሉ በሌላ ሰው ቁጥጥር ስር መሆን አለብዎት። በሌላ አባባል፡ ስቃዩን ለማምለጥ አይችሉም ማለት ነው። ስቃይ ስንል የተለያዩ ድርጊቶችን እንደ አስገድዶ መድፈር፣ በኤለክትሪክ ማቃጠል፣ አእምሮን የሚጎዳ መሳርያ መጠቀም፣ መደብደብ፣ እንዲሁም እንደዚህ

ዓይነቶቹ ስቃይመፈጸም ማስፈራራት።

**• አንድ ሰው ከመንግስት ጋር በመስማማት ድርጊቱን ይፈጽማል ሲባል ምን ማለት ነው?**

ይህ ማለት፡ የመንግስት ባለስልጣኖች፡ ሌላ ሰው እንዲያሰቃይዎ ፍቃድ ይሰጣሉ ማለት ነው። ስቃዩ በሚፈጸምበት ጊዜ ደግሞ የመንግስት ባለስልጣኑ የግድ እዛ መገኘት የለበትም። ይህ ማለት፡ መንግስት የሚደርሰውን ስቃይ ያውቃል ነገር ግን መንግስቱ ስቃዩን የማስቆም ግዴታ ቢኖሮውም፡ ስቃዩ ለማስቆም ምንም እርምጃ አይወስድም፡ ማለት ነው።

**• የ CAT ከለላ ጥቅሞች ምንድን ናቸው?**

አገርን ለቀው እንዳይወጡ ከCAT የከለላ ፍቃድ ከተሰጥዎት፡ ስቃይ እንዳይደርስብዎት ወደሚፈሩት አገር አይላኩም። "አገርን ለቀው እንዳይወጡ የመከላከል" ወይም ደግሞ "አገርን ለቆ የማስወጣት ሂደት የመዘግየት" መብት ይሰጥዎታል።

"አገርን ለቀው እንዳይወጡ የመከላከል" በCAT ሕግ መሰረት እላይ እንደተለጸው በ INA ሕግ አንቀጽ 241(b)(3) መሰረት አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ማግኘት ጋር አንድ አይነት ነው። አንድ ዓይነት ጥቅሞች አሉት። ለምሳሌ፡ ከDHS ወጥተው የስራ ፍቃድ እንዲያገኙ ያስችላል። ሕጋዊ የሆነ ቋሚ የመሮርያ ፍቃድ ሊያገኙ አይችሉም፤ እንዲሁም ባለቤትዎ ወይም ልጆችዎ ወደ አሜሪካ አገር ሊያስመጡ አይችሉም። ይህ የከለላ ፎርም አንድ ዓይነት ቅርጽ አለው። በሌላ አባባል፡ እታች የተዘረዘሩት ነገሮችን የሚመለከትዎ ከሆነ በ CAT ሕግ መሰረት አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ያገኛሉ፥

1) **"በዓይነቱ ከባድ የሆነ ወንጀል"** ያልፈጸሙ ከሆነ (ወደፊት ይብራራል)፣
2) እላይ የተዘረዘሩት መሰረታዊ የሆኑ መብቶች አስመልክቶ **በሌሎች ሰዎች መሰቃየት ላይ** ያልተሳተፉ ከሆነ፣
3) የፖለቲካ ወንጀል ሳይሆን ሌላ **በዓይነቱ ከባድ የሆነ** ወንጀል ከአሜሪካ ውጭ ያልፈጸሙ ከሆነ፣ እንዲሁም
4) **ሽብርተኛ** ካልሆኑ ወይም ደግሞ **ለአሜሪካ አገር ጸጥታ አደጋ የሚያመጡ** ያልተባሉ ከሆኑ።

እላይ ከተዘረዘሩት ወንጀሎች አንዱይ የፈጸሙ ከሆነ፡ ወይም ደግሞ ለአሜሪካ አገር ጸጥታ አደገኛ ነው ከተባሉ በ CAT ሕግ መሰረት አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት አያገኙም። ነገር ግን በCAT ሕግ ስር "አገርን ለቆ የማስወጣት ሂደት የመዘግየት" ፍቃድ ሊያገኙ ይችላሉ።

"አገርን ለቆ የማስወጣት ሂደት የመዘግየት" ፍቃድ ካገኙ ጥቅሙ እንደ አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ማግኘት አይሆንም። አገር እንዲለቁ ትእዛዝ ይቀበላሉ፡ ነገር ግን ትእዛዙ እንዳይፈጸም ይዘገያል። በነዚህ ሁለቱ ፍቃዶች መካከል ያለው ልዩነት፡ ሁኔታው ከተቀየረ የማስወጣት ሂደቱ የመዘግየት ፍቃድ የተሰጠው ሰው ለማስወጣት ቀላል ይሆናል። በተጨማሪም፡ በCAT ስር የማስወጣት ሂደት መዘግየት ፍቃድ ካገኙ፡ DHS በቁጥጥሩ ስር እንዲቆዩ ለማድረግ ይሞክራል። DHS ከእስር ቤቱ እንዲወጡ የሚፈቅድልዎት፡ በማህበረሰቡ አደጋ እንደማያደርሱ ለDHS ማሳመን ከቻሉ ብቻ ነው።

በ CAT ሕግ ስር የማስወጣት ሂደት የመዘግየት ፍቃድ ካገኙ፡ በኃላ ቢመለሱ እንደ ማይሰቃዩ ከታወቀ DHS የተሰጡትን ፍቃድ እንዲሻር ሊያደርግ ይችላል። DHS ይህን ማድረግ የሚችለው፡ በኢሚግሬሽን ዳኛ ፊት ብቻ ነው። ይገኙትን የማስወጣት ሂደት መዘግየት ፍቃድ ደግሞ በራስዎ ፍቃድ እንዲሻር ሊያደርጉት ይችላሉ።

ለምሳሌ፡ የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ከ የማስወጣት ሂደት መዘግየት ፍቃድ የበለጡ ከለላ ናቸው። ነገር ግን፡ ለእነዚህ የማረፍያ/ከለላ መብቶች በሙሉ ብቁ ከሆኑ፡ ለሁሉም እንዲያመለክቱ እንደገና ልናሳስብ እንወዳለን።

እንደሚሰቃዩ ማስረጃ ቢያመጡም፡ እዛ ያለው መንግስት ስቃይ እንደማያደርስብዎት ቃል ከገባ DHS ወደ አገርዎ ሊመልስዎት ይችላል። በDHS መንገጫ መሰረት፡ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ብዙ አይፈጸምም።

**• በCAT ሕግ ስር ከለላ ለማግኘት እንዴት ማመልከት ይገባኛል?**

ለ CAT ከለላ ለማግነት የሚያመለክቱት ይህ የመጀመርያ ጊዜ ከሆነ፡ ልክ የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ለምግኘት እንደሚያመከልቱ ማመልከት ይችላሉ። ማመልከቻዎ ወደ የኢሚግሬሽን ዳኛ ያቀርባሉ።

**• የCAT ከለላ ለማግኘት ምን ዓይነት ማመልከቻ ነው መጠቀም ያለብኝ?**

ልክ የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ለማግኘት የሚጠቀሙበት የማመልከቻ ፎርም፡ ለጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት የሚለው የI-589 ፎርም ማመልከቻ ይጠቀማሉ። ፎርሙን እንዴት ሞምላት እንደሚችሉ የሚገልጽ እታች የጻፍነውን ይመለከቱ። በጥያቄ ቁጥር 4 ክፍል B ያለውን ነገር በደምብ እዩት። ጥያቄው የሚጠይቀው ስቃይ ይፈራሉ ወይ የሚል ነው። በተቻለ መጠን ሰፊ እና ዝርዝር መልስ ለመስጠት ሞክሩ። ከአሁን በፊት ያሳለፉት ማንኛውም ዓይነት ስቃይ በሙሉ በማመልከቻው መግለጫ ክፍል ላይ ይጻፉት።

**• ስቃይ ሊደርስብኝ እንደሚችል ማስረጃ እንዴት ማቅረብ እችላለሁኝ?**

በዚህ አጭር ጽሑፍ ላይ የጥገኝነት ፍቃድ ወይም አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ለማግኘት እንዴት ማሳመን እንደሚቻል አብራርተናል። ስቃይ እንደሚደርስብዎት ለማሳመን ምን ማድረግ እንዳለብዎት ምክር ለማግኘት ይህን ክፍል አንብቡት። ይህ ማስረጃም፡ በጣም ተማሳሳይ ነው። ለምሳሌ፡ በአገርዎ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ እንዲሁም/ወይም የእርስዎ ችግር በደምብ ከሚያውቁት ሰዎች ደብዳቤ ማስመጣት፣ በአገርዎ ምን ሁኔታ እንዳለ የሚገልጹ ጋዜጣዎች እና ጽሑፎች ወይም ደግሞ በአገርዎ ያሉት ሰዎች እየተሰቃዩ መሆናቸውን የሚያሳዩ በየሰብአዊ መብት ማህበሮች የተጻፉ ጽሑፎችን ማሰባሰብ ጠቃሚ ይሆናል።

ለ CAT ከለላ እንዴት ማመልከት እንዳለብዎት የበለጠ መረጃ ለማግኘት፡ በዚህ አድራሻ ይጻፉ፥

World Organization for Human Rights USA, 1725 K Street NW, Suite 610 **ዋሽንግተን፡ ዲሲ** 20006 (info@humanrightsusa.org) **ስ.ቁጥር፡** 202-296-5702; **ፋክስ**: 202-296-5704

ዓለምአቀፋዊ የሰብአዊ መብት ማህበር፡ የተባለው ስቃይ የሚደርስበት አካል ለመርዳት የሚጥር ማህበር ነው። ወደዚህ ማህበር ከጻፉ፡ ስለ ጉዳይዎ በተቻለ መጠን በሰፊ በመዘርዘር ወደ አገርዎ ከተመለሱ ለምን ስቃይ እንደሚፈሩ ይግለጹት።

## • <u>የጥገኝነት ፍቃድ፣ አገርን ለቀው እንዳይወጡ የመከላከል መብት ወይም ስቃይን የሚቃወም የስምምነት ከለላ ለማግኘት እንዴት ማመልከት አለብኝ?</u>

በመሰረቱ፡ ጉዳይዎ ሁለት ክፍል የያዘ ነው።

- **የጉዳዩ የመጀመርያ ክፍል፥**

በጉዳይዎ የመጀመርያ ገጽታ ላይ፡ Master Calendar Hearing ተብሎ የሚጠራ ከመጀመርያዎቹ ፍርድ ቤት ቀጠሮዎች አንዱ፡ ዳኛው የተከሰሱበት እያንዳንዱ ክሶች እውነት ከሆኑ ይጠይቅዎታል። ዳኛው ስለእርስዎ የቀረቡትን ክሶች በሙሉ እንዲነግርዎት ይጠይቁ። ጥያቄዎቹን በደምብ ያዳምጡ እና <u>ሙሉ በሙሉ እውነት ያልሆኑ ነጥቦች</u> ጋር መስማማት የለብዎትም። ለምሳሌ፡ ዳኛው ወደዚህ አገር የገቡት ሕገወጥ በሆነ መንገድ ጥር 1፡ 1997 ነው ወይ፡ ብሎ ከጠየቀ እና እርስዎ የገቡት ግን በ1998 ከሆነ፣ ክሱ ትክክል ነው ማለት የለብዎትም። የገቡበት ቀን በትክክል የማያውቁት ከሆነ፡ ይህንንም ለዳኛው ያሳውቁ። ይህ በጣም አስፈላጊ ነው፡ ምክንያቱም በኃላ ለጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት በሚያመክቱበት ጊዜ፡ የሚጽፉት ቀኖች አስቀድመው ካሉት ጋር አንድ ዓይነት መሆን ስላለበት። ወይም

ደግሞ ዳኛው ውሸት እንደተናገሩ ወይም ያልተፈጸመው ተፈጽመዋል እንዳሉ ብሎ ሊያስብ ይችላልና። በዳኛው የቀረቡ ጥያቄዎች ለአንዳንዱ መልስ ከሰጡ እና ከተሰማሙበት፡ እያንዳንዱ ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ አለብዎት።

> በዳኛው ከቀረቡ ጥያቄዎች ለአንዳንዱ መልስ ከሰጡ እና ከተሰማሙበት፡
> ☞ እያንዳንዱ ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ አለብዎት።

- **የጉዳዩ ሁለተኛ ክፍል፥**

በተለምዶ፡ የተከሰሱበት ክሶች እውነት መሆናቸውን ለማሳየት ለመንግስቱ ከባድ ነገር አይደለም። ከዛ በኃላ፡ ዳኛው እርስዎ በአሜሪካ አገር ሊቆዩ የሚችሉበት መንገድ ካለ ለማየት አንዳንድ ጥያቄዎች መጠየቅ ይጀምራል። ዳኛው ወደ አገርዎ እንዳይመለሱ የሚያስፈራዎት ነገር ካለ ይጠይቅዎታል። የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት፡ ወይም ስቃይን የሚቃወም የስምምነት ከለላ ለማግኘት ያመለከቱ ከሆነ፡ ይህንንም ለዳኛው ይግለጹነት። ዳኛው ወደ አገርዎ ከተመለሱ ለምን እንደሚፈሩ ሊጠይቅዎት ይችላል። ዳኛው ከእነዚህ የከለላዎች መብቶች አንዱ ለመግኘት ብቁ ነው ብሎ ከወሰነ፡ ማመልከቻ ማስገባት ያለብዎት ቀን መቼ እንደሚሆን ይነግርዎታል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ፡ ዳኛው ለጥገኝነት ፍቃድ ወይም አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ለመግኘት ብቁ መሆንዎ ወይም አለመሆንዎ ለመወሰን ሌላ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ያደርጋል። ማመልከቻዎ ወደ ፍርድ ቤት እንዴት ማቅረብ እንደሚገባዎት ዳኛው ማብራርያ ይሰጥዎታል እንዲሁም ደግሞ ይህንን የሚገልጽ የጽሑፍ ማብራርያ ከDHS ጠበቃ ይቀበላሉ። የDHS የጽሑፍ ማብራርያ እንዲህ የሚል ርእስ አለው፡ *አንዳንድ ማመልከቻዎች ወደ የኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት የማስገባት እና የባዮሜትሪክ እና የግል መረጃዎች ወደ የዩኤስ የዜግነት እና የሰደተኛ አገልግሎቶች የማቅረብ መመርያዎች (Instructions For Submitting Certain Applications In Immigration Court and For Providing Biometric and Biographical Information to U.S. Citizenship and Immigration Services)*።

የማመልከቻው ፎርም ሞልተው ከመለሱት በኃላ፡ ፍርድ ቤቱ ዋሽንግተን ወደሚገኘው የአሜሪካ ተባበሩት አገሮች ክፍል ቢሮ ይልከዋል። የስቴቱ ክፍል ደግሞ፡ ማመልከቻውን ካነበበው ሀኃላ፡ የራሱ የሆነ አስተያየት አያይዞ ወይም ደግሞ፡ የአገርዎ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለፍርድ ቤቱ መረጃ ይልካል። (በብዙ ጉዳዮች ላይ አስተያየት ከመስጠት ይታቀባሉ።) እርስዎ እና የDHS ጠበቃ የስቴት ክፍል ወደ ፍርድ ቤቱ የላከውን ግልባጭ ይቀበላሉ።

ከዛ በኃላ፡ የግለሰብ ወይም "Merits" ተብሎ የሚጠራ በፍርድ ቤት ቀጠሮ ላይ ጉዳይዎ እንዲሰማ ይደረጋል። ይህ ክፍል የጉዳይዎ የመጨረሻ ክፍል ሲሆን፡ ዳኛው የሚናገሩትን ታሪክ ይሰማል፤ እንዲሁም እርስዎ እና ምስክሮች ካልዎት ደግሞ ምስክሮቹን ይጠይቃል። ማመልከቻው እና ለዳኛው ያቀረቡት ሌላ ጽሑፎች ካሉም፡ በነዚህም ሁሉ ላይ ጥያቄ ይጠይቃል።

- **<u>የጥገኝነት ፍቃድ፡ አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ወይም የCAT ከለላ ለማግኘት፡ ሲያመለክት፡ ምን ዓይነት ፎርምና ፎርሙን እንዴት ሞምላት አለብኝ?</u>**

> ☞ **የጥገኝነት ፍቃድ ወይም አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ለማግኘት ሲያመለክቱ፡ የ"I-589" ፎርም ሞልተው፣ አባዝተው፣ ማመልከቻው ማስገባት አለብዎት።**

የሚያስፈልገው ፎርም "Form I-589" የሚባለው ወይም "የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል" ማመልከቻ ፎርም ይባላል።

ፎርሙ ታይፕ አድርገው ወይም በእስክርፒቶ ይሙሉ። ፎርሙን ለማግኘት DHSን ወይም የኢሚሬሽን ዳኛ ይጠይቁ።


**<u>እርሳስ ለመጻፍ አይጠቀሙ</u>። <u>በተጨማሪም ፎርሙን ራስዎ በእንግሊዛኛ ቋንቋ ሞምላት አለብዎት ወይም ደግሞ ሌላ</u>**

**እንግሊዘኛ ቋንቋ የሚችል እንዲያግዝዎት ይጠይቁ።**

የፎርሙ የመጨረሻ ገጽ በላይኛው ክፍል እንዲህ የሚል ጽሑፍ አለው፡ "Supplement B Form"። በዋናው ገጽ ያለው ቦታ ካነሰ ይህን ገጽ እንዲጠቀሙ ተብሎ ነው የተሰጠው። ጥያቄዎቹ በሙሉ እና በዝርዝር መመለስ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ስለሆነም በፎርሙ ላይ መጻፍ ከመጀምራቹ በፊት፡ ፎርሙን "Supplement B Form" የሚለውን ክፍል ቢያባዙት ጥሩ ነው። ወይም ደግሞ እንደዛ ዓይነት ፎርም ራስዎ መስራት ይችላሉ። በአንድ ባዶ ወረቀት ላይ የእርስዎ የ "A number" (alien number) እና እንዲሁም በላይኛው ክፍል ቀኑ ይጻፋበት። ከማመልከው ፎርም ጋር አያይዘው የሚልኩትን እያንዳንዱ ወረቀት ላይ መፈረም ይኖርብዎታል።

በፎርሙ የመጀመርያ ገጽ ላይ፡ ፎርሙን እንዴት ሞምላት እንዳለብዎት የሚገጽ ረጅም ማብራርያ አለ። እንዲህ ይላል፥ **በማመልከቻው የI-589 ፎርም ተጨማሪ፡ የእርስዎ ግላዊ መረጃ (በዲጂታል ካሜራ የተነሳ ፎቶግራፍ እና የጣት አሽራዎች) እንዱሁም ሌላ ፎቶግራፍ ለDHS መስጠት ይኖርብዎታል።** በእስር ቤት ውስጥ ካሉ፡ ይህን በተመለከተ እንዲያግዝዎት DHSን ይጠይቁ። ማመልከቻው ከማስገባትዎ በፊት ከእስር ቤት የወጡ እንደሆነ ወይም ደግሞ፡ በመመልከቻዎ ላይ የቤተሰብ አባሎችን ለማስገባት ከፈለጉ፡ ፎቶግራፍ እና የጣት አሽራዎች ያስፈልግዎታል፤ ስለዚህ ጉዳይ በኃላ በዝርዝር እንገልጻዋለን። ለDHS የሚሰጡት የባዮሜትሪክስ እና የጣት አሽራዎች በሙሉ መስጠት ይኖርብዎታል፤ ካልሆነ ግን፡ ይህንን ነገር ለምን እንዳላሟሉ በቂ የሆነ ምክንያት ከሌልዎት በስተቀር፡ የኢሚግሬሽን ዳኛው ጉዳይዎን ችላ በለው እንደተዉት ይቆጥረዋል።

**ወደ ፍርድ ቤት ለሚያቀርቡት ወረቀቶች በሙሉ አራት ቅጂ ያድርጉ (ወይም ባለስልጣኑ እንድያባዛው ይጠይቁ)። ለኢሚግሬሽን ዳኛው ኦሪጂናሉ እና 2 ቅጂ ይስጡት። ለዳኛው የሰጡትን በሙሉ 1 ቅጂ ለ ICE ይስጡት። የቀረው ቅጂ የእርስዎ ነው። ማሳሰብያ፥ የI-589 የማመልከቻ ፎርም ካልሆነ በስተቀር፡ ኦሪጅናሉ በሙሉ ከእርስዎ ጋር ያስቀምጡት፤ የኦሪጂናሎቹ እርስዎ ዘንድ ያስቀምጡ፡ ቅጂ ደግሞ ለዳኛው እና ለICE ይስጡ። ኦሪጂናል ዶኩመንት፡ እንደ የልደት ሰርቲፊኬት፣ ፓስፖርት የመሳሰሉት ለመንግስት ከሰጡ፡ ዶኩመንቶቹ መልሰው ያገኙዋቸው አይችሉም።**



አንዳንድ ጊዜ ለፍርድ ቤት የሰጡት ወይም የላኩት ዶኩመንት ሊጠፋ ስለሚችል፡ ምናልባት ዶኩመንቶቹን በተመለከተ ከተጠየቁ እንዲረዳዎት፡ ወደ ፍርድ ቤት በሚሄዱበት ጊዜ ሁሉ፡ የራስዎ ዶኩመንቶችን ይዘው ይሂዱ። በተጨማሪም፡ የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ለማግኘት የI-589 መመልከቻ ፎርም በሚያስገቡ ጊዜ፡ የእርስዎ ቅጂ ላይ ማህተም እንዲያደርጉለት ዳኛው ወይም ዳኛውን የሚተባበር ሰው መጠየቅ ይችላሉ! ምናልባት ከእስር ቤት ከወጡ እና የስራ ፍቃድ እንዲሰጥዎት ካመለከቱ ይህንን ጠቃሚ ይሆናል።

**የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ማመልከቻ (Form I-589)**

ለእርስዎ እንዲረዳ ብለን በፎርሙ ላይ ያሉትን አንዳንድ ጥያቄዎችን ማብራርያ እንሰጣለን። ከፎርሙ ጋር የሚመጣ መመርያ ደግሞ ማንበብ ይኖርብዎታል። አንዳንድ ጥያቄዎችን እንዴት መመለስ እንዳለብዎትም ማብራርያ ይሰጣሉ። በቅርቡ ጊዜ፡ ማለትም በ12/14/06፡ እንደገና የታተመውን ፎርም እንዴት ሞምላት እንደሚችሉ ማብራርያ እንሰጣለን (ፎርሙን የታተመበትን ቀን በፎርሙ በታች በቀኝ በኩል ተጽፎ ይገኛል)። የኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት ወይም ጉዳይዎ የሚሰማውን ፍርድ ቤት በኃላ የታተመ ፎርም ከተጠቀሙ፤ አሁን የምንገልጻቸው አንዳንድ ቁጥሮች እና ክፍሎች ከዛ ፎርም የተለዩ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ መግለጫ ለመመርያ ብቻ ይጠቀሙበት።

በመጀመርያ የማመልከቻ ገጽ ላይ፡ እንደዚህ የሚሉ ሁለት ሣጥኖች አሉ፥ "ለEOIR ብቻ የሚመለከት" እንዲሁም

"ለUSCIS ብቻ የሚመለከት"። በነዚህ ሣጥኖች ምንም ነገር መጻፍ የለብዎትም። ከዛ ሌላ እና ከክፍል E እና F ሌላ፡ በመጨረሻ፡ <u>ጥያቄዎቹን በሙሉ መመለስ አለብዎት</u>። ጥያቄው እርስዎን የማይመለከት ከሆነ ሣጥኑ ውስጥ፡ "N/A" ብሎው መጻፍ አለብዎት፤ ይህ ማለት "አይመለከተኝም" ማለት ነው። "ስቃይን የሚቃወም የስምምነት ከለላ ሕግ መሰረት፡ አገር ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል" መብት ለማግኘት የሚያመለክቱ ከሆነ፡ በመጀመርያ ገጽ ክፍል A. I. ላይ ያለው ሣጥን ውስጥ ምልክት ማድረግ እንዳለብዎት ያስተውሉ።

## ክፍል A. I: "እርስዎን የሚመለከት መረጃ"

አንዱ ጥያቄ ላይ፡ ከአሁን በፊት በሌላ መጠርያ ስም ይጠሩ ነበር ወይ፡ ብሎ ይጠይቃል። ግልጽ ሁኑ! ብዙ ሰዎች DHS እስር ቤት ሲያስገባቸው፡ የውሸት ስም ይጠቀማሉ። እርስዎ እንደዛ ያደረጉ ከሆነ፤ ለምን እንደዛ እንዳደረጉ በፎርሙ መጨረሻ ላይ መግለጽ ይችላሉ። በተጨማሪም፡ ካገቡ፡ ስምዎ ከቀየሩ፣ ወይም ደግሞ፡ የስምዎ ልዩ አጠራር ካለው በሙሉ ይጽፉት።

አንዱ ጥያቄ ላይ ደግሞ አድራሻዎ በአሜሪካ አገር ይጠይቃል። እስር ቤት ውስጥ ካሉ፡ የእስር ቤቱን አድራሻ መጻፍ ይችላሉ።

አንዱ ጥያቄ ደግሞ አግብተው ከሆኑ ይጠይቃል። (እንዲህ ይላል፡ "የጋብቻ ሁኔታ")። ብዙ ሰዎች ያላገቡ፡ ወይም በሕጋዊ መንገድ ያላገቡ ነገር ግን ለረጅም ጊዜ ከሌላ "ሰው ጋር አብረው" የኖሩ አሉ። በአንዳንድ ቦታዎች፤ ለተወሰነ ጊዜ እንደ ባል እና ሚስት አብረው ከኖሩ እንደተጋቡ ይቆጠራሉ። የዚህ ዓይነት ጋብቻ የ"common law" ተብሎ ይጠራል። እርስዎ እና ባለቤትዎ ወይም ሚስትዎ በሚሮሩበት አገር ሕጉ ምን እንደሚል ላያውቁ ይችላሉ፤ ነገር ግን ከሌላ "ሰው ጋር አብረው" የኖሩ ከሆነ እና "እንደ ተጋቡ" ሊቆጠር ይችላል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፡ "ያገባ" የሚለውን ሣጥን ላይ ምልክት ያድርጉ እና በአጠገቡ "common law" ብለው ይጻፉበት -- በተለይም የሚያስገቡት ማመልከቻ፡ ባለቤትዎ ወይም ሚስትዎ በአሜሪካ አገር ሕጋዊ የሆነ መኖርያ ለማግኘት ብለው የሚያስቡ ከሆነ። (የእርስዎ የጥገኝነት ፍቃድ በመጠቀም አብረው የሚኖር ሰው ለማስመጣት ከፈለጉ እና ያልተጋቡ ከሆነ፡ ዳኛው በእርስዎ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ <u>በፊት</u> መጋባት አለባችሁ።) ወይም ደግሞ፡ ከሌላ "ሰው ጋር አብረው" የሚኖሩ ከሆኑ ወይም ከነበሩ፡ ነገር ግን ያልተጋቡ ከሆኑ "ያላገባ" በሚለው ሣጥን ላይ ምልክት ሊያደርጉ ይችላሉ።

አንዱ ጥያቄ ስለ "ዘር፣ ጎሳ ወይም ብሄር" ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ ለእርስዎ ጉዳይ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፤ በተለይም የአንድ ጎሳ ወይም ብሄር አባል በመሆንዎ ግፍ የደረሰብዎት ከሆነ።

አንዱ ጥያቄ ጉዳይዎ በኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት ሂደት ላይ መሆኑን እና አለመሆኑን ይጠይቃል። የሚመከለትዎ ከሆነ ሣጥኑ ላይ ምልክት ያድርጉ።

አንዱ ጥያቄ ወደ አሜሪካ የገቡበት እያንዳንዱ ፖርት፡ መጨረሻ የገቡበትን በመጀመር በቅደም ተከለል እንዲጽፉት ይጠይቃል። ወደ አሜሪካ የገቡበት እያንዳንዱ ጊዜ ምን ዓይነት ፍቃድ ወይም ቪዛ እንደ ተጠቀሙ ደግሞ ይጠይቃል። በሕገወጥ መንገድ የገቡ ከሆነ "**No inspection**" በማለት ይሙሉት፤ እንዲሁም የ "I-94 ቁጥር" ሲጠየቁ "**None**" ብለው ይጻፉ። I-94 በሕጋዊ መንገድ ሲገቡ የሚቀበሉት ወረቀት ነው።

ፓስፖርት እና የጉዞ ወረቀት በተመለከተ አንዳንድ ጥያቄዎች አሉ። ከማንም አገር የጉዞ ፍቃድ ወረቀት ያልተቀበሉ ከሆነ፡ በእያንዳንዱ መልስ ላይ "**N/A**" (ማለት አይመለከተኝም) ብለው ይጻፉ።

## ክፍል A. II: "ባለቤትዎን እና ልጆችዎን የሚመለከት መረጃ"

በዚህ ክፍል የሚጠየቀው ጥያቄ ስለ ባለቤትዎ፣ ሚስትዎ፣ እና ልጆችዎ ነው። ስለ ልጆችዎ መረጃ በሙሉ መጻፍ ይኖርብዎታል፡ ነገር ግን በፎርሙ ላይ ለአራት ልጆች ብቻ የሚበቃ ቦታ ነው የተሰጠው። ከአራት በላይ ልጆች ካልዎት፡ በማመልከቻው መጨረሻ ላይ “Supplement A” የሚለውን ክፍል ሊሞሉ ይችላሉ ወይም ደግሞ ሌላ ባዶ ወረቀት መጠቀም ይችላሉ። ይህ በጣም አስፈላጊ ነው ምክንያቱም፡ ከልጆችዎ አንዱ ስሙን ሳይጽፉት ከቀሩ፡ የጥገኝነት ፍቃድ ከተሰጠዎት፡ ልጁን ወደ አሜሪካ ለማስመጣት አስቸጋሪ ይሆናል።

በባዶ ወረቀት ላይ ከጻፉ፡ ስምዎ፣ የ“A number” � ጥርዎ፣ ፊርማዎ፣ ቀን እና “ከ **I-589** የቀጠለ፡ ክፍል**A. II**" በሙሉ እዛ ላይ መጻፍዎን ያረጋግጡ። ከዛ በኃላ የጥያቄውን ቁጥር ልክ ከክፍል A.II እንደተወሰደ ይጻፉት።

ለባለቤትዎ ወይም ለሚስትዎ እና/ወይም ለልጆችዎ ጭምር ወደ አሜሪካ ለማስመጣት ከፈለጉ ሌላ ሞምላት ያለባችሁ ፎርም አለ (ፎቶግራፍ፣ ባዮሜትሪክስ (የጣት አሻራዎች)፣ የ I-589 ማመልከቻ ፎርም ተጨማሪ ቅጂ፡ እና ከነዚህ ሰዎች ጋር ያለብዎት መተሳሰር የሚገልጽ ማስረጃ)። ከDHS ጠበቃ የተቀበሉትን የማመልከቻ ፎርም ላይ ያለውን መመርያ በሙሉ በማንበብ በጥንቃቄ ይከተሉት።

## ክፍል A. III: “የህይወት ታሪክዎን የሚመለከት መረጃ"

ወደ አሜሪካ አገር ከመምጣትዎ በፊት የት እንደኖሩ የሚጠይቁ ጥያቄዎች አሉ፥ ያለፉት አምስት አመታት የት ይኖሩ እንደነበረ፣ የት እና መቼ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ፣ እንዲሁም ያለፉት አምስት አመታት ውስጥ ምን ዓይነት ስራ ይሰሩ እንደነበሩ። ለያንዳንዱ ጥያቄ መልስ ሲሰጡ፡ በመጀመርያ መስመር ላይ አሁን ያሉበትን ሁኔታ የሚገልጽ መልስ ይስጡ። በሌላ አባባል፡ በአሁኑ ጊዜ ይጀምሩ እና መበጨረሻም ከአምስት ዓመታት በፊት የነበረውን ሁኔታ በመጻፍ ይደምድሙ (የትምህርት ቤት በተመለከተ የመጀመርያ ትምህርት ቤትዎ የነበረው፡ መደምደምያ በማድረግ ይዝጉ)። በተጨማሪም፡ የማያስታውሱት ቀኖች፣ አድራሻዎች እና ሌሎች ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። በጣም እርግጠኛ ላልሆኑት ቀን "**በግምት**" ብለው ይምሉት፡ እንዲሁም ማስታወስ ላልቻሉትን ነገሮች (እንደ የጎዳና ስም ወይም አድራሻ) "**አላስታውሰውም**" በማለት ይምሉት። ወላጆችዎን፣ ወንድሞችዎን እና እህቶችዎን የሚመለከቱ ጥያቄዎችም አሉ። ተጨማሪ ቦታ ካስፈለግዎ፡ ተጨማሪ ወረቀት ላይ መጻፍ ይችላሉ (እላይ ይመለከቱ)።

� �.


## ክፍል B: “ማመልከቻዎን የሚመለከት መረጃ"

ክፍል B የማመልከቻው በጣም አስፈላጊ ክፍል ነው። ይህን ለመመለስ ረጅም ጊዜ-- ወይም ብዙ ቀኖች --ወስደው በጥንቃቄ መመለስ ይኖርብዎታል። ወደ አገርዎ ከተመለሱ እንደሚሰቃዩ ወይም ደግሞ ከአሁን በፊት ተሰቃይተው እንደነበረ በመግለጽ ዳኛውን ለማሳመን የሚችሉት በዚህ ክፍል ላይ ነው። ለምን ከአገርዎ እንደወጡ ወይም ደግሞ ወደ አገርዎ ለመመለስ ለምን እንደሚፈሩ በጥንቃቄ እና በዝርዝር ይግለጹት። ጥያቄው የጠየቀውን በሙሉ መመለስዎን ያረጋግጡ። በማመልከቻው ላይ በክፍል B ላይ ያሉት ጥያቄዎችን አንድ በአንድ ሊመልሱዋቸው ይችላሉ፡ ወይም ደግሞ፡ በክፍል B ያለውን በአንድ ላይ እንደ መግለጫ ዘርዝረው መጻፍ ይችላሉ። ተጨማሪ መግለጫ “Supplement B” በሚለው ላይ ወይም ደግሞ በሌላ ባዶ ወረቀት ላይ መጻፍ ይችላሉ።

ፎርሙ ላይ ወይም በባዶ ወረቀት ላይ ይጻፉ፡ ስምዎ፣ “የA ቁጥርዎ”፣ ቀን፣ እና ፊርማዎ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ መጻፍ እንዳለብዎት ያስታውሱ። በላይኛው ክፍል ደግሞ "**መግለጫ**" (**“Declaration”**) ብለው ይጻፉ።


በማመልከቻው ክፍል B ላይ ያሉት ጥያቄዎችን በሚመልሱበት ጊዜ፡ መግለጫ የሚለውን ክፍል ለብቻው ከለዩት፡ በዛ ላይ ትንሽ መልስ ከሰጡ በኃላ፡ "**እባክዎ መግለጫውን ይመለከቱ**" (“**Please see Declaration**”) ብለው መጻፍ ይችላሉ። በዚህ መንገድ፡ የጥያቄዎቹ መልስ በሙሉ በአንድ መግለጫ ሰጥተዋል ማለት ነው።

**መግለጫው**

የሚሰጡት መግለጫ ልክ እንደ የታሪክ መጽሐፍ ወይም ፊልም ሆኖ ስለ እርስዎ ታሪክ የሚናገር ነው። ልክ እንደ የታሪክ መጽሐፍ ወይም ፊልም፥ መጀመርያ በሆነ ሁኔታ ይጀምራል፤ ማለትም መቼ እና የት እንደተወለዱ በመግለጽ ይጀምራል። ከዛ በኃላ ታሪኩ ከአንድ የህይወትዎ አስፈላጊ ገጽታ ወደ ሌላ እየሄደ፥ ያሳለፉት ጊዜ እና በታሪክዎ ላይ ተራ ያላቸው ሰዎችም ይዘረዝራል።

በካሜራ እንደተቀረጸ ፊልም፥ ቶሎ ብለው የሚያልፉ የታሪኩ ክፍል ይኖራሉ። የነዚህ ነገሮች ሁኔታ በዝርዝር ለማየት አይቻልም፤ በሌላ በኩል ደግሞ ካሜራው ቀስ ብሎ ዝርዝር ነገሮችን ያሳያል። ካሜራው የሚያሳየው አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች ስለሆነ፥ እርስዎ ያዩትን እንድናይ ይረዳናል። ድርጊቶቹ ቀስ ብለው ያልፋሉ።

የሚጽፉት መግለጫ እንደዛ መሆን አለበት። ስለ ህይወትዎ በሙሉ መናገር መቻል አለብዎት፥ ነገር ግን አስፈላጊ የሆኑ በቻ በመምረጥ በጥንቃቄ እና በዝርዝር መግለጽ አለብዎት። ታሪክዎን የሚያነብ ዳኛ ስለታሪክዎ ከአሁን በፊት አያውቅም፥ ምናልባት ደግሞ ወደ አገርዎ ሄዶ አያውቅም ወይም ስለ አገርዎ የሚያውቀው በጣም ትንሽ ብቻ ወይም ምንም የማያውቅ ሊሆን ይችላል። የእርስዎ ስራ ዳኛው ለማስረዳት ነው። በይህወትዎ የተከሰተውን አስፈላጊ ሁኔታ በሚገልጹበት ጊዜ – ለምሳሌ፥ ያስፈራርዎት፣ የታሰሩበት፣ የተሰቃዩበት፣ የተጎዱበት፣ ጊዜ ሲገልጹ፥ – ዳኛው የሚከተሉት ስሜቶች እንዲሰማው ያደርገዋል፥

እርስዎ የተሰማዎትን፣ ያዩትን፣ ያሸተቱትን፣ እና የሰሙትን፥ እንዲያይ ፣ እንዲያሸተት፣  እና እንዲሰማ  ያደርገዋል።

ለምሳሌ፥ በተራራው የሚገኝ ትንሽ መንደር የኖሩ እና፥ በዛ መንደር ብዙ ጠብ አለ ብለን እናስብ። 

አንድ ቀን ማታ፥ ሰዎች በግሩፕ ሆነው መጡ። ወደ ቤቶቹ ገቡ እና  እዛ የነበሩትን ሰዎች በሙሉ እንዲወጡ ትእዛዝ አስተላለፉ። የመንደሩ ሰዎች እያጋፉ፥ ወንዶቹ ከእነርሱ ጋር ተቀላቅለው እንዲሄዱ ነገርዋቸው፤ አለበለዝያ ተመልሰው በመምጣት ሁላችሁም እንገድላቸዋለን ብለው አስፈራሩዋቸው።

በመግለጫዎ ላይ ይህን ሁኔታ ከመጻፍዎ በፊት፤ ይህ ሁሉ ችግር እንዴት እንደጀመረ ስለ መንደሩ መጻፍ አለብዎት። በጠቡ የተሳተፉ እነማን ናቸው? ምን ነበር ምክንያቱ? ይህ ነገር ከመሆኑ በፊት በእርስዎ መንደር ምን ተካሄደ? በእርስዎ ህይወትስ ምን ለውጥ አመጣ? በቤተሰቦችዎ ህይወትስ? ጎረቤቶችዎስ? የትኞቹ የቤተሰብ አባሎች እና እንዴት?

ስለተከሰተ ነገር በሚያወሩ ጊዜ፥ በዝርዝር እና በጥንቃቄ መግለጽ ይኖርብዎታል። መቼ እንደተፈጸመ?  በምን ሰዓት ላይ?

እነዚህ ሰዎች ሲመጡ፥ ምን እያደረግክ ነበር? ሰዎቹ ምን ዓይነት ልብስ ነበር የለበሱት? በቁጥር ስንት ሰዎች ነበሩ? ከዛ ጊዜ በፊት ያውቋቸው ነበር ወይ? መቼ እና የት? መሳርያ ነበራቸው ወይ?  ምን ዓይነት መሳርያ ነበር የታጠቁት? ምንድን ናቸው? ወታደሮች? ሽምቅ ተዋጊዎች? እንዴት አወቅህ? ምን ይመስላሉ? መጀመርያ ሲመጡ ምን አደረጉ? ምን ነበር ያሉት በትክክል? ምን አደረጉህ? ሰዎቹን ያጋፉስ እንዴት ነበር? አስፈራሩህ ወይ? ምን ዓይነት

ማስፈራራት ነው የተጠቀሙት? የነኩት ወይ፣ የተናገሩት ሰው ነበር ወይ? አንተ፣ ዘመዶችህ፣ ወይም ጎረቤቶችህ? እንዴት?

ያየሀውን በሙሉ፤ የተፈጸመውን በሙሉ፤ የተሰማህ ነገር በሙሉ ገልጸህ ጻፍ። ይህ ሁሉ ሲሆን ስንት ሰዓት ፈጀ? ከዛ በኃላስ ምን ሆነ? በአንተና በመንደሩ የሚነሩ ሰዎች ይህወት ላይ ምን ለውጥ አመጣ? ሰዎቹ እንደገና ተመልሰው መጥተው ከሆነ፡ እንደገና ምን እንደተፈጸመ በዝርዝር ግለጽ።

ይህ መግለጫ በሚጽፉበት ጊዜ ለምን የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ከለላ ማለት ምን ማለት እንደሆኑ ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። ዓላማቸው፡ ሰዎች በፖለቲካ አስተያየታቸው፣ ዘራቸው፣ የትውልድ አገራቸው፣ ሀይማኖታቸው፣ የአንድ ህብረተሰብ አባል በመሆናቸው የተነሳ አደጋ ላይ ያሉ ወይም አደጋ የደረሰባቸው ሰዎችን ለመከላከል ነው። ስለዚህ፡ አመጸኛው ማን እንደሆነ እና ለምን በእርስዎ ላይ እንዳመጸ መግለጽ በጣም ጠቃሚ ነው። አመጸኛው ያደረገው አመጽ እላይ የተዘረዘሩትን አምስት ምክንያቶች የተነሳ መሆኑን ለማሳየት በእንደዚህ መንገድ ይግለጹት፥

ለምሳሌ፡ መሳርያ የታጠቁ እና የወታደር ልብስ የለበሱ ሰዎች ከደበደብዎ፡ ስለ ፖለቲካ ጉዳይ በተመለከተ ሊሆን ይችላል። ሰዎቹ ዩኒፎርም እንደለበሱ ካልገለጹት ወይም ወታደሮች መሆናቸውን እንዴት እንዳወቁ ካልገለጹት፡ ዳኛው ወንጀል የሚፈጽሙ ዱርየዎች ናቸው እና ከፖለቲካ ጋር ምንም መተሳሰር የለውም ብሎ ሊያስብ ይችላል።

እርስዎ ያሉት ወይም ያደረጉት ነገር ካለ እና ስለ አመጸኞቹ የሰሙት ወይም ያዩት ነገር ካለ ደግሞ ስለዛ ነገር መግለጽ ይኖርብዎታል። ለምሳሌ፡ መግስትን የሚቋወም ብዱን ጋር የተሳተፉ ከሆነ፡ እርስዎ ምን ዓይነት እንቅስቃሴዎች ላይ እንደተሳተፉ መግለጽ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ ብዱን በመንግስት እንደ ተቋዋሚ ብዱን እንደሚላቸው መግለጽም አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም፤ እርስዎ ከብዱኑ ጋር መኖራቸውን መንግስት እንዳወቀ ወይም በቅርብ ማወቅ እንደሚችሉ፡ የሚያስረዱ ማስረጃዎች ማቅረብ ይኖርብዎታል። እነዚህ መረጃዎችን ካላቀረቡ፡ ዳኛው እርስዎ የሚፈሩት ስቃይ እላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች የሚነሳ አይደለም ብሎ ሊያስብ ስለሚችል፡ ጉዳይዎን ሊሽነፉ ይችላሉ።

መንግስቱ ወይም ሌላ የአንድ ቡድን አባል በመሆንዎ ሊጎዳዎት የሚፈልግ ከሆነ፡ እዛ ቡድን ውስጥ ብዙ ስራ ባይሰሩም፡ አባል የሆኑበት ማንኛውም ቡድን መጥቀስ አለብዎት።

### *የተለመዱ ችግሮች*

**> አገሩን ለቀው የወጡበት ጊዜ እና በደሉ ወይም ስቃዩን በተፈጸመበት ጊዜ መካከል ረጅም የጊዜ ልዩነት አለ <**

አገሩን ለቀው እንዲወጡ ያደረገው ምክንያት የተፈጸመውና አገሩን ሲለቁ አንድ አመት የሆነው ከሆነ። ሁኔታው ከተከሰተ በኃላ ለአንድ ዓመት ያህል የቆዩ ከሆነ፡ ዳኛው፡ እርስዎ በዛ አገር ውስጥ ለመኖር እንዳልፈሩ እና አሁን ቢመለሱ ደግሞ ምንም ችግር ኣይፈጥርም ብሎ ሊያምን ይችላል። በዛ ዓመት ውስጥ ምን እያደረጉ እንደነበሩ መግለስ ይኖርብዎታል። ለምሳሌ፡ በዛን ጊዜ ከቤትዎ ወጥተው በሌላ ተደብቀው ከኖሩ፣ ለጉዞ የሚሆን ገንዘብ እያሰባሰቡ ከኖሩ፣ በሚገልጹበት ጊዜ አደጋ ላይ እንደነበሩ ዳኛውን ማሳመን ይችላሉ።

**> ወደ አገርዎ መመለስ <**

በችግር የተነሳ ከአገርዎ ሸሽተው ከወጡ በኃላ እንደገና አገርዎ ደርሰው ከመጡ፡ ዳኛው ወደ አገርዎ ተመልሰው ሄደው እዛ ቢቀመጡ ምንም ችግር እንደሌለት ያምናል። ወደ አገርዎ በተመለሱበት ጊዜ ምን እንዳደረጉ እና በዛን ጊዜ ምን አደጋ እንደ ደረሰብዎት በዝርዝር ማስረዳት መቻል አለብዎት። ይህን ጉዳይ አስመልክቶ የቀረበ ጥያቄ በፎርሙ ውስጥ ይገኛል።

**> የቤተሰብዎ አባሎች ወይም በዛ አገር የሚኖሩ ሌሎች ሰዎች<**

የአንድ ህብረተሰብ አባል በመሆንዎ ስቃይ ሊደርስብኝ ይችላል ካሉ፡ የቤተሰብዎ አባሎች ደግሞ ከዛ ህብረተሰብ ከሆኑ፡ ነገር ግን አገሩን ለቀው ካልወጡ፡ ዳኛው፡ እርስዎ ከተመለሱም ምንም ችግር አይኖርም ብሎ ሊታመን ይችላል። እንዲሁም በአንድ የፖለቲካ ማህበር የተሳተፉ ከሆነ እና ሌሎች በዛ ማህበር የተሳተፉ ሰዎች አገሩን ለቀው ያልወጡ ከሆነ ዳኛው የሚያስበው እንደዛ ይሆናል። ነገር ግን እነርሱም ችግር ላይ ካሉ፡ የእነርሱ ችግር በመግለጫዎ መግለጽ ያስፈልጋል። ወይም ደግሞ፡ የእርስዎ ሁኔታ ከእነርሱ የተለየ ከሆነ፡ ለምን እዛ ከሚኖሩ ሰዎች እርስዎ በበለጠ ችግር እንደነበሩ ማስረዳት መቻል አለብዎት።

**> በዝርዝር ያልቀረበ <**

ፍርድ ቤት ውስጥ የእውነት ነጥቦች በጣም አስፈላጊ ናቸው። አንድ አስፈላጊ ነገር ተፈጸመ ብለው ካሉ እና መቼ እንደተፈጸመ፣ ምን ያህል እንደቆየ፣ ወይም ሌላ ዝርዝር መረጃዎችን ማስታወስ ካልቻሉ፡ ዳኛው ውሸት እንደሆነ ያስባል። በመግለጫው ላይ እና በፍርድ ቤት ውስጥ በሚናገሩበት ጊዜ፡ ዝርዝር መረጃ ካቀረቡ ዳኛው እንዲያምንዎት የበለጠ ዕድል ያገኛሉ። በትክክል ማስታወስ ካልቻሉ፡ አንዳንድ ነገሮች በትክክል ለማስታወስ እንደሚያስቸግርዎት ዳኛውን ይንገሩት እና፡ ቀኑን <u>በግምት</u> ይስጡ።

ብዙ ሰዎች፡ ስሜታቸውን የሚነካ ሁኔታ አንስተው ለመናገር አይወዱም። የሚወዱት ሰው ሲሞት በአይናቸው ያዩ ከሆነ፣ ወይም ደግሞ በጣም ተሰቃይተው ወይም ጾታዊ ግፍ የደርሰባቸው ከሆነ፡ ስለነዚህ ነገሮች ላለመናገር ከመረጡ የተለመደ ነገር ነው። ነገር ግን የጥገኝነት ጉዳይዎን ለማሸነፍ ከፈለጉ፡ መናገር በጣም አስፈላጊ ነው። የተከሰተውን ነገር በሙሉ እና ያዩትን ነገር በሙሉ መንገር መቻል አለብዎት። ማጋነን የለብዎትም። በዝርዝር ኢና እውነቱን ብቻ መናገር ይኖርብዎታል።

**> በሰጡት መረጃ ላይ የተለያዩ እና የማይስማሙ ነጥቦች ካሉ <**

ፎርሙ ላይ የሞሉትን መረጃ በሙሉ ትክክል መሆኑን ለማየት፡ ዳኛው እና DHS ፎርሙን እና መግለጫውን ደግመው ያነቡታል። ለምሳሌ፡ በማመልከቻው ፎርም ላይ እስከ መስከረም 1997 ድረስ በሁንድራስ ይሰሩ እንደነበረ ከጻፉ፡ ነገር ግን በፍርድ ቤት ወደ አመሪካ የገቡበት ቀን ነሐሴ 1997 ነው ካሉ (ወደ ሁንድራስ ተመልሰው አልሄዱም)፡ ዳኛው ውሸት እየተናገረ ነው ብሎ ያስባል። ምክንያቱም እነዚህ ነጥቦች እርስ በርሳቸው አይስማሙም (በሌላ አባባል ሁለቱም እውነት ሊሆኑ አይችሉም)። በመስከረም 1997 በሁንድራስ እና በአሜሪካ አገር ሊቆዩ አይችሉም። በተጨማሪ፡ መግለጫው ላይ ጥቅምት ላይ 4 ሰዎች በሰማያዊ የጭነት መኪና ወደ መኖርያ ቤትዎ እንደመጡ ከገለጹ፡ ነገር ግን በፍርድ ቤት ቀጥሮ ጊዜ፡ በታህሳስ 5 ሰዎች በግራጫ የጭነት መኪና እንደመጡ ካሉ፡ ዳኛው እየዋሹ እንደሁኑ ሊያስብ ይችላል።

በትክክል ማስታወስ የማይችሉ ከሆነ፡ እንደዛ ብለው ይናገሩ፡ እና ለምን ለማስታወስ ከባድ እንደሆነ ያስረዱ። (ለምሳሌ፡ በጣም ረጅም ጊዜ ስለሆነ፣ ወይም ፈርተው ስለነበር ነገሮችን በደምብ ለማጤን አልቻሉም፤ ወይም ደግሞ ምን እንደሆነ በደምብ ማየት ወይም መስማት ስላልቻሉ)።

በፎርሙ እና በመግለጫው ላይ ብዙ መረጃ መስጠት አስፈላጊ ቢሆንም፡ በጣም ትክክል ያልሆኑበት መረጃ ግን <u>ባይገልጹት</u> የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል። አንድ ነገር ሰኔ ወይም ሐምሌ ላይ እንደተፈጸመ በትክክል ማስታወስ ካልቻሉ፤ ነገር ግን ጊዜው ክረምት እንደነገር የሚያስታውሱ ከሆነ፡ በክረምት ወቅት ላይ እንደተፈጸመ ብለው መጻፍ ይችላሉ። የሚኖሩበት ከነበረው መንደር ወደ ዋና ከተማ ስንት ኪሎሜትር መሆኑን የማያውቁ ከሆነ ነገር ግን የአንድ ቀን ሙሉ በእግር መሆኑን ካወቁ፡ እንደዛ ብለው ይጻፉ። ከ 4 እስከ 6 ሰዎች ከነበሩ፡ 5 ብለው መጻፍ የለብዎትም፡ ከ4 እስከ 6 ሰዎች ብለው ይጻፉ። በ1991 ዓ.ም አንድ ነገር እንደተፈጸመ ካሰቡ፡ ነገር ግን 1991 ዓ.ም ሊሆን ይችላል ብለው ካመኑ፡ 1991 ወይም 1992 ብለው ይምሉት። ቀኑ በግምት እየጻፈ ከሆነ ደግሞ በፎሙም ላይ ቢሆን "በግምት" ብለው ይጻፉ። በተጨማሪ፡ በመግለጫው ላይ የሞሉን ማንኛውም እውነት፡ በፍርድ ቤት ከሚሉት ጋር አንድ ዓይነት እንደሚሆን ማረጋገጥ ይኖርብዎታል።

እንደ ባህል ሆኖ ብዙ ሰዎች የሚሰጡት ምክንያት በተመለከተ ችግር አለው። በአሜሪካ የሚኖሩ ሰዎች የተከሰቱ ነገሮች በቅደም ተከተል መልክ ያስቀምጣሉ። በእርስዎ ባህል ግን ይህ ዓይነት ቅደም ተከተል አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። ነገር

ግን ጉዳይዎ የሚገልጹት በአሜሪካ ለሚኖረው ዳኛ ስለሆነ፡ ልክ እንደ እርሱ ወይም እርሷ ለማሰብ መሞከር አለብዎት። ስለዚህም፡ ሁሉም ነገር ግልጽ ለማድረግ ይሞክሩ። ምንም እንኳ አንድ ነገር የተከሰተበት ቀን ለማስታወስ ባይችሉም፡ ነገሩ የተከሰተው ከምን በፊት ወይም በኋላ መሆኑን ለማስታወስ ይሞክሩ፤ ስለዚህም የተፈጸሙት ነገሮች እንደ ቅደም ተከተላቸው ይተርኩት። በመግለጫዎ ውስጥ ለመጻፍ የፈለጉትን ነገሮች ምን ቅደም ተከተል መያዝ እንዳለባቸው እንዲያግዝዎት፡ የክስተቶች ዝርዝር ለራስዎ መያዝ ይችላሉ። ለምሳሌ፥ 1) የተወለድኩበት በ1962 ዓ.ም ነው፤ 2) ቤተሰቦቼ ወደ ሳን ማርኮስ ሄዱ፤ 3) በሳንታ ሉችያ ከተማ የሰዎች እልቂት ነበረ፡ ወዘተ።

## > በማስተርጎም ጊዜ የሚደረጉ ስህተቶች <

ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ በሚተረጎምበት ጊዜ በቀላሉ ስህተት ሊከሰት ይችላል። አንድ ሰው የጻፉት መግለጫ ወደ እንግሊዘኛ የተረጎመው ከሆነ፡ የተረጎመው ሰው በራስዎ ቋንቋ ቀስ ብሎ እንዲያነብልዎት ይጠይቁት። ስለዚህም ስህተት እንዳልተደረገ ማረጋገጥ ይችላሉ። በማመልከቻው ፎርም እና በማግለጫው ላይ የተጻፈውን መረጃ በሙሉ እንደተደረገ በጥንቃቄ ማንበብ አስፈላጊ ነው።

## በክፍል B የሚገኙ አንዳንድ ጥያቄዎች

አስቀድመን እንዳሳሰብነው፡ ረጅም መግለጫ ለመስጠት ከፈለጉ፤ በእያንዳንዱ በክፍል B ያሉት ጥያቄዎች መጨረሻ ላይ **"እባክዎ መግለጫውን ይመለከቱ"** ብለው መጻፍ እንዳለብዎት ያስታውሱ። መርሳት የለብዎትም።

**ጥያቄ 1፡** ለምን ለጥገኝነት እንደሚያመለክቱ ይጠይቃል። ጉዳይዎን የሚመለከተው በአንዱ ወይም ከዛ በላይ ሣጥኖች ላይ ምልክት ያድርጉ (ዘር፣ ሀይማኖት፣ ወዘተ)፤ ከአንድ በላይ ምክንያት ሎሆን ይችላልና። ለምሳሌ፡ በዘርዎ እና በአንድ የህብረተሰብ ክፍል አባል በመሆንዎ እንዲሁም በፖለቲካ አስተያየትዎ የተነሳ ሊሰቃዩ ይችላሉ።

በጥያቄዎች 1.A. እና 1.B፡ ከአገርዎ ለምን ሸሽተው እንደመጡ እና ወደ አገርዎ ለመመለስ ለምን እንደሚፈሩ ምክንያት ይስጡ። ብዙ ሰዎች የሚያደርጉት ስህተት ወደ አሜሪካ የመጡበት ስራ ለመስራት እና ኖሮአቸው ለማሻሻል ነው ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ለመቀላቀል ኢንደመጡ ይናገራሉ። የጥገኝነት ፍቃድ መስጠት ዓላማ፡ መስራት የሚፈልጉ ድሆችን ለመከላከል ወይም ደግሞ ቤተሰቦችን ለመቀላቀል እንዳልሆነ ማስታወስ ይኖርብዎታል። ዓላማው እላይ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች አንዱ በተነሳ ለሚሰቃዩ ሰዎችን ከለላ ለምስጠት ነው። ስለዚህ እውነት መናገር ቢኖርብዎት እንኳ፡ ወደ አሜሪካ የመጡበትን እያንዳንዱ ምክንያት መግለጽ አስፈላጊ አይደለም፤ እንዳይመለሱ የሚፈሩበት ምክንያት እላይ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች አንዱ መሰረት በማድረግ እንዳይሰቃዩ ስለሚፈሩ መሆን አለበት። በ CAT ሕግ መሰረት ከለላ ለማግኘት እያመለከቱ ከሆነ ደግሞ፡ ወደ አገርዎ ከተመለሱ እንዳይሰቃዩ የሚፈሩት ለምንድነው የሚለውን ጥያቄ መመለስ አለብዎት።

**ጥያቄ I. A፡** ቤተሰቦችዎ፣ ጓደኞችዎ፣ ወይም የስራ ባልደረቦችዎ ላይ የደረሰ ጉዳት ወይም ግፍ አለ ወይ የሚል ጥያቄ ይጠይቃል። ለዚህ መልስዎ፡ "አይደለም" ከሆነ፡ እርስዎ ከለላ አያስፈልግዎትም ሊባል ይችላል፤ እና ባለፈው ጊዜ ግፍ ወይም ጉዳት ካልደረሰብዎ ለምን ለወደፊቱ ሊደርስብዎ እንደሚችል ማብራራት አለብዎት። "አዎን" የሚል መልስ ከሰጡ፡ ጥያቄው በመመለስ ምን እንደተፈጸመ በዝርዝር መግለጽ አለብዎት።

**ጥያቄ 1. B፡** ለወደፊቱ ወደ አገርዎ ከተመለሱ ስቃይ ወይም ጉዳይ እንዳይደርስብዎት ይፈራሉ ወይ ብሎ ይጠይቃል። "አዎን" የሚል መልስ ከሰጡ፡ የጥያቄው መልስ ለመስጥት በዝርዝር መግለጽ ይኖርብዎታል። በትክክል ምንድነው የሚፈሩት? ይህን ማሰብ አለብዎት። በመንግስት ወይም በሌላ ቡድን በግድ ተወስደው እርስ ቤት እንዳይጣሉ ነው ወይ የሚፈሩት? እንዳይሰቃዩ ነው ወይ የሚፈሩት? እንዳይገደሉ ነው ወይ የሚፈሩት? እነዚህ ነገሮች በሙሉ እንዳይደርስብዎት ነው ወይ የሚፈሩት? ምን ይሆናል ብለው የሚያስቡትን ወይም የሚያምኑትን ይናገሩ። ለምን እንደዛ ሊፈጸም ይችላል ብለው እንደሚያስቡ ደግሞ ይግለጹት። በሌሎች ሰዎች ላይ ተፈጽመዋል ወይ? እነርሱ እና እርስዎ በምን ይመሳሰላሉ?

**ጥያቄ 2፡** ከአሜሪካ አገር ውጭ፡ እርስዎ ወይም ከቤተሰቦችዎ አባል "ተከሰው፣ ወንጀለኛ ተብለው፣ ታስረው፣ በቁጥጥር ስር ገብተው፣ ተመርምረው" ወዘተ ያውቃሉ ወይ ብሎ ይጠይቃል። በሌላ አባባል በመንግስት ባለስልጣኖች ተጠይቀው ወይም ታስረይ ያውቃሉ ወይ? በመንግስቱ ወይም ሌላ ሰው ከፍላጎትዎ ውጭ በሆነ መንገድ ታፍነው ወይም ወደ ሌላ ቦታ በግድ ተወስደው ያውቃሉ ወይ? በባለስልጣኖች ወይም በሌላ ሰው ተመርምረው ያውቃሉ ወይ? ለዚህ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ፡ የደርሰው ጉዳት ወይም በወንጀል ምክንያት በአገርዎ ወይም ሌላ አገር የተፈጸመውን በሙሉ መግለጽ ይኖርብዎታል። የስቃይ መከራ በተመለከተ፡ እስር ቤት ውስጥ እንዴት እንደተያዙ ለመግለጽ ፎርሙ የሚጠይቀው ጥያቄ በሙሉ መመለስ ይኖርብዎታል።

**ጥያቄ 3፡** በአገርዎ እርስዎ ወይም ቤተሰቦችዎ፡ ከማንኛውም ዓይነት ማህበር ወይም ቡድን አባልነት ወይም ግንኙነት አባል ነበሩ ወይ ብሎ ይጠይቃል። ይህን ጥያቄ ከመመለስዎ በፊት የእርስዎ እና የቤተሰቦችዎ እንቅስቃሴዎች በጥንቃቄ በማሰብ፡ ለአደጋ ምክንያት የሆነው የትኛው መሆኑን ያስታውሱ። የተጠየቀውን ጥያቄ በሙሉ ይመልሱ፡ ለምሳሌ የቡዱኑ ስም፣ እርስዎ ወይም ቤተሰቦችዎ አባል የሆኑበት ቀን፣ የእርስዎ ወይም የቤተሰቦችዎ ስራ ወይም እንቅስቃሴ ምን እንደነበር ወዘተ። እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ እስካሁን የማህበሩ ወይም የቡድኑ አባል መሆንዎን ወይም አለመሆንዎን የሚጠይቅ በ3. B. የተጠቀሰውን መረጃ እዚህ ላይ ማካተት አለብዎት።

**ጥያቄ 4፡** በአገርዎ ወይም ማንኛውም ሌላ አገር ስቃይ ይፈራሉ ወይ የሚል ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ አስፈላጊ ጥያቄ ነው። አሰቃቂ የሆነ የአካል ወይም የአእምሮ ስቃይ ሊደርስብኝ ይችላል ብሎ የሚያስቡ ከሆነ፡ አዎ የሚለውን መልስ መስጠይ አለብዎት። ጥያቄው አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም በአንዳንድ ምክንያት የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ለማግኘት ብቁ ካልሆኑ፡ በ CAT ስር የሚሰጥ የከለላ ፍቃድ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ምን ሊደርስብዎት እንደሚችል እና ለምን እንደሆነ በዝርዝር መግለጽ ይኖርብዎታል። በተጨማሪም፡ ከአሁን በፊት ተሰቃይተው የሚያውቁ ከሆነ፡ እዚህ ላይ መጻፍ ይኖርብዎታል። ከአሁን በፊት ምን እንደሆነ በጥያቄ 1 ላይ፡ ቢገልጹትም፡ እዚህ ላይ ደግሞ ኢንደገና መግለጽ አለብዎት። ወይም ደግሞ የተጻፈውን እንደገና ከመጻፍ "ጥያቄ 1 ይመለከቱ" ብለው መጻፍ ይችላሉ።

### ክፍል C: "ማመልከቻዎ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ"

**ጥያቄ C. 1፡** እርስዎ፣ ባለቤትዎ ወይም ሚስትዎ፣ ልጆችዎ፣ ቤተሰቦችዎ፣ ወንድሞችዎ፣ ወይም እህቶችዎ ከአሁን በፊት፡ የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ለማግኘት ወደ አሜሪካ መንግስት አመልክተው ያውቃሉ ወይ ብሎ ይጠይቃል። በእናትዎ፣ አባትዎ፣ ባለቤትዎ ወይም ሚስትዎ ባመለከቱት ማመልከቻ ላይ የእርስዎ ስም ማስገባታቸውን እርግጠኛ ካልሆኑ፡ ሣጥኑ ላይ ምልክት ማድረግ የለብዎትም። ነገር ግን "እርግጠኛ አይደለሁም" ብለው ይጻፉ እና፡ በሌላ ተጨማሪ ወረቀት ላይ፡ ስለሁኔታው የሚያውቁትን ነገር ብቻ ይጻፉ።

**ጥያቄ C. 2፡** ከአገርዎ ወጥተው ወደ አሜሪካ ሲመጡ፡ እርስዎ፣ ባለቤትዎ ወይም ሚስትዎ ወይም ልጆችዎ፣ በምን አገሮች እንዳለፉ ይጠይቃል። በተጨማሪም እርስዎ ወይም ቤተሰቦችዎ፡ በእነዛ አገሮች ሕጋዊ የሆነ ፍቃድ እንዲሰጣቸው አመልክተው ነበር ወይ፡ ብሎም ይጠይቃል። ከአገርዎ ካለው ስቃይ ሸሽተው ወደ አሜሪካ መምጣት የፈለጉበት ምክንያት፡ እዚህ ከለላ ስለሚያገኙ እና ደግሞ ብዙ የስራ ዕድል ስላለ ከሆነ፡ ችግር ላያመጣ ይችላል። በግልጽ ይናገሩ። ወደዚህ ለመምጣት ያለፍባቸው አገሮች ውስጥ ያጋጠምዎት ማንኛውም ዓይነት ችግር ካለ ይግለጹት። ለምሳሌ፡ እንዳይባረሩ በመፍራት ከባለስልጣኖች ይደበቁ ከነበረ፡ ወይም በካምፕ ቁጥጥር ስር ይኖሩ ከነበረ፡ በሙሉ ይግለጹት።

**ጥያቄ C. 5፡** ይህ ጥያቄ የሚጠይቀው፡ ወደ አሜሪካ ከመጡ አንድ ዓመት ካለፈ በኃላ ለምን አሁን ለማመልከት እንደሚችሉ እንዲገልጹ ነው። ከዚህ በፊት እንደገለጽነው ከአንድ ዓመት ጊዜ በኃላ ማመልከት እንዲችሉ፡ "አስፈላጊ ለውጦች" ወይም "ከቁጥጥር በላይ የሆነ ሁኔታ" ማሳየት አለብዎት። ይህን ለማድረግ ካልቻሉ ደግሞ፡ አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ለመግኘት ማመልከት ይችላሉ።

**ጥያቄ C. 6፡** በአሜሪካ አገር የፈጸሙት ማንኛውም ዓይነት ወንጀል ካለ ይግለጹት (ወይም ደግሞ በማመልከቻዎ ላይ ስሙ የተጻፈውን የቤተሰብ አባል ያደረገው ወንጀል ካለ)። እስራት ወይም ክስ በሙሉ መጻፍ ኣለብዎት። ካልጻፉት ግን ይህን

መረጃ ከDHS ጋር ሊኖር ስለሚችል፡ በፍርድ ቤት ቀጠሮ ጊዜ ስለዚህ ጉዳይ ይጠየቃሉ። እነዚህን ነገሮች በማመልካቻው ላይ ካልጻፉት፡ ዳኛው፡ አንዳንድ ነገሮችን ለመደበቅ እየሞከሩ ነው ብሎ ሊያስብ ይችላል። እነዚህ ክሶች አስመልክቶ ንጹህ እንኳ ቢሆኑ፡ እያንዳንዱ እስራት ወይም የተከሰሱበትን ወንጀል መጻፍ ይኖርብዎታል። በተጨማሪም በአሜርካ አገር በ DHS ታስረው እንደነበር ወይም እስካሁን እንደታሰሩ መግለጽ ይኖርብዎታል።

**ክፍል E**

የI-589 ፎርም በሞምላት፡ ወይም ወደ እንግሊዘኛ ቋንቋ በማስተርጎም ከሌላ ሰው እገዛ ያገኙ ከሆነ፡ ያ ሰው በዚህ ክፍል ላይ መፈረም፣ አድራሻው እና ስልክ ቁጥሩ መጻፍ ይኖርበታል። ይህ ሰው እንደእርስዎ እስር ቤት ውስጥ ያለ ቢሆንም፡ እሱ ወይም እሷ ክፍል E ሞምላት አለበት ወይም አለባት። በተጨማሪም ማመልከቻዎ ላይ ከመፈረምዎ በፊት፡ ያገዘው ሰውየ ማመልከቻውን በሙሉ (መግለጫ የሰጡ ከሆነ ደግሞ፤ እሱም ጭምር) ለእርስዎ <u>በቋንቋዎ</u> (የመጀመርያ ወይም የእናት ቋንቋ) ማንበብ እንዳለበት ፍሮሙ ይገልጻል። የእርስዎ ቋንቋ እና እንግሊዘኛ ቋንቋ የሚናገር ሰው ላያገኙ ይችላሉ። ይህን ፎርም ለሞምላት፡ ሌላ ሰው እርስዎ በሚያውቁት ሌላ ቋንቋ በመጠቀም የረዳ ከሆነ፡ "በራሱ ወይም በራስዋ ቋንቋ" እንደተጠቀመ ይጻፍ፡ እንዲሁም የተጠቀበመትን ቋንቋ ስም ምን እንደሚባል ይጻፍ። ይህ የሚሆንበት ምክንያት፡ አስተርጓሚው ልስዎን በሚያስተገሩምበት ጊዜ፡ ስህተት ያደረገ እንደሆነ ለማወቅ ስለሚረዳ ነው።

**ክፍል F**

<u>የፍርድ ቤት ቀጠሮ እስከሚደርስ ድረስ በዚህ ክፍል ላይ መፈረም የለብዎትም።</u>

**ሌሎች ወረቀቶች**

ፎርሙ በሞምላት እና በፍርድ ቤት ቀጠሮ ጊዜ ደግሞ ስለ ጉዳይዎ ለዳኛ መንገር ብቻ፡ ጉዳይዎ እንዲያሸንፉ ብዙ ላይረዳ ይችላል። ከተቻለ፡ ጉዳይዎን የሚደግፉ ሌሎች ወረቀቶችን ወይም ምስክሮችን ማቅረብ አለብዎት። ብዙ ጊዜ በጣም አሳማኝ የሚሆነው አዋቂ ከተባለ ገለሰብ ምስክርነት ሲያገኙ ነው። አዋቂ የሚባል ሰው እንዲመሰክር ለማግኘት ካልቻሉ፡ ቢስያን የሚደግፉት ዶኩመንቶችን ማቅረብ ይኖርብዎታል። ለምሳሌ፡ ከቤተሰብ አባሎች የተላኩ ደብዳቤቶች፤ ወይም ስለ እርስዎ ሁኔታ የሚያውቁ ሌሎች ሰዎች፣ በጋዜጣ የተጻፉ ጽሑፎች፣ በሰብአዊ መብት ማህበሮች የተሰጡ ዘገባዎች፣ ፎርቶግራፎች፣ ወይም ሌሎች በአገራቹ ስላለ ሁኔታ ወይም ስለእርስዎ፣ ስለማህበርዎ፣ ስለቤተሰብዎ ወይም ስለሌላ አስፈላጊ እና ከጉዳይዎ ጋር የተያያዘ የሚናገሩ። ከማመልከቻው ፎርም በስተቀር፡ ሌላ ዶኩመንት ካላስገቡ፡ በI-589 ፎርም Supplement B ላይ፡ ለምን ተጨማሪ ዶኩመንት እንዳላስገቡ ያብራሩ። ጉዳይዎን የሚደግፍ ሌላ ተጨማሪ ዶኩመንት ከሌለ ጉዳይዎን ተቀባይነት ላያገኝ ይችላል።

**ከቻሉ፡ ጉዳይዎን የሚደግፉ ሌሎች ዶኩመንቶችን እና ደብዳቤዎችን ያቅርቡ።**


እዚህ ላይ ዳኛውን ከሰጡት በጣም ጠቃሚ የሆኑ የዶኩመንቶችን ምሳሌ ተዘዝረዋል። ለምሳሌ፡ አገርዎን ለቀው እንዲወጡ ያደረገዎት አንዱ ምክንያት፡ መንግስቱን ከሚቃወሙ ብዱኖች የማስፈራርያ ደብዳቤ ስለተቀበሉ ከሆነ። ብዙ ጊዜ ይህንን ዓይነት ደብዳቤ ከእርስዎ ጋር ላይኖር ይችላል፤ ነገር ግን ደብዳቤው ካገኙት ከማመልከቻው ጋር አያይዘው ማስገባት ይኖርብዎታል። ።

በተጨማሪም፡ የቤተሰብዎ አባሎች ከእርስዎ ጋር ኣብረው ያልሸሹ ከሆነ፡ አሁን እዛ ምን እንደተፈጸመ መሆኑን መንገር ይችላሉ። ለምሳሌ፡ እርስዎ አገርን ለቀው ከወጡ በኃላ፡ ምን እንደተፈጸመ ወደ ቤተሰቦችዎ ወይም ጓደኞችዎ ደብዳቤ መበላክ መጠየቅ ይችላሉ። እነዚህ ደብዳቤዎች ጉዳይዎን የሚደግፉ ማስረጃዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

በተጨማሪም፡ የአንድ ማህበር አባል መሆንዎን የሚያሳይ ማስረጃ ካለ፡ ሸሽተው የወጡበት ምክንያት ደግሞ የዛ ማህበር አባል በመሆንዎ ከሆነ፡ ይህ ማስረጃ ወደ ፍርድ ቤት መምጣት በጣም ጠቃሚ ይሆናል። ለምሳሌ፡ በሀይማነትዎ ምክንያት እንዳይሰቃዩ የሞፈሩ ከሆነ፡ እና የልደት ሰርቲፊኬትዎ ደግሞ የምን ሀይማኖት ተከታይ መሆንዎን የሚያሳይ ከሆነ፡ ወይም ደግሞ የወላጆችዎ ስም የምን ሀይማኖት ተከታይ መሆንዎን የሚያሳይ ከሆነ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። የስምዎ ትርጉም ምን እንደሆነ ለመግለጽ የሚችል፡ ሀይማኖትዎን የሚከተል ሌላ ሰው ማምጣት ይችላሉ። የመንግስት ወታደር ከነበሩ እና

ወታደር በመሆንዎ እንዳይሰቃዩ የሚፈሩ ከሆነ፡ በውትድርና ያገለገሉበትን ማስረጃ ለማምጣት ይሞክሩ። የአንድ ጎሳ አባል በመሆንዎ እንዳይሰቃዩ የሚፈሩ ከሆነ፡ የዛ ጎሳ አባል መሆንዎን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያቅርቡ። እንደዚህ ዓይነት ማረጋጫዎች ለማቅረብ የማይችሉ ከሆነ፡ ለምን እንደማይችሉ ለማብራራት ዝግጁ ይሁኑ። እንደዚህ ዓይነት ማስረጃዎች ለፍርድ ቤቱ በጣም አስፈላጊ ነው።

በተጨማሪም፡ ከጉዳይዎ የሚያያዝ በጋዜጣ እና በመጽሄት የተጻፉ ጽሑፎችን፣ ወይም ደግሞ ከሰብአዊ መብቶች ማህበር የተገኘ ዘገባ ለማምጣት የምችሉ ከሆነ፡ ከማመልከቻዎ አያይዘው ማስገባት አለብዎት። ጽሑፎች እና ዘገባዎች፡ በትውልድ አገርዎ ያለው ሰላለው ፖለቲካ ሁኔታ፣ በአንድ ዓይነት ማህበር ያሉት ሰዎች የሚያጋጥማቸው ችግር የመሳሰሉ፡ ከጉዳይዎ ጋር የተያያዘ አስፈላጊ ወሬ የያዙ ሊሆኑ ይችላሉ።




ጽሑፎቹ ስለ እርስዎ እና በእርስዎ ዓይነት ሁኔታ የሚገኙ ሰዎች የሚናገር ከሆነ፡ ለጉዳይዎ በጣም አስፈላጊ ይሆናሉ።

## የከለላ ጥያቄዎን በተመለከተ ዶኩመንቶችን ማሰባሰብ

ለጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቀ ላለመውጣት የመከላከል መብት፡ ወይም ደግሞ የCAT ከለላ ለማግኘት ያስገቡትን ጥያቄ ለመደገፍ ዶኩመንቶችን በማቅረብ፡ ጉዳይዎን ለማሸነፍ ረገድ በጣም ይጠቅማል። ወደ ትውልድ አገርዎ ከተመለሱ ችግር ላይ እንደሚወድቁ ዳኛውን ማሳመን ይኖርብዎታል። የጥገኝነት መብት ማሸነፍ የሚችሉ፡ በዘርዎ፣ ሀይማኖትዎ፣ ትውልድ አገርዎ፣ የፖለቲካ አስተያየትዎ፣ ወይም የአንድ ህብረተሰብ ክፍል አባል በመሆንዎ ስቃይ ወይም ፍራቻ እንደሚደርስብዎት ዳኛው ማሳመን ከቻሉ ነው። **ስለዚህ ያቀረቡትን ጥያቄ የሚደግፉ ዶኩመንቶችን ማሰባሰብ አስፈላጊ ነው። ክዊመንቶችን።**

ጉዳይዎ የሚደግፉ ዶኩመንቶችን ሲያቀርቡ፡ ከአሁን በፊት ምን እንደተከሰተ ወይም አሁን ምን እየተከሰተ መሆኑን እውነቱን ለመግለጽ ይጠቅማል። ያቀረቡትን ጥያቄ ለመደገፍ የሚረዱ ዶኩመንቶች ዝርዝር ይከተላል፥

- ህጋዊ/የመንግስት ዶኩመንቶች (የልደት/የሞት ሰርቲፊኬቶች፣ የትምህርት ወይም የግብር ሪከርድ)
- የግል ዶኩመንቶች (የድጋፍ ደብዳቤ፣ የመመረቅያ ደብዳቤዎች፣ ሽልማቶች፣ ከቤተሰብ ወይም ከጓደኞች የሚላኩ ደብዳቤዎች፣ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያዎች፣ የሕክምና ሪፖርቶች፣ ወዘተ)
- የአገሩ ሁኔታ በተመለከተ ከአዋቂዎች ወይም ምሁራን የተገኘ ማረጋገጫ፣ የባህል ሁኔታዎች፣ ወይም ደግሞ ልዩ የሆነ የሰብአዊ መብት ጉዳዮችና ሪፖርቶች
- ስለ የአገሪቱ ሁኔታዎች ወይም የሰብአዊ መብት መጣስ አስመልክቶ በጋዜጣ የወጡ ጽሁፎች
- የሬድዮ ወይም የቲቪ ጽሑፎች
- መጻሕፍቶች
- ከመንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተገኙ የሰብአዊ መብት ዘገባዎች (ለምሳሌ፡ ከአምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ የተባበሩ መንግስታት፣ የሰብአዊ መብቶች ዋች፣ ዩኤስ የስቴት ክፍል፣ ወዘተ)

<u>ያቀረቡትን ማመልከቻ ለመደገፍ የሚጠቅሙ ዶኩመንቶችን ለመሰባሰብ የሚረዱ ብዙ መንገዶች አሉ።</u>

ጠበቃ ከሌለዎት፡ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ነገሮችን ማድረግ አለብዎት፥

1. ደኩመንቱን በሙሉ በጥንቃቄ ያንብቡ። የእርስዎ ጉዳይ የሚደግፍ ክፍል ብቻ ያቅርቡ። ከአሁን በፊት እርስዎ ካሉት ጋር የማይስማማ ማስረጃ እንዳይሰጡ ይጠንቀቁ። በሌላ አባባል፡ ለኢሚግሬሽን ዳኛ ከሚነግሩት ነገር ጋር የሚስማማ ማስረጃ ብቻ ማቅረብ ይኖርብዎታል። የተናገሩትን ነገር እውነት መሆኑን በማስረጃ ማሳየት እንዳለብዎት ያስታውሱ።
2. የእርስዎ የጥገኝነት ጥያቄ የሚደግፈውን ክፍል ለይተው፡ ያስምሩበት፣ ምልክት ያድርጉበት፣ ወይም ልዩ ቀለም ያርዱበት። ጉዳይዎን የሚደግፍ ማስረጃ ለማሰባሰብ የሚቻል ነገር ሁሉ ያድርጉ።
3. ቀጥሎ የተዘረዘሩትን የማህበሮች ስም ዝርዝር በደምብ ያንብቡ። ለእርስዎ ጉዳይ የሚጠቅመውን ማህበር ይምረጡ። የደኩመንት መጠየቅያ ፎርም ግልባጭ ይምሉ። እባክዎን፡ በፎርም ላይ የተጠየቀውን በሙሉ መሙላት እንዳለብዎት ያስታውሱ።

## ዶኩመንቶችን የመሰባሰብ መንገዶች

በትውልድ አገርዎ ስላለው ሁኔታ በተመለከተ ዶኩመንቶችን ለመሰባሰብ የሚረዱ ብዙመንገዶች አሉ። ነገር ግን፡ ይህ አጭር ጽሑፍ መጨረሻ እስከታተመበት ጊዜ ድረስ ላይ (ሰኔ 2007) አገርዎ ስላለው ሁኔታ እውነቶችን በማሰባሰብ በነጻ ምርምር የሚያደርጉ ማህበሮች የሉም።

አንድ፤ ለምርምሩ የሚከፍሉት ገንዘብ ካለዎት፡ እታች ከተዘረዘሩት ማህበሮች አንዱ ሊረዳዎት ይችላል (በሚቀጥለው ገጽ ላይ ዝርዝር አድራሻ ይመለከቱ)፥

**የመረጃ ማእከል (The Data Center)**
**የፖለቲካ ጥገኝነት ምርምር እና የዶኩመንቶችን ማሰባሰብ አገልግሎት (Political Asylum Research and Documentation Service) (PARDS)**

ሁለት፥ እርስዎ ወይም ቤተሰቦችዎ በቀላሉ ኢንተርነት ላይ ማየት የሚችሉ ከሆነ፡ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ዌብሳይቶች ስለ አገርዎ መረጃ ይሰጣሉ፥

አለምአቀፋዊ የአምንስቲ ማህበር (**Amnesty International**): http://www.amnesty.org
የሰብአዊ መብቶች ማስከበር (**Human Rights Watch**): http://www.hrw.org
የጥገኝነት ሕግ ማግበር (**AsylumLaw.org**): http://www.asylumlaw.org: ይህ ዌብሳይት፤ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች፡ በየሰብአዊ መብቶች የዶኩመንቶችን መለዋወጥ (Human Rights Documentation Exchange (HRDE)) የመሳሰሉት የተገኙ ዝርዝር የሆኑ መረጃዎች የያዘ ነው።
የዩኤስ ስቴት ክፍል (**U.S. Department of State**): http://www.state.gov

**የDHS የመረጃ ምንጭ ማእከል (DHS Resource Information Center):**
http://www.uscis.gov/graphics/services/asylum/ric/index.htm

***ሶስት፥ በአገርዎ ውስጥ ያለው ሁኔታ የሚገልጹ ጽሑፎችን ለመግዛት ቀጥሎ የተዘረዘሩት ማህበሮችን ደውለው ማነጋገር ይችላሉ፥***

**የስደተኞች ፕሮግራም (The Refugee Program, AIUSA)**
600 Pennsylvania Avenue, SE, 5th Floor
**ዋሽንግተን፡ ዲሲ.** 20003
**ስ.ቁጥር፡** 202-544-0200 x540
**ፋክስ፡** 202-546-7142
**ኢ.መይል፡** refugee@aiusa.org

**የሰብአዊ መብቶች ማስከበር (Human Rights Watch)**
350 Fifth Avenue, 34th floor
**ኒው ዮርክ፡** NY 10118-3299 USA
**ስ.ቁጥር፡** 1-(212) 290-4700
**ፋክስ፡** 1-(212) 736-1300
**ኢ.መይል፡** hrwnyc@hrw.org

***ነገር ግን፡ እነዚህ ጽሑፎችን እንዲላክልዎት ከጠይቁ የሚከፈል ክፍያ እንዳለ እንዲሁም እስከሚያገኙት ድረስ ጊዜ የሚወስድ መሆኑን ማወቅ ይኖርብዎታል። በጊዜው እንዲደርስ እና ደኩመቶቹን በተፈለገው ጊዜ ወደ ዳኛ እንዲደርሱ፡ ከአሁኑ መጥየቅ ይኖርብዎታል። ደኩመንት እንዲላክልዎት በሚጠይቁ ጊዜ፡ ምን ያህል የጊዜ ገደብ እንዳለብዎት መግለጽ ይኖርብዎታል። ይህ የጊዜ ገደብ ደግሞ፡ ደኩመንቶቹን በሙሉ ወደ የኢሚግሬሽን ዳኛ የሚያቀርቡት ጊዜ ይሆናል።***

***አራት፥ የሚፈልጉት መረጃ በአገርዎ ያለውን፡ በተለይም ስለ ጾታዊ ባህርይ፣ የጾታ ማንነት፣ ወይም የ*HIV *ሁኔታ ከሆነ፡ አገርዎ ያለው ሁኔታ በተመለከተ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ማህበሮች ደኩመንቶች ማግኘት ይችላሉ፤ ይህም በርካሽ ዋጋ ወይም በነጻ ሊሆን ይችላል (አድራሻዎቹ በሚቀጥለው ገጽ ላይ፡ ይገኛሉ)፥***

**አለምአቀፋዊ የግብረሰዶም ተከታዮች መብት ኮምሽን (International Gay & Lesbian Human Rights Commission) (IGLHRC)**
**አህጉራዊ የጥገኝነት የጾታዊ ባህርይ ማህበር (The National Asylum Partnership for Sexual Orientation) (NAPSO)**

## ማህበሮች

***እባክዎ፡ ቀጥሎ ያለውን ዝርዝር መረጃ፡ በጥንቃቄ ያንብቡና፡ የእርስዎ ጉዳይ የያዘ ማህበር ብቻ ምረጡ። እነዚህ ማህበሮች ለሚያቀርቡት፡ የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት፡ እንዲሁም የ*CAT *ከለላ ጥያቄ የሚሆን ደኩመንቶችን በመሰባሰብ ላይ እርዳታ የሚሰጡ ናቸው። እነዚህ ማህበሮች፡ ሕጋዊ የሆነ ምክር መስጠት አይችሉም፡ እንዲሁም በፍርድ ቤት ቀጠሮ ጊዜ እርስዎን ወክለው መቅረብ አይችሉም። ነገር ግን፡ ከነዚህ ማህበሮች አብዛኞቹ፡ እርስዎን ለመርዳት የሚችሉ የሕግ አማካሪዎች/ጠበቃዎች ስም ዝርዝር ይሰጣሉ።***

| ***ማህበር፥*** | ***መግለጫ፥*** |
|---|---|

| | |
|---|---|
| **የአምንስቲ ማህበረሰብ (Amnesty International) (AI)**<br>**የስደተኞች ፐሮግራም፡**<br>AIUSA<br>600 Pennsylvania Avenue, SE, 5th Floor<br>**ዋሽንግተን ዲሲ** 20003<br>Ph: 202-544-0200 x540<br>**ፋ**: 202-546-7142<br>**ኢ.መይል** refugee@aiusa.org<br>**ግረገጽ፡**<br>http://www.amnestyusa.org/refugee/ | **አገልግሎቶች፥** በዌብሳይታቸን የሚገኙ፡ ከ1996 ጀምሮ፡ በየዓመቱ የሚቀርቡ ዘገባዎች እና ዶኩመንቶች። እስር ቤት ውስጥ የሚገኙ የመጻህፍት ቤቶች፡ የአሁኑ ዓመት ዘገባ መያዝ አለባቸው። እዛ ካልተገኘ ግን፡ ፕሮግራማችን፡ ኢንተርነት ማየት ለሚችሉ እስረኞች፡ የዓመቱ አስፈላጊውን ዘገባ መላክ ይችላል። ፕሮግራማችን፡ የአንዳንድ በAI የተመረመሩ በኢንተርነት የማይገኙ ጽሑፎች ቅጂ መላክ ይችላል፡ እንዲሁም በተቻለ መጠን ምርምር ያደርጋል። በእያንዳንዱ አገሮች ስላለው ሁኔታን እና ክስተትን መረጃዎች፣ ወይም ማረጋገጫዎች ማቅረብ የሚችሉ፡ በፍቃደኝነት የሚሰሩ፡ የሰዎች ኔትዎክ አለን። በአንዳንድ የተወሰኑ ጉዳዮች ላይ፡ የምርመራ ውጤት ደብዳቤ ማዘጋጀት እንችላለን።<br>**ክፍያ፥** የሚከፈል ክፍያ የለም።<br>**መረጃን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል፥** በኢመይል መልክ ቢልኩልን ይመረጣል። እስር ቤት ውስጥ ያሉት ሰዎች ደግሞ በፖስጣ ወይም ፋክስ በማድረግ ጥያቄያቸው መላክ ይችላሉ። እባክዎን የአሊየን ቁጥርዎ፣ የትውልድ አገርዎ፣ አድራሻዎ፣ የጉዳይዎ ሂደት ሁኔታ፣ እንዲሁም ቀጥሎ ያለው የቃለ መጠይቅ ወይም የፍርድ ቤት ቀጠሮ ቀን ይጻፉልን። ከተቻለ፡ የጻፉት መግለጫ በሙሉ ቅጂ በመላክ፤ የትኞቹ ነጥቦች ለማረጋገጥ እንደሚፈልጉ የሚገልጽ ማብራርያ ይላኩልን። |
| **የዳታ ማእከል (The Data Center)**<br>1904 Franklin St., Suite 900<br>**ኦክላንድ፡** CA 94612-2912<br>**ስ.ቁጥር፡** 1-800-735-3741<br>**ፋክስ፡** (510) 835-3017<br>www.datacenter.org | **አገልግሎቶች፥** የመረጃ ማእከል የሚባለው ማህበር፡ በዓለም ስላሉ አገሮች በሙሉ፡ ስለ የሰብአዊ መብት ሁኔታ መረጃ ለማቅረብ፡ ከተለያዩ ጽሑፎች ማስረጃ ያሰባስባል። በአንዳንድ የሰብአዊ መብት ማህበሮች የታተሙ መጽሐፍቶችን እና ዘገባዎች በጥንቃቄ በመምረጥ፡ ተጨማሪ መረጃዎችን ያቀርባል።<br>**ክፍያ፥** የጉልበት፣ ዶኩመንቶችን ማባዛት፣ የተጠየቀውን አገልግሎት መሰረት በማድረግ የመላክያ ወጪ፣ እንዲሁም በኢንተርነት ለሚሰጡ ክፍያዎች በሰዓት ያስከፍላል። አብዛኛው ጊዜ አንድ የመረጃ አገልግሎት ለመስጠት $300.00-$500.00 ይሆናል። አስቀድሞው የሚከፍሉት ክፍያ ተፈላጊው ክፍያ በሙሉ ይሆናል፤ ይህም በቼክ፣ ቪዛ፣ ማስተር ካርድ መክፈል ይቻላል። ይህ የመጨረሻ ዋጋ ይሆናል።<br>**መረጃን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል፥** የፈለጉትን መረጃ በተመለከተ፡ ጠበቃዎ ወይም ቤተሰቦችዎ ሊደውሉ ወይም ኢመይል ሊልኩ ይችላሉ።<br>**ስልክ በተዘዋዋሪ መደወል አይፈቀድም።** |

| | |
|---|---|
| **አለምአቀፋዊ የግብረሰዶም ተከታዮች መብት ኮምሽን (International Gay & Lesbian Human Rights Commission) (IGLHRC)**<br>**የጥገኝነት መመዝገብያ ፕሮግራም**<br>P.O. Box 550<br>**ሳን ፍራንችስኮ፡** CA 94104<br>**ስ.ቁጥር፡** (415) 398-2759<br>**ፋክስ፡** (415) 398-4635<br>**ኢ.መይል፡** asylum@iglhrc.org | **አገልግሎቶች፥** የጥገኝነት ዶኩመንቶች ማሰባሰብ ፕሮግራም IGLHRC፡ በተለይም ስለ ጾታዊ ባህርይ፣ የጾታ ማንነት፣ ወይም የHIV ሁኔታ በተመለከተ ስቃይን ፈርተው ጥገኝነት የጠየቁ ሰዎች የሚደግፍ ነው። የተለያዩ አገሮች ሁኔታዎች፡ ስለ የግብረሶዶም ተከታዮች፡ እንዲሁም የHIV/AIDS በሽታ ያለባቸው ሰዎች የሚያሳልፉት ስቃይ እና ግፍ አስመልክቶ ከሰብአዊ መብት ማህበሮች የተገኘ መረጃ እናቀርባለን። እነዚህ መረጃዎች፡ ለጥገኝነት ጠያቂዎች፣ ጠበቃዎች፣ የኢሚግሬሽን ተካራካሪዎች፣ እንዲሁም ሌሎች አካሎች እንሰጣለን። ሕጋዊ ምክር አንሰጥም፡ ነገር ግን የኢሚግሬሽን ጠበቃዎች ስም ዝርዝር ማቅረብ እንችላለን። እባክዎን፡ በhttp://www.iglhrc.org የሚገኘውን የጥገኝነት ዶኩመንቶች ማሰባሰብ ፎርም በሞምላት፡ ይደውሉልን ወይም በኢመይል፣ በፋክስ ወይም በፖስታ ይላኩልን። ይህ መረጃ ለመላክ ከ2-3 ሳምንታት ጊዜ መጠበቅ አለብዎት። የዶኩመንቱ ዋጋ ለመክፈል የማይችሉ ከሆነ፡ በነጻ የሚያገኙበት መንገድ አለ።<br>**ስልክ በተዘዋዋሪ መደወል አይፈቀድም።** |

| | |
|---|---|
| **አህጉራዊ የጥገኝነት የጾታዊ ባህርይ ማህበር (The National Asylum Partnership for Sexual Orientation) (NAPSO)**<br>208 S. LaSalle, Suite 1818<br>**ሽካጎ፡** IL 60604<br>**ስ.ቁጥር፡** (312) 660-1370<br>**ፋክስ፡** (312) 660-1505<br>**የስራ ሰዓቶች፡ ሮብ** 9:00 - **ቀትር** 12፡00<br>**ቋንቋዎች፡ እንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ ፈረንሳይኛ እና አረብኛ። ለሎች ቋንቋዎች ሲጠይቁ ይገኛሉ** | **አገልግሎቶች፥ በጾታዊ ባህርያ ወይም የ**HIV **በሽታ መሰረት የፍርድ ቤት ጉዳይ ላለባቸው ሰዎች የሚወክሉትን ጠበቃዎች የ**NAPSO **ሰራተኖች የቴክኒክ እርዳታ ይሰጣሉ። እንዲሁም ደግሞ የጥገኝነት ጉዳይ ላለባቸው ሰዎች፡ ሕጋዊ የምክር አገልግሎቶች የሚሰጡ እና እንዲሁም የጠበቃዎች ስም ዝርዝር መስጠት እንችላለን። በመካከለኛው ምዕራብ ክልል የታሰሩት ጠበቃ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ብቻ በተመለከተ፡ እታች በተጻፈው አድራሻ ሊደውልልን ወይም ሊጽፉልን ይችላሉ። "የጥገኝነት ድል ማግኘት፣ መከላከል፣ እና በጾታዊ ባህርይ የተመሰረተ የ**CAT **ከለላ፣ የጾታ መተላለፍ ማንነት እንዲሁም/ወይም የ**HIV **በሽታ ያለባቸው ሰዎች ሁኔታ" የሚለውን ጽሁፍ በ** www.MIHRC.org **ይገኛል።**<br>**መረጃን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል፥ እባክዎን፡ ስልክ በመደውል፣ ፋክስ ወይም ኢመይል በማድረግ ያነጋግሩን።** |

| | |
|---|---|
| **የፖለቲካ ጥገኝነት ጥናት እና መዝገብ (Political Asylum Research and Documentation Service) (PARDS)**<br>145 Witherspoon Street<br>Princeton, NJ 08542<br>**ስ.ቁጥር፡** (609) 497-7663<br>**(በተዘዋዋሪ መደወል አይፈቀድም፤ ብዙ ቋንቋዎች መናገር የሚችሉ ሰራተኖች አሉን)** | **አገልግሎቶች፥ የጥገኝነት ጠያቂዎችን እና፡ ጠበቃዎቻቸውን፡ የሚገልጽ ዶኩመቶች እንሰጣለን እንዲሁም፡ ስለ አገሮችንና ልዩ የሆኑ ጉዳዮችን መረጃ ለማየት ወይም ማመልከቻዎችን ለመርመር እንዲችሉ እንረዳለን።**<br><br>**ማመልከቻዎች ከመግባታቸው በፊት ለመመርመር እንዲችሉ እንረዳለን። በአንዳንድ ሁኔታዎች፡ ከአማልካቹ ጋር ቃለመጠይቅ በማድረግ በጥሩ አሳማኝ ምክንያት ላይ የተመሰረተ ጉዳይ እንዲሆን እንረዳለን። ዶኩመንቶቹን በአገር ውጭ ካሉት መንግስታት ማረጋገጫ እንዲያገኙ እንረዳለን።**<br>**ክፍያ፥** PARDS **ነጻ የሆነ አገልግሎት የሚሰጥ ማህበር ነው። የተጠየቀው የአገልግሎቱ ዓይነትና ለዛ የሚያፈልገው ጊዜ መሰረት ክፍያ ይኖራል። አብዛኖቹ፡ ሁሉም ሳይሆን፡ ተማራማሪዎች፡ ያስከፍላሉ። በ** DHS **ቁጥጥር ስር ያሉና ጥበቃ ለሌላቸው ሰዎች፡ ቅናሽ ዋጋ ያገኛሉ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ፡ ለአንዳንድ ግለሰቦች ማካካሻ ተብሎ በነጻ ይሰጣል።** |

| | |
|---|---|
| | መረጃን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል፥ እባክዎን ፎርሙን በሞምላት ቀጥሎ ከተዘረዘሩትን ነገሮች ጋር በማያያዝ ይላኩልን (1) የ I-589 ፎርም ቅጂ (ለጥገኝነት ጥያቂዎች የሚመለከት) እንዲሁም የጥገኝነት ጥያቄዎን ምን ላይ እንደተመሰረተ የሚያሳይ የጻፉት መግለጫ (2) የጉዳይዎ ሂደት የት እንደደረሰ የሚያሳይ መረጃ፣ (3) የሚቀጥለው የቃለመጠይቅ ወይም የፍርድ ቤት ቀጠሮዎን ቀኑ መቼ እንደሆነ የሚገልጽ፣ እንዲሁም (4) ምን አገልግሎቶች እንደሚፈልጉ። እባክዎን ቅጂ እንጂ ኦሪጂናል እንዳይልኩ። የሚያቀርቡት ጥያቄ በሙሉ በእንግሊዘኛ ቋንቋ፣ በጥቁር ቀለም እስክርፒቶ በጥንቃቄ የተጻፈ መሆን አለበት። እባክዎ፣ ጥያቄዎ እና ክፍያው በተመለከተ ከኛ ጋር ለመነጋገር የሚችል ሰው፣ ስም እና፣ ስልክ ቁጥር ይስጡን። **ማሳሰብያ፣ እባክዎን ወደ PARDS የሚደውሉ ሰዎች፣ በኢንግሊዘኛ ቋንቋ በደምብ መነጋገር የሚችሉ መሆቻቸውን ያረጋግጡ። |

**እባክዎን ያስተውሉ፣ ማንኛውም የሚልኩት የጥገኝነት ማመልከቻ (I-589)፣ ደብዳቤዎች ወይም ፎርም ጉዳይዎን ለመደገፍ የሚረዱ ለውስጥ ጉዳይ ብቻ የሚጠቅሙ ናቸው። እርስዎ ፍቃድ ካልሰጡ በስተቀር፣ ይህ መረጃ፣ ለሌላ ማንኛውም ዓይነት ማህበር፣ DHS ወይም ሌላ ማንኛውም የመግስት ኤጀንሲ**

እላይ ከተዘረዘሩትን ማህበሮች፣ አንዱ ጋር ለመነጋገር ከፈለጉ፣ በዚህ አጭር ጽሑፍ መጨረሻ ገጽ ላይ ያለውን፣ ዶኩመንቶች መጠየቅያ ፎርም ይጠቀሙ።

## ወደ ፍርድ ቤቱ የሚቀርቡ ደብዳቤዎች

ወደ ፍርድ ቤት ያስገቡት እያንዳንዱ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ያልተጻፈ ዶኩመንቶችን፣ በእንግሊዘኛ ተተርጉመው መቅረብ አለብዎት። የተረጎመውን ጽሑፍ መጨረሻ ላይ፣ አስተርጓሚው እንደሚከተለው መጻፍ ይኖርበታል፥

እኔ፣ (የአስተርጓሚው ስም)፣ ይህን ዶኩመንት ለመተርጎም ብቃት ያለኝ እንደሆንኩን እና በተቻለኝ መጠን ዶኩመንቱን በእውነት እና በትክክል እንደተተረጎመ አረጋግጣለሁኝ።

(የአስተርጉሚ ፊርማ)/ (ቀን)

**አንድ ዶኩመንት ወይም ደብዳቤ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተጻፈ ካልሆነ፣ የእንግሊዘኛ ትርጉም ከዛ ጋር አያይዘው ይላኩ!**

በአገርዎ ምን እንደተፈጸመ ወይም ደግሞ ተመልሰው ከሄዱ ምን እንደሚፈጸም በደምብ ከሚያውቁ ጓደኞችዎ ወይም የቤተሰብዎ አባሎች፣ ደብዳቤዎች ለማግኘት ከቻሉ፣ እያንዳንዱ ደብዳቤ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ነገሮች ያካተት መሆን አለበት፥

### ወደ ዳኛ የሚቀርቡ ደብዳቤዎች ምን ዓይነት ደምብ እንደሚከተሉ

1. ለ "የተከበሩ የኢሚግሬሽን ዳኛ" ብለው የተጻፈ መሆን አለበት።
2. የጻፈው ሰው፣ ስሙ፣ አድራሻው፣ ስራው፣ ዕድሜው፣ የስደተኛ ፍቃድ፣ እንዲሁም ከእርስዎ ጋር ያለው ግንኙነት (ለምሳሌ፣ ወንድም፣ የእኅት ልጅ፣ ጎረቤት፣ አለቃ) መግለጽ ይኖርበታል።
3. ደብዳቤ የጻፈው ሰው የራሱ የሆነ ቃላት መጠቀም አለበት።

4. ከተቻለ፡ ደብዳቤው የማረጋገጫ ማህተም ያለበት ይሁን።
5. ደብዳቤው በእንግሊዘኛ ቋንቋ ያልተጻፈ ከሆነ፡ የእንግሊዘኛ ትርጉም እና፡ የአስተርጓሚው ሰርቲፊኬት ከዛ ጋር በመያያዝ ማቅረብ አለበት (ልክ አላይ እንደተገለጸው አንድ ዓይነት ቃላት ይጠቀሙ)።

## የስም ዝርዝር

ከማመልከቻዎ ጋር ደብዳቤዎች፣ የመጽሔት ጽሑፎች ወይም ሌሎች ዶኩመንቶችን አያይዘው ካስገቡ፤ የእነዚህ ዶኩመንቶችን ስም ዝርዝር ማድረግ ይኖርብዎታል። ይህ ዝርዝር "የስም ዝርዝር" ("index) ተብሎ የሚጥራ ሲሆን፤ ዳኛው የትኞቹ ዶኩመንቶች እንደቀረቡ እና እንዲሁም የትኞቹ እንደቀሩ ለማየት ይረዳዋል። በዝርዝሩ ላይኛው ክፍል ላይ፡ ስምዎ፣ “የA ቁጥርዎ፣” እንዲሁም "የጥገኝነት ማመልከቻ የሚደግፉ ዶኩመንቶችን ስም ዝርዝር" ብለው ይጻፉበት።

## የአገልግሎት ሰርቲፊኬት

ከተቻለ፡ የማመልከቻ ፎርሙን በሚያስገቡበት ጊዜ፡ ደብዳቤዎቹ፣ ጽሑፎቹ፣ እና ሌሎች ወረቀቶችን አንድ ላይ አድርገው፣ ማስገባት ይኖርብዎታል። ካልቻሉ ግን፡ በኃላ እንዲያስገቡት ዕድል ይሰጥዎታል (ነገር ግን ከፍርድ ቤት ቀጥሮ <u>በፊት</u> መሆን አለበት)። ስለዚህም፡ ወረቀቶቹ፡ ለዳኛው ወይም ለ DHS ጥበቃ በአካል ከመስጠት ይልቅ፡ በፖስጣ ሊልኩት ይችላሉ። እንደዚህ ከሆነ፡ ለ DHS አንድ ቅጂ እንደላኩ የሚገልጽ ደብዳቤ ወደ ዳኛው መላክ ይኖርብዎታል። ያኛው ደብዳቤ "የአገልግሎት ሰርቲፊኬት" ተብሎ ይጠራል፤ በዚህ አጭር ጽሑፍ መጨረሻ ገጽ ላይ ይገኛል። ሲሞሉት፡ ስምዎ፣ “የA ቁጥርዎ፣” እና ዶኩመንቱን የሚልኩበት ቀን መጻፍ ይኖርብዎታል። ከዛ በኃላ፡ የእርስዎ ጉዳይ የሚከታተል የDHS ጽሕፈት ቤት አድራሻ ይጻፉበት። አድራሻው የማያውቁት ከሆነ፡ ባለስልጣኑን ይጠይቁ። የአገልግሎት ሰርቲፊኬቱ ላይ በመፈረም፡ አራት ቅጂዎች ያድርጉ።

<u>ኦሪጂናል የአገልግሎት ሰርቲፊኬት፡ እና ኦሪጂናል የ I-589 ፎርም እንዲሁም ሁለት ቅጂዎች (የአገልግሎት ሰርቲፊኬትን ጨምሮ) ወደ ዳኛው በፖስታ ይላኩት። ሌላ 3 ቅጂዎች ማስረጃ ዶኩመንቶች (የአገርዎን ሁኔታ አስመልክቶ የሚደግፉ፣ ልዩ የሆነ የጉዳይዎን ገጽታ የሚደግፍ፣ ፓስፖርት ወይም የኢሚግሬሽን ዶኩመንቶችን፣ የመታወቂያ ዶኩመንቶች እና የቤተሰቦችዎን የዝምድና ማረጋገጫ) ለዳኛው ይስጡት። የዶኩመንቶችን በሙሉ ቅጂ ወደ DHS በፖስታ ይላኩ እና አንድ የመጨረሻ ቅጂ ለራስዎ ያስቀምጡ። አስፈላጊ የሆኑትን ዶኩመንቶችን ኦሪጂናል መላክ እንደሌለበት ያስታውሱ (ለምሳሌ፡ ፓስፖርት፣ የልደት እና የጋብቻ ሰርቲፊኬት፣ የመታወቂያ ወረቀት) የእነዚህ ነገሮች ቅጂ ብቻ ወደ ዳኛው እና DHS ይላኩ። አስፈላጊ የሆኑትን ዶኩመንቶች ኦሪጂናሉን ወደ መንግስት ከላኩ፡ እነዚህ አስፈላጊ ዶኩመንቶች ከመንግስት መልሰው ለማግኘት አይችሉም።</u>


## የጣት አሸራዎች እና ፎቶግራፎች

ከዚህ በፊት እንደገለጽነው፡ በማመልከቻዎ ላይ የቤተሰብ አባሎችን ያስገቡ ከሆነ፡ የጣት አሸራቸውን (ባዮሜትሪክስ) (ከ15 ዓመት ዕድሜ በታች ካልሆኑ በስተቀር) እና ፎቶግራፎችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል። እርስዎም እንደዛ ማድረግ ይኖርብዎታል። እስር ቤት ውስጥ ካሉ፡ DHS ይህን ነገር እንዲያጠናቅቅ ይጠይቁት። ማመልከቻውን በሚያስገቡበት ጊዜ፡ በቁጥጥር ስር ከሌሉ፡ ይህንን ነገር ራስዎ ማድረግ አለብዎት። የDHS የጽሑፍ ማብራርያ እንዲህ የሚል ርእስ አለው፡ *አንዳንድ ማመልከቻዎች ወደ የኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት የማስገባት እና የባዮሜትሪክ እና የግል መረጃዎች ወደ የዩኤስ የዜግነት እና የሰደተኛ አገልግሎቶች የማቅረብ መመርያዎች (Instructions For Submitting Certain Applications In Immigration Court and For Providing Biometric and Biographical Information to U.S. Citizenship and Immigration Services)* ይህም የጣት አሸራው (ባዮሜትሪክስ) እንዴት፣ መቼ እና የት መደረግ እንዳለበት የሚገልጽ ነው። <u>ባዮመትሪክስ በDHS መደረግ አለበት። ይህን ነገር በሌላ ማህበር ለማድረግ መሞከር የተብዎትም፡ ምክንያቱም እንደዛ ካደረጉ ተቀባይነት አይኖሮውም</u>። ማመልከቻዎን ለማስገባት እንደወሰኑ ለዳኛው በሚያሳውቁበት ጊዜ፡ ይህንን የሚገልጹ መመርያዎቹ ከDHS ጠበቃ ይቀበላሉ። በቂ ምክንያት ሳያቀርቡ፡ እነዚህ የባዮሜትሪክ መመዘኛዎች ካልፈጸሙ፡ ዳኛው ማመልከቻዎን ችላ እንዳሉ ሊቆጥረው እንደሚችል እባክዎን ያስታውሱ።

• <u>የወንጀል ክስ ያለባቸው ሰዎች</u>

ለጥገኝነት በሚያመለክቱበት ጊዜ፡ የወንጀል ክስ ወይም ሌላ አሉታዊ ነገር በጉዳይዎ በፊት ካለ፡ ዳኛው ወደ አገርዎ ከሄዱ ችግር ላይ ይወድቃሉ ብሎ ቢያምንም፡ የጥገኝነት ጥያቄዎን ግን ላይቀበለው እንደሚችል አስታውሱ። ጉዳይዎን የሚነካ የወንጀል ክስ ወይም ሌሎች አሉታዊ ነገሮች ካሉ፡ ሰላደረጉት ወንጀል እንደ ተጸጸቱ፣ ለህብረተሰቡ አደገኛ እንዳልሆኑ፣ እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ ታታሪ እና ጠቃሚ አባል እንደሚሆኑ ለዳኛው መግለጽ ይኖርብዎታል። ለምሳሌ፡ በደምብ የሚያውቅዎ ሰው -- ጎረቤት፣ የቤተክርስትያኑ አላፊ፣ እንዲሁም የቤተሰብ አባልም ቢሆን -- ስለእርስዎ የሂሊና ጸባይ እና ለምን እንደገና በህብረተሰቡ ላይ ችግር አያመጡም ብለው እንደሚያምኑ መግለጽ ይችላሉ። ከእስር ቤት ከወጡ በኃላ ስራ እንዲሰጡ፡ ከአንድ ስራ ቀጣሪ ደብዳቤ ቢያመጡ ደግሞ ይጠቅማል።

<u>ደብዳቤዎች</u>

- ሰዎች ለዳኛው በሚልኩት በደብዳቤ ላይ ምን ማለት አለባቸው? 

ጓደኞችዎ፣ የበተሰብዎ አባሎች፣ ወይም ስራ ቀጣሪው ምን ብለው መጻፍ እንዳለብዎት ካልነገሩዋችው፡ ደብዳቤአቸው ምን ማካተት እንዳለበት አያውቁም። ለእያንዳንዱ ደብዳቤ እንዲጽፍልዎት የሚፈልጉት ሰው፡ እርስዎ አስቀድመው ይጻፉለት። በሚጽፉት ደብዳቤ እንዲህ ማለት አለብዎት፥

1. በኢሚግሬሽን ሕግ ስር እንዳሉ እና በዚህ አገር እንዲቆዩ ለጥገኝነት እንዳመለከቱ ያሳውቁ። ስለ ወንጀሉ ክስ ወይም ሌላ ችግር ካለ፡ ከገለጹ በኃላ ለዳኛው የጥገኝነት መብት እንደሚገባዎ እና የህብረተሰቡ ጥሩ አባል እንደሚሆኑ ይግለጹ።

2. ደብዳቤ የሚጽፈውን ሰው እንዲህ ብሎ እንዲጽፍ ይጥይቁት፥

- ከእርሱ ወይም ከእርሷ ጋር እንዴት እንደሚተዋወቁ (ለምሳሌ፡ እሱ/እርሷ ጎረበትዎ፣ እህትዎ፣ አለቃዎ መሆኑን/መሆንዋን)፡ እንዲሁም ለምን ያህል እንደሚተዋወቁ።

- ሌላ ዳኛው ለማወቅ የሚፈልገው መረጃ፡ ለምሳሌ፥
    - ይህ ሰው ስለእርስዎ የሚያውቀው ጥሩ የሆነ ነገር ምንድነው? ለዚህ ሰው ወይም ለሌላ በቤተሰቡ ወይም በማህበረሰቡ ያሉት ሌሎች ሰዎች ያደረጉት መልካም ነገር ምንድነው?
    - ከተመለሱ ምን ይሆናሉ? ይህ ጥያቄ የእርስዎ አገር በተመለከተ በቂ እውቀት ያላቸው ሰዎች፡ እንደ የበተሰብዎ አባሎች፣ ብቻ ነው መመለስ የሚችሉት።
    - ምን ዓይነት የስራ ታሪክ አለዎት? አለቃዎ ወይም የድሮ አሰሪዎ የነበረ ሰዎች፡ ለምን ያህል ጊዜ ከእነርሱ ጋር እንደ ሰሩ፣ ምን ዓይነት ኃላፊነት እንደነበርዎት፣ ምን ዓይነት ሰራተኛ እንደነበሩ ያውቃሉ።
    - በጣም ከባድ የሆነ ወንጀል የፈጸሙ እንደሆነ፡ ስለእርስዎ በደምብ የሚያውቅ ሰው ወይም ደግሞ ወንጀሉ በሚፈጸምበት ጊዜ እዛ የነበረው ሰው፡ እርስዎ በወንጀሉ የተሳተፉበት እንዴት እንደነበር ሊናገር ይችላል። እንዲሁም እንደዚህ ዓይነት ወንጀል እንደገና አይፈጽምም እንዲሁም ለህብረተሰቡ አደጋ አይሆንም ብሎ ለምን እንዳመነ መጻፍ ይችላል። ወንጀሉን አስመልክቶ የረዳዎትን ጠበቃም ደብዳቤ እንዲጽፍልዎት ሊተይቁ ይችላሉ።

የኢሚግሬሽ ዳኛው <u>አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት</u> ብቻ ነው የሚገባዎት ብሎ ካመነ (ምክንያቱ የጥገኝነት

መብት ለማግኘት ብቁ ካልሆኑ)፡ ዳኛው እንደዚህ ዓይነቶች ደብዳቤዎች ማየት አይችልም። አስቀድመን እንደገለጽነው፡ ዳኛው እርስዎ ከለላ ለማግኘት ብቁ ነው ወይ ብሎ ለመወሰን ከፈለገ ብቻ ነው ወንጀሉን የሚያሳስበው፤ በሌላ አብባል፡ የፈጸሙት ወንጀል "በዓይነቱ ከባድ የሆነ" ለምሆኑ ማረጋገጥ ይፈልጋል።

- <u>የወንጀል ክስ አስመልክቶ ሌላ ማስረጃ</u>

የወንጀል ክስ ካለብዎት፡ ጉዳይዎን በደምብ ለመዘጋጀት፡ የሚያስፈልግዎ ሶስት ነገሮች አሉ፥

1) ከበፊቱ የወንጀል ክስ "የpresentence ዘገባ"፣
2) ስለእርስዎ ከDHS የተገኘ ዶኩመንት ቅጂ፣ እና
3) የእርስዎ የFBI "rap sheet"

እነዚህ ምን እንደሆኑ እና እንዴት ማግኘት እንደሚቻሉ፡ በመቀጠል እንገልጻለን።

- **የpresentence ዘገባ**

ይህ ዓይነት ዘገባ፡ አንዳንድ ጊዜ አንድ ሰው ለፈጸመው ወንጀል የቅጣት ውሳኔ ከማግኘቱ በፊት የሚጻፍ ዘገባ ነው። ስለ እርስዎ የግል ታሪክ፣ የወንጀል ታሪክ፣ ማስጠንቀቂያ እና ሕግን መጣስ የሚያጠቃልል፣ እንዲሁም ወንጀሉ ከእነዛ ጉዳዮች ጋር በማነጻጸር የሚናገር ዘገባ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ፡ ስለ እርስዎ መጥፎ ነገር የያዘ ሊሆን ይችላል። እንደዛ ከሆነ፡ የዚህ ቅጂ ለዳኛው መስጠት የለብዎትም። DHS የዘገባው ቅጂ ካለው እና እርስዎን ለማጥቃት እንዳይጠቀምበት፡ ሁል ጊዜ ዘገባውን ደግሞ ማንበብ አስፈላጊ ነው። በዛ ዘገባ መሰረት DHS ሊጠይቅዎ የሚችለው ጥያቄዎች ለመመለስ ይዘጋጁ።

በወንጀሉ ጊዜ እርስዎን ወክሎ የቀረበው ጠበቃ ጋ በመደወል ወይም በመጻፍ፡ የዚህ ዘገባ ቅጂ ማግኘት ይችላሉ። ጠበቃው ማን እንደነበረ ማስታወስ ካልቻሉ፡ ፋይሉን እንዲያይልዎት የDHS ባለስልጣንን ይጠይቁት። ከወንጀል ፍርድ ቤት የሚመጣ ወረቀት ላይ፡ ጠበቃዎ የነበረውን ሰው ስም የያዘ ነው። ጠበቃው የህዝብ ወኪል ከሆነ (ምንም ያልከፈሉት)፣ በካውንቲው የሚገኝ ወደ የህዝብ ጠበቃ ቢሮ መደወል ወይም መጻፍ ይችላሉ።

- **የDHS ፋይል**

**የ Freedom of Information /Privacy Act Request (ፎርም G-639)"** በሞምላት፡ በእርስዎ የኢሚግሬሽብ ፋይል ውስጥ ያለውን መረጃ ቅጂ እንዲሰጥዎት መጠየቅ ይችላሉ። ይህንን ማድረግ የሚችሉ የ G-639 ፍሮም በሞምላት ነው። የDHS ባለስልጣን እንዲሰጥዎት ይጠይቁ። <u>በእስር ቤት ውስጥ ካሉ፡ በፎሙ ላይ የሚሞሉት አድራሻ፡ የእስር ቤቱ ማእከል አድራሻ መሆን አለበት።</u> እርስዎን የማይመለከት ጥያቄ ካለ "አይመለከተኝም" ብለው ይምሉት። ፎርሙን በተለያዩ ቦታዎች ላይ መፈረም አለብዎት። መጀመርያ፡ ከጥያቄ ቁጥር ሁለት በታች ያለው "የጠያቂው ፊርማ" በሚለው ላይ፤ ከዛ በኃላ ከጥያቄ ቁጥር ሰባት በታች ያለው፡ "የዘገባው ባለቤት ፊርማ" በሚለው ላይ፤ በመጨረሻ ላይ ደግሞ በቁጥር ስምንት በታች ያለው "በአሜሪካ አገር የተፈረዱ ከሆነ...." ብሎ የሚጀምረው። እነዚህ በመፈረምዎ፡ የማባዛት ወጪ እንደሚከፍሉ ተስማምተዋል ማለት ነው፤ ነገር ግን ብዙ ጊዜ ምንም ክፍያ አይኖርም።

ፎርሙን ከሞሉት በኃላ፡ ኦሪጂናሉ በፖስታ አሽገው ፖስታው ላይ "FOIAን መጠየቅ" ብለው ከጻፉበት በኃላ ወደ DHS ይላኩት። በዚህ ረገድ ላይ የሚሰራ ሰው፡ አድራሻው፡ ሌሎች ወረቀቶቹን ከላኩበት አድራሻ የተለየ ሊሆን ስለሚችል፤ ባለስልጣኑን በሚኖሩበት የ DHS ክልል የሚሰራ "የFOIA ባለስልጣን" አድራሻ ምን እንደሆነ ይጠይቁ። አንድ ቅጂ ለራስዎ ያስቀምጡ። <u>የዚህ ፎርም ቅጂ ወደ ፍርድ ቤቱ መላክ የለብዎትም።</u>

ለጠየቁት ጥያቄ መልስ ለማግኘት ረጅም ጊዜ ሊወስድ ይችላልና፡ የፍርድ ቤቱ ቀጠሮ ከዛ በፊት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን፡ ይህንን ጥያቄ በመላክዎ ይጠቀማሉ እንጂ ምንም አይጎዱም፤ ፍርድ ቤቱ ውስጥ የእርስዎን ጉዳይ እንዲሸነፍ DHS ምን ዓይነት ማስረጃ ማቅረብ እንደሚሞክር ለማየት ያስችልዎታል። ፋይልዎን በማየትዎ፡ የወንጀሉ ወይም የኢሚግሬሉ ጉዳይዎ በተመለከተ ለመናገር እንዲዘጋጁ እና አንዳንድ የDHS ጠበቃ ወደ ዳኛው የሚያመጣቸው ነጥቦችን

እንዴት መቃወም እንደሚችሉ ጠቃሚ ይሆናል።

- **የFBI ዘገባዎች**

የወንጀል ክስ ካለብዎት፡ DHS በፋይልዎ ካስቀመጠው አንዱ ነገር "ራፕ ሺት" ("rap sheet") የሚባለውን ስለእርስዎ የወንጀል ታሪክ፡ እና ማንኛውም ዓይነት የእስራት ሁኔታ ያጠቃለለ በፌደራል የምርመራ ቢሮ (FBI) የሚገኝ ዘገባ ነው። ይህን ነገር ለማግኘት ከDHS ፋይል ቅጂ ከማግኘት ይልቅ በቀላሉ እና ቶሎ ብለው ሊያገኙት ይችላሉ። መላክ ያለብዎት ነገሮች 1) የተሞላ የጣት አሻራ ካርድ (ፎርም FD-258)፡ 2) ለ"FBI" የሚከፈል የ$18 ማኒ ኦርደር፡ 3) ራፕ ሽት እንዲሰጥዎ የሚጥይቅ ደብዳቤ። ደብዳቤው በመፈረም፡ የራፕ ሺቱ እንዲላክልዎት የሚፈልጉትን አድራሻ ይጻፉበት። ሪከርዱን መቼ እንደሚፈልጉት ደግሞ መግለጽ አለብዎት፤ ምክንያቱም እስከ ስምንት ሳምንታት ጊዜ ሊወስድ ስለሚችል። ይህን ካደረጉ በኃላ፡ ወደዚህ አድራሻ ይላኩት፥

የፌደራል የምርመራ ቢሮ (Federal Bureau of Investigations) – CJIS Division<br>
1000 Custer Hollow Road<br>
ክላርስበርግ፡ ዌስት ቨርጂንያ 26306

<u>የዚህ ደብዳቤ ቅጂ ወደ ፍርድ ቤት ወይም ወደ DHS መላክ የለብዎትም።</u>

## • <u>የእኔ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ጊዜ ምን ይሆናል?</u>

በመጨረሻ የፍርድ ቤት ቀጠሮዎ፡ ታሪክዎን ይናገራሉ፡ ዳኛው ደግሞ ውሳኔ ይሰጣል። በፍርድ ቤት ቀጠሮው ጊዜ፡ የኢሚግሬሽን ዳኛ፣ አስተርጓሚ (የእንግሊዘኛ ቋንቋ በደምብ የማይችሉ ከሆነ)፣ DHSን የሚወክል ጠበቃ (የምርመራ ጊዜ ጠበቃ ተብሎ የሚጠራ)፣ እና እርስዎም ይገኛሉ። ምስክሮች ካሉት ደግሞ እነሱም መገኘው ይኖርባቸዋል። DHS እርስዎን የሚቃወሙ ምስክሮችን ሊያመጣ ይችላል።

የወንጀል ክስ ካለ Iየጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቀ ላለመውጣት የመከላከል መብት እንዳያገኙ ሊያግድዎት ይችላል፡ እና ዳኛው የፈጸሙትን ወንጀል የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቀ እንዳይወጡ የመከላከል መብት እንዳያገኙ ይከለክላል ወይስ አይከለክልም ለማየት ቀጠሮው ወደ ሌላ ቀን እንዲተላልፍ ያደርጋል። በዚህ ቀጠሮ ካሸነፉ፡ የጥገኝነት ፍቃድ እና/ወይም አገርን ለቀ ላለመውጣት የመከላከል መብት ያገኛሉ።

በየጥገኝነት/አገርን ለቀ ለለመውጣት መከላከል ቀጠሮ መጨረሻ ላይ፡ ብዙ ጊዜ ዳኛው ጉዳዩን፡ ማሸነፍዎን ወይም አለማሸነፍዎን ይናገራል። አንዳንድ ጊዜ ግን፡ ዳኛው እንዲያስብለት ጊዜ ሊወስድ ይችላል፡ ወይም ደግሞ ውሳኔው በጽሑፍ ያስቀምጥ እና ስለ ውሳኔው ለማወቅ ትንሽ ያስጠብቅዎታል።

### • በፍርድ ቤት ቀጠሮው ላይ ዳኛ ምን ያደርጋል?

ዳኛው የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቀ ላለመውጣት የመከላከል መብት ወይም ደግሞ አገርን ለቀ እንዳይወጡ የመከላከል መብት እና የ CAT ሕግ ከለላ ያገኛሉ ወይስ አያገኙም ብሎ ውሳኔ ይሰጣል። በሞሉት ፎርም፣ የጻፉት መግለጫ፣ እና ሌሎች ዶኩመንቶችን መሰረት በማድረግ ጥያቄ ይጠይቅዎታል፤ ይህም የሚጠይቅበት ምክንያት፡ አገርዎን ለምን ለቀው እንደመጡ የበለጠ ለማወቅ እና፤ እንዲሁም እውነቱን እየተናገሩ መሆንዎን ለመወሰን ነው።

### • የDHS ጠበቃ (በምርመራ ጊዜ ጠበቃ) ምን ያደርጋል?

በምርመራ ጊዜ ጠበቃው ደግሞ ጥያቄ ይጠይቅዎታል። እርሱ ወይም እሷ፡ የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቀ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ማግኘት እንደማይገባዎት ዳኛውን ለማሳመን ይጥራል። እንዲሁም ለጥገኝነት እያመለከቱ ከሆነ፡ የምርመራው ጊዜ ጥበቃ ይህንን ፍቃድ እንደማይገባዎት ለማሳየት ይሞክራል። እርስዎን ጥያቄ የሚጠይቅበት ምክንያት፡

እንዲደናበሩ ስለፈገለ ወይም እውነት እየተናገረ አይደለም ብሎ ለማሳየት ስለፈለገ ነው። በምርመራው ጊዜ ጠበቃው፡ አንዳንድ የተናገሩትን ነገሮች፡ በማመልከቻ ፎርም ከጻፉት ጋር እንደማይስማማ ለማሳየት ይሞራል። ወይም ደግሞ ወደ አሜሪካ አገር የመጡ፡ ለመስራት፣ ወይም ከብሄራዊ አገልግሎት ለመሸሽ፣ እንጂ የስቃይ ቅጣት ፈርተው እንዳልሆነ ለማሳመን ይሞክራል። ማመልከቻዎ በሚሞሉበት ጊዜ ያልጻፉት መረጃ አሁን በፍርድ ቤት ቀጠሮ ካነሱት፡ በማመልከቻዎ ለምን እንዳልተጻፈ ለመግለጽ ተዘጋጁ፤ ምክንያቱ የምርመራው ጊዜ ጠበቃው መረጃው በፎሙ ያልተጻፈበት ምክንያት አሁን እየዋሹ ስለሆነ ነው ብሎ ዳኛውን ለማሳመን ይሞክራልና።

**• አስተርጓሚው ምን ያደርጋል?**

አስተርጓሚው፣ ዳኛው፣ እና የምርምራ ጊዜ ጠበቃው የጠየቁትን ጥያቄዎች ይተረጉማል፡ እንዲሁም እርስዎ የሰጡትን መልሶች ወደ እንግሊዘኛ ይተረጉማል። የአንተርጓሚው ስራ፡ እያንዳንዱ የተጠየቀው ጥያቄ እና እያንዳንዱ የተሰጠው መልስ መተርጎም ነው። አስተርጓሚው የሚለውን ነገር ለመረዳት ችግር ካለ፡ ወይም ደግሞ አስተርጓሚው የተናገሩትን ነገር በትክክል አላለውም ብለው ካሰቡ፡ ይህንን ነገር ዳኛውን እንዲያውቅ ያድርጉ።

**• ምስክሮች ካሉ ምን ያደርጋሉ?**

ምስክሮቹ፣ ዳኛው፣ የምርመራ ጊዜ ጠበቃው ወይም እርስዎ የጠየቁትን ጥያቄዎች ይመልሳሉ። ምስክሩ እርስዎን ደግፎ ለመመስከር የመጣ ከሆነ፡ መጀመርያ መጠየቅ ያለብዎት እርስዎ ነዎት። እርስዎ መጠየቅ ከጨረሱ በኃላ ዳኛውና ጠበቃው ይጥይቃሉ። እርስዎን ከሚጠይቁት ጥያቄዎች ጋር ተመሳሳይ ነው። DHS ምስክሮች ካመጡ፡ ለእነሱም ለመጠየቅ ዕድል ይሰጥዎታል።

**• ምን ማድረግ አለብኝ?**

በመጀመርያ የምርመራው ጊዜ፡ ዳኛው የላኩትን ዶኩመንቶቹን በሙሉ እንደተቀበለ ማረጋገጥ አለብዎት። ማመልከቻውን ካስገቡ በኃላ አዲስ ደብዳቤ፣ ጽሑፍ፣ ወይም ሌላ ዶኩመንቶች ከተቀበሉ፡ በመጀመርያ ለዳኛው ይስጡት፡ ቅጂ ደግሞ ለመርማሪው ጠበቃ (ሁል ጊዜ አንድ ቅጂ ከእርስዎ ጋር ያስቀምጡ)።

በዳኛው እና በመርማሪው ጠበቃ የተጠየቁትን ጥያቄ ይመልሳሉ። የሚናገሩትን ቃላቶች በሙሉ አስተርጓሚው በደምብ መስማት እንዲችል፡ በጥራት ይናገሩ። አንድ ወይም ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ከተናገሩ በኃላ አስተርጓሚው እንዲተረጎም ጊዜ ይስጡት፤ ምክንያቱም ዳኛው የሚሰማው አስተርጓሚ የተናገረውን ብቻ ስለሆነ። በተጨማሪም፡ በሚናገሩበት ጊዜ ዳኛውን ፊርት ለፊት እዩት፡ ወለሉ ወይም አስተርጓሚው ብቻ ማየት የለብዎትም። ካልሆነ፡ ዳኛው እየዋሸ ነው ወይም እርግጠኛ አይደለም ብሎ ሊያስብ ይችላል።

## • <u>ለፍርድ ቤት ቀጠሮ እንዴት መዘጋጀት አለብኝ?</u>

ለፍርድ ቤት ቀጠሮ ዝግጁ ለመሆን፥

1. ከተቻለ፡ ጽሑፎች፣ የሰብአዊ መብቶች ዘገባዎች፣ እንዲሁም ሌሎች ዶኩመንቶችን እንዲቀርቡ ይጠይቁ፤ ምክንያቱም ዳኛው እነዚህ ነገሮች ሲያይ፡ ከአሁን በፊት እንደተሰቃዩ እና ወደ አገርዎ ከተመለሱ ደግሞ እንደሚሰቃዩ እንዲያምን ያግዛሉ።

2. የጻፉት መግለጫ፣ ማመልከቻ፡ እንዲሁም ወደ ፍርድ ቤቱ ያስገቡት ማንኛውም ዶኩመንት እንደገና ያንብቡት። የተሰጡትን ነጥቦች፣ ቀኖች፣ እና ሌሎች ዝርዝር መረጃዎችን ለማረጋገጥ <u>ብዙ ጊዜ</u> ያንብቡት።

3. በመግለጫዎ ላይ የተጻፉትን በጣም አስፈላጊ የሆኑት ክስተቶች፡ በተለይም ባለፉት ጊዜ የተከሰተ፡ ጉዳት ወይም ማስፈራራት በዝርዝር ጻፉ። ዳኛው ወይም የምርመራ ጊዜ ጠበቃው ስለእነዚህ ነገሮች ይጠይቅዎታል። እነዚህ ነገሮች ጩክ ብሎ በመናገር ይለማመዱ። በቀጠሮው ጊዜ ዳኛው ወይም የምርመራ ጊዜ ጠበቃ፡ እነዚህ ነገሮች በተመለከተ ካልጠየቅዎት፡ ራስዎ ለመግለጽ ተዘጋጁ።

4. ምስክሮች ካመጡ፤ በፍርድ ቤት እነሱን ለመጠየቅ የሚፈልጉትን ጥያቄ ይጻፉት። ጥያቄዎቹን እና መልሶቹን ደጋግመው ያንብቡት።

**በተጨማሪ፡ የወንጀል ችግር ካለብዎት፡**

**ጉዳይዎን የሚደግፉ ደብዳቤዎች እና ሌሎች ዶኩመንቶችን ያሰባስቡ (የሚጠቅምከሆነ የpresentence ዘገባው ጭምር)፡ የወንጀል ክስዎን አስመልክቶ ለመናገር ራስዎን ያዘጋጁ።**

## • <u>ዳኛው የእኔ ጉዳይ በተመለከተ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ምን ይሆናል</u>

እርስዎ እና DHS፡ የኢሚግሬሽን የይግባኝ ቦርድ ተብሎ የሚጠራው ወደ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመሄድ ይግባኝ የማለት መብት አላቹ። ይህ ፍርድ ቤት በቨርጂንያ የሚገኝ የጠበቃዎች ብድን ሲሆን፡ ጉዳዩ በተመለከተ የተሰጡትን ወረቀቶች እና፡ በፍርድ ቤቱ ውስጥ የተባለውን በሙሉ በማየት ዳኛው የሰጠው ውሳኔ ትክክል መሆኑን እና አለሆኑን ያያሉ። አብዛኛው ጊዜ፡ ዳኛው ሕጉን በተመለከተ ወይም በማመልከቻው የተሰጠውን መረጃ በተመለከተ ስህተት ካላደረገ በስተቀር፡ ቦርዱ የተሰጠውን ውሳኔ አይቀይሩትም። ዳኛው ውሳኔ ከነገርዎት በኋላ ወድያውኑ፡ (በኋላ በጽሑፍ ካልተቀበሉት በስተቀር)፡ ዳኛው ለእርስዎ እና ለምርመራ ጊዜ ጥበቃው ይግባኝ ማለት የሚፈልጉ ከሆነ ይጠይቃቹሀል። ይህ ማለት ደግሞ ያላችሁ የይግባኝ መብት ለመጠቀም የሚፈልጉ እንደሆኑ ብሎ ነው። ሁለቱም ወገኖች "ይግባኝ ከሰረዙ"፡ ማለትም ይግባኝ የማለት መብታችሁን ለመጠቀም ካልፈለጉ፡ ጉዳዩ ይዘጋል ማለት ነው። አንዴ "ይግባኝ ከሰረዙ" ተመልሰው አሳብዎ በመቀየር የዳኛው ውሳኔ መቃወም አይችሉም። ይግባኝ ለማለት እርግጠኛ ካልሆኑ ደግሞ፡ ዳኛው ጉዳዩ እንዲዘጋ ያደርጋል። ሁል ጊዜ የይግባኝ መብትዎ መጠበቅ ይኖርብዎታል። አንድ ሰው "የይግባኝ መብቱ ከጠበቀ"፡ የይባኝ ማመልካቻ ለመላክ 30 ቀናት ይሰጥዋል፤ በዛን ጊዜ "የይግባኝ ማመልከቻ" የሚለውን ፎርም በሞምላት ቨርጂንያ ወዳለው ቦርድ መላክ አለበት። DHS ይግባኝ ካለ፡ የይግባኝ ማመልከቻ ቅጂ ወደ እርስዎ መላክ ይኖርበታል፤ እርስዎ ይግባኝ ካሉ ደግሞ ቅጂ ወደ DHS መላክ አለብዎት። ሁለቱም ወገኖች በ30 ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማመልከቻ ካላስገቡ፡ የኢሚግሬሽን ዳኛው ውሳኔ የመጨረሻ ሆኖ ይጽድቃል። የይግባኝ ማመልከቻው፡ ወደ የኢሚግሬሽን የይግባኝ ቦርድ ዳኛው ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ያለው የ30 ቀናት የጊዜ ገደብ ውስጥ መድረስ አለበት።

## • DHS የተሰጠኝ ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ካለ ምን ይሆናል?

የምርመራ ጊዜ ጠበቃው "የይግባኝ መብቴን እጠብቃለሁኝ" ማለት ይችላል፤ ይህ ማለት ግን DHS ይግባኝ ይላል ማለት አይደለም። በሚቀጥሉት 30 ቀናት ውስጥ ከዳኛው ውሳኔ ይሰማሉ፡ እና በዛ ጊዜ DHS የይግባኝ ማመልከቻ ካላስገባ፡ ይግባኝ ማለት አይችልም (ማወቅ ይኖርብዎታል ምክንያቱ ይግባኝ ካስገባ፡ ቅጂው ወደ እርስዎ ስለሚላክ)።

DHS የይግባኝ ማመልከቻ ካስገባ፡ ወይም ደግሞ በፎርሙ ላይ አጭር መግለጫ ባኃላ በጽሑፍ ያቀርባል ካለ፡ የኢሚግሬሽን የይግባኝ ቦርድ፡ በኃላ DHS አጭር የጽሑፍ መግለጫ ያቀርባል የሚለውን ወረቀት ወደ እርስዎ እና ወደ DHS ይልካል፤ ወይም ደግሞ ወደ ቦርድ መልስ ለመላክ ከፈለጉ፡ የDHS ነጥቦችን በማየት መልስ መላክ ይችላሉ።

**በተጨማሪ፡ እርስዎ ካሸነፉ እና DHS ይግባኝ የማለት መብቱ ከተጠቀበት፤**

ዳኛው ወይም **DHS** በራስዎ ታዋቂነት መሰረት ከፍርድ ቤት እንዲወጡ መጠየቅ ይችላሉ (የገንዘብ ዋስትና ሳይከፍሉ)!

በዚህ አጭር ጽሑፍ መጀመርያ ላይ እንደገለጽነው፡ አንዳንድ ሰዎች፡ ዳኛው ከእስር ቤት እንዲያስወጣቸው ለመጠየቅ ብቁ ናቸው፤ አንዳንድ ሰዎች ግን ብቁ ስላልሆኑ እንዲወጡ DHSን መጠየቅ ይኖርባቸዋል። የገንዘብ ዋስትና በማስያዝ

እንዲወጡ ዳኛውን ለመጠየቅ ብቁ ከሆኑ እና ከተፈቀደልዎት፣ ዳኛው ነጻ እንዲለቅዎት በዛን ጊዜ ይጠይቁት። በዛን ጊዜ ዕድሉን ካላገኙ፣ የገንዘብ ዋስትና በማስያዝ እንዲወጡ የሚጥይቅ ደብዳቤ ወደ ዳኛ ይላኩ (ከአሁን በፊት እንደዛ አድርገው ከሆነ)።

**• ከተሸነፍኩኝ፡ እንዴት ይግባኝ ማለት እችላለሁኝ**

ከተሸነፉ እና ይግባኝ ለማለት ከጠየቁ፣ የኢሚግሬሽን የይግባኝ ቦርድ በ30ኛው ቀን ወረቀቶቹን ማግኘት አለበት። ካልሆነ፣ ዳኛው መልሶ አያየውም እና በቀላሉ ይሸነፋሉ።

ዳኛው የይግባኝ ውሳኔ እንዲሰጥዎ፣ ሞምላይ ያለብዎት ፍርሞችን እንደሚከተሉት ናቸው፥

1. ነጭ "የይግባኝ ማመልከቻ" ፎርም (EOIR-26)፣ እና
2. ቡናማ "የይግባኝ ማመልከቻ ማስቀረት" ፎርም (EOIR-26A) ($110 መክፈል የማይችሉ ካልሆነ በስተቀር፣ ለማንኛውም በ"የይግባኝ ማመልከቻ እና ክፍያ መክፈል" በሚለው ያለው መመርያን ይከተሉ)

ፍሮሞቹ እንዴት መሙላት እንዳለብዎት እና ወዴት መላክ እንዳለብዎት ይገልጻሉ።

ከ 30 ቀናት በኃላ የይግባኝ ወረቀቶቹ ወደ ቪርጂንያ ካልደረሱ፣ ይግባኝ ለማለት አይችሉም፣ እና የዳኛው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል። ስለሆነም፣ ወረቀቶቹ በተቻለ መጠን ቶሎ ብለው በአስቸኳይ የፖስታ አገልግሎት በኩል መላክ እንዳለብዎት እናሳስባለን (የደረሰኝ ማረጋገጫ መያዝ አለብዎት)።

ቦርዱ ፎርሙን ከተቀበለው፣ DHS አንዳንድ ወረቀቶች ፋይል ማድረግ እንዲችል እድል ይሰጥዋል። DHS ያስገባውን ወረቀት ቅጂ በሙሉ ይሰጥዎታል።

በይግባኝ ሂደት ጊዜ በእስር ቤት ስር ከነበሩ፣ ቦርዱ የይግባኝ ውሳኔ ለመስጠት አብዛኛውን ጊዜ ከአራት እስከ ስድስት ወራት ይወስዳል። በይግባኝ ሂደት ጊዜ ከእስር ቤት ውጭ ከሆኑ፣ በጣም የረዘመ ጊዜ ይወስዳል። የታወቀ የጊዜ ገደብ የለም፤ ስለሆነም ለይግባኝ ውሳኔ ስንት ጊዜ እንደሚያፈልግ ለመወሰን አይቻልም።

- **የኢሚግሬሽን የይግባኝ ቦርድ እኔን በመቃወም ውሳኔ ከሰጠስ ምን ይሆናል?**

የቦርዱ ውሳኔ በመቃወም፣ ወደ የፌደራል ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላሉ፤ ነገር ግን የፌደራሉ ፍርድ ቤት ልዩ የሆኑ ጉዳዮች ብቻ ነው የሚያዩት። በተጨማሪም፣ አገርን ልቀ ላለመውጣት በተሰጠው ውሳኔ መሰረት፣ ከፌደራል ፍርድ ቤት "stay" የሚባል ልዩ የሆነ ትእዛዝ ካልተቀበሉ በስተቀር፣ ፌደራል ፍርድ ቤቱ ጉዳይዎን እያየ ሳለ፣ DHS ከአገር ሊያስወጠዎት ይችላል። ይህ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊፈጸም ይችላል። ስለዚህ ወደ ቦርድ ይግባኝ ካሉ፣ ቦርዱ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ወድያውኑ የጠበቃ እርዳታ መፈለግ ይኖርብዎታል። ምክንያቱ ቦርዱ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ፣ እንዲቆዩ የሚወስን ትእዛዝ ለማግኘት ፋይል ማድረግ አለብዎት። ወደ ፌደራል ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት በጣም የተወሳሰበ ጉዳይ ነው፣ ስለሆነም እህ አጭር ጽሁፍ እንዴት እንደሚደረግ አይገልጽም።

- **<u>የፍርድ ቤት የቀጠሮ ቀን በፊት ከእስር ቤት ከወጣሁኝ ምን ይሆናል?</u>**

ጉዳይዎ ከማለቁ በፊት ከእስር ቤቱ እንዲወጡ ከተፈቀደልዎት፣ ጉዳይዎ ግን ይቀጥላል። አድራሻ ከቀየሩ፣ በአምስት

ቀናት ጊዜ ውስጥ የ EOIR-33/IC ፎርምን በመሙላት ፍርድ ቤቱን ማሳወቅ ይኖርብዎታል። ፍርድ ቤቱ ደግሞ ቀጥሎ ያለው የፍርድ ቤት ቀጠሮ በተመለከተ ቀኑን፣ ጊዜው፣ ቦታው የሚገልጽ ደብዳቤ ይልክልዎታል።

ስለዚህም፡ በተቻለ መጠን ወድያውኑ፤ ሕጋዊ እርዳታ መፈለግ ይኖርብዎታል። እንዳይዘገዩ!

**ከእስር ቤት ከወጡ፡ ጉዳይዎን በተመለከተ ሕጋዊ እርዳታ ይፈልጉ!**

ጉዳይዎ ወደ ተጀመረበት ፍርድ ቤት ለመሄድ ካልፈለጉ በስተቀር፡ እርስዎ እና ጠበቃዎ፡ ጉዳዩን ወደ ሌላ ፍርድ ቤት እንዲያስተላልፉት፡ ፍርድ ቤቱን መጠየቅ፡ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህን ለማድረግ "Motion for Change of Venue" ተብሎ የሚጠራውን ፎርም ላይ ከእስር ቤት ከወጡ በኃላ የሚኖሩበትን አዲሱ አድራሻ እዛ ይጽፉሉ። (ይህ <u>የጎዳና</u> አድራሻ እንጂ ፖ.ሳ.ቁጥር መሆን የለበትም!)። በዚህ አጭር ጽሑፍ መጨረሻ ገጽ ላይ፡ የዚህ ዓይነት ፎርም አለ፡ ነገር ግን አንዳንድ ፍርድ ቤቶች ሌላ ዓይነት ፎርም እንዲጠቀሙ ይፈልጋሉ፤ ለማንኛውም ያንብቡት እና ይወስኑ። በአንዳንድ የእስር ቤት ማእከሎች፡ የDHS ባለስልጣን ፎርሙን ሊሰጥዎ ይችላል፤ እና ምልተው ከጨረሱ በኃላ ለፍርድ ቤቱ ያስረክቡት። የነበሩበት እስር ነገሮች እንዴት እንደሚሰሩ ካወቁ በኃላ ትክክለኛውን ፎርም እንደሞሉ ያረጋግጡ (አንድ ቅጂ ደግሞ ለDHS ጠበቃ ይስጡት)። ፍርድ ቤቱ ይህን ወረቀት ከተቀበለ በኃላ፡ በሰጡት አድራሻ መሰረት አቅራብያ ወደ ሆነው የኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት ይልከዋል። አዱሱ ፍርድ ቤት እንግዲህ፡ በሚቀጥለው የፍርድ ቤት ቀጠሮዎ እንዲገኙ የት እና መቼ እንደሚሆን ደብዳቤ በመላክ ያሳውቆታል። ይህ ደብዳቤ ከተቀበሉ በኃላ፡ በእርስዎ አዲሱ አድራሻ ወደ ሚገኘው ፍርድ ቤት እና DHS ብቻ መላክ ይኖርብዎታል።

**ከእስር ቤት ከወጡ በኃላ፡ ቀጥሎ ያለው የፍርድ ቤት ቀጠሮ አሁን ባሉበት እንዲሆን ካልፈለጉ፡ የ"Motion for Change of Venue" ፎርም በመሙላት ማስገባት ይኖርብዎታል!**

አንዳንድ ፍርድ ቤቶች፡ ለምን ፍርድ ቤት መቀየር እንደሚፈልጉ ረጅም መግለጫ እዲያቀርቡ ይጠይቃሉ። በፍርድ ቤት ቀጠርው ጊዜ፡ እንደዛ ማድረጉ አስፈላጊ ከሆነ ለማወቅ ዳኛውን ይጠይቁ።

በፍርድ ቤት ቀጠሮ ቀን ካልተገኙ፡ ዳኛው፡ የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ ላለመውጣት የመከላከል መብት ለማግኘት ምንም ዕድል ሳይሰጥ፡ ከአገር እንዲወጡ ማድረግ እንደሚችል አስታውሱ።

**• ወደ ሌላ ሰፈር ከሄድኹኝ ምን ማድረግ አለብኝ?**

**ወደ ሌላ ሰፈር የሄዱበት እያንዳንዱ ጊዜ፡ የኢሚግሬሽን ፍርድ ቤትንና DHSን ማሳወቅ <u>የራስዎ</u> ሐላፊነት ይሆናል!** ይህን ነገር ለማድረግ የሚሞሉ ልዩ የሆኑ ፎርሞች አሉ፤ አንዱ ዓይነት (EOIR 33/IC) የተባለው ፎርም ከፍርድ ቤት ማግኘት ይችላሉ፤ ሌላው ደግሞ የ(AR-11) ፎርም ከDHS ማግኘት ይችላሉ (በሚዘዋወሩበት ጊዜ ባለስልጣኖቹ ፎርሙን ሊሰጥዎት ይችላሉ)። አዲስ አድራሻዎ ምን መሆኑን ፍርድ ቤቱን እና DHSን ማሳወቅ፡ የፍርድ ቤት ቀጠሮው የት እንደሚሆን አይወስነውም። ነገር ግን፡ አድራሻን መቀየር በተመለከተ የሚሞሉ ፎርሞች፡ ፍርድ ቤቱና DHS ጉዳይዎን በተመለከተ ወረቀቶቹ ወዴት መላክ እንዳለባቸው ለማወቅ ይረዳቸዋል።

የኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት እና DHS ዶኩመንቶችን መላክ ሲፈልጉ፡ ከእርስዎ የተቀበሉትን አድራሻ በመጠቀም ይልኩታል። ፍርድ ቤት የእርስዎ የድሮ አድራሻ ብቻ ካለው፡ የሚቀጥለው የፍርድ ቤት ቀጠሮው መቼ እንደሚሆን የሚገልጽ ደብዳቤ ወደ የድሮ አድራሻዎ ይሉኩታል፤ እርስዎ ደግሞ በተባለው ቀን ወደ ፍርድ ቤቱ ሳይመጡ ሲቀሩ፡ አገርን ለቀው እንዲወጡ ትእዛዝ ይሰጣሉ። ይህ ማለት፡ DHS እንደገና በሚይዝዎት ጊዜ፡ ምንም የፍርድ ቤት ቀጠሮ ሳያደርግ በቀጥታ ወደ አገርዎ እንዲመለሱ ያደርጋል።

ወደ ሌላ ሰፈር ከሄዱ፡ ከወጡበት ቀን ጀምሮ በ5 ቀናት ውስጥ፡ አዲሱ አድራሻዎ የት እንደሆነ የሚገልጽ የEOIR 33/IC ፎርም በሞምላት ወደ የኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት ይላኩት! በተጨማሪም፡ ከወጡበት ቀን ጀምሮ በ10 ቀናት ውስጥ፡ አዲሱ አድራሻዎ የት እንደሆነ የሚገልጽ የAR-11 ፎርም በሞምላት ወደ DHS ይላኩት!

ፍርድ ቤቱንና DHSን ሁለት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። ስለ አዲሱ አድራሻው DHSን ካሳወቁ፡ ነገር ግን ወደ የኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት ትክክለኛውን ፎርም ካልላኩ (ሰማያዊ EOIR 33/IC፡ "አድራሻን ስለ መቀየር" የሚል ፎርም)፡ ፍርድ ቤቱ ወረቀቶቹን የሚልከው ወደ የድሮ አድራሻዎ ብቻ ይሆናል፡ በዚህ የተነሳ ከፍርድ ቤት ቀጠሮዎ ይቀራሉ። እንደዛ ከሆነ ደግሞ፡ ዳኛ ለማየት ዕድል ሳያገኙ አገርን ለቀው እንዲወጡ ትእዛዝ ይሰጣሉ። ጉዳይዎ ይግባኝ በማለት ወደ የኢሚግሬሽን የይግባኝ ቦርድ የተላከ ከሆነ ደግሞ ልክ እንደዚህ ይሆናል። ወደ ሌላ ቦታ ከተዘዋወሩ በ5 ቀናት ውስጥ የ EOIR-33/BIA ፍሮም በመሙላት የኢሚግሬሽን የይግባኝ ቦርዱ ማሳወቅ ይኖርብዎታል።

**• የስራ ፍቃድ ማግኘት እችላለሁኝ ወይ?**

የጥገኝነት ፍቃድ እና/ወይም አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት እንዲያገኙ ወደ የኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት አስገብተው ከሆነ የስራ ፍቃድ ሊያገኙ ይችላሉ፤ ነገር ግን የስራ ፍቃድ እንዲሰጥዎት ለማመልከት፡ <u>የጥገኝነት ፍቃድ እንዲሰጥዎ ካመለከቱ በኃላ 150 ቀናት መጠበቅ ይኖርብዎታል</u>። 180 ቀኖች ከመሆኑ በፊት ጉዳይዎን ከተሸነፉ፡ የዳኛው ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ቢሊም፡ የስራ ፍቃድ ሊያገኙ አይችሉም። ከ180 ቀኖች በፊት የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል ፍቃድ ካገኙ፤ ጉዳይዎ ካሸነፉ በኃላ ወድያውኑ፡ የስራ ፍቃድ እንዲሰጥዎት ማመልከት ይኖርብዎታል። የጥገኝነት ፍቃድ እና አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ከጠየቁ 150 ካለፈ እና ጉዳይዎ ደግሞ ገና ውሳኔ ያልተሰጠበት ከሆነ፡ የስራ ፍቃድ ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ፡ ነገር ግን 180 ቀኖች እስከሚያልፉ ድረስ ፍቃዱ አይሰጥዎትም።

| የስራ ፍቃድ ለማግኘት ማመልከት (የI-765 ፎርም) |
|---|

የስራ ፍቃድን ለማግኘት በሚያመለክቱበት ጊዜ፡ "የI-765 ፎርም" በሞምላት፡ ከ I-589 ፎርም (የጥገኝነት ማመልከቻ - ፎርሙን እና መግለጫዎች ብቻ)፡ እንዲሁም በኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት እንዳስገቡት የሚያሳይ ማስረጃ ጭምር፡ አንድ ላይ በማያያዝ በፎርሙ መመርያ ላይ ወደተጻፈው አድራሻ በፖስጣ መላክ ይኖርብዎታል። የኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት በማመልከቻዎ የመጀመርያ ገጽ ላይ መቼ እንደገባ ቀኑን የሚያሳይ ማህተም፡ ስለሚያደርጉበት፤ ይህ እንደማስረጃ ሊሆን ይችላል። ካልሆነ ደግሞ፡ ከፍርድ ቤቱ የማመልከቻዎ የመጀመርያ ገጽ ቅጂ ማግኘት ይችላሉ። ጉዳይዎን ያሸነፉ ከሆነ፡ የዳኛው ትእዛዝ ቅጂ ከ I-765 ፎርም ጋር አያይዘው ይላኩ። የጥገኝነት ጉዳይዎ ያሸነፉ ከሆነ፡ ዳኛው በቃል የሰጥዎትን መመርያዎች እና የDHS የምርመራ ጊዜ ጠበቃ በጽሑፍ የሰጥዎትን (*Post-Order Instruction for Individuals Granted Relief or Protection from Removal by Immigration Court*) የሚል መግለጫ መከተል፡ ይኖርብዎታል። ይህም የመኖርያ እና የስራ መስራት ፍቃድ ከDHS እና የዩኤስ የዜግነት እና የኢሚግሬሽን አገልግሎቶች ለመቀበል ነው። ማስታወሻ፥ አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ፍቃድ የመጨረሻ ውሳኔ የተቀበሉ ከሆነ፡ የ I-765 ፎርም እንዴት እንደሚሞላ መመርያውን መከተል አለብዎት።

የስራ ፍቃድ ለማግኘት የማመልከቻ ፎርም ጋር የሚመጣን መመርያ በደምን ያንብቡት እና የጥያቄዎቹን በሙሉ መልስ ይስጡ። እንዲሁም ከማመልከቻው ጋር ምን ማያያዝ እንዳለብዎት በመመሪያው ላይ ተገልጸዋል።

**ለጥያቄ #14፡** በሕገወጥ መንገድ የገቡ ከሆነ፡ "ሳይፈተሸገባ" ("entered without inspection") ብለው ይጻፉ።

**ለጥያቄ #15፡** ዳኛው ጉዳይዎን በተመለከተ ገና ውሳኔ ያልሰጠ ከሆነ፡ "ጥገኝነት/እንዳይወጡ መከላከል የዘገየ" ("asylum/withholding pending") ብለው ይጻፉ። የጥገኝነት ጉዳይዎ ያሸነፉ ከሆነ "ጥገኛ" ("asylee") ብለው ይጻፉ። አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ወይም በCAT ሕግ የከለላ ስር አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት የተፈቀደልዎት ከሆነ፡ "ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት የተፈቀደለት" ("granted withholding of removal") ብለው

ይጻፉ።

**ለጥያቄ #16፡ ዳኛው ጉዳይዎን በተመለከተ ገና ውሳኔ ያልሰጥ ከሆነ፡ ወይም ደግሞ፡ ካሸነፉ ነገር ግን DHS ይግባኝ ካለ፡ "(c)(8)" በመጻፍ፡ ማመልከቻው በፖስጣ ወደ DHS የአገልግሎት ማእከል ይላኩት (የትኛው መላክ እንዳለብዎት መመርያው ያሳያል)። የጥገኝነት ጉዳይዎ ካሸነፉ እና DHS ደግሞ ይግባኝ ካላለ፡ "(a)(5)" ብለው በመጻፍ፡ የኢሚግሬሽን ዳኛው በቃል የሰጥዎትን መመርያዎች እና የDHS የምርመራ ጊዜ ጠበቃ በጽሑፍ የሰጥዎትን (*Post-Order Instruction for Individuals Granted Relief or Protection from Removal by Immigration Court*) የሚል መግለጫ በመከተል፡ ይኖርብዎታል። እ.ኤ.አ ከሚያዝያ 1፣ 2005 ዓ.ም ጀምሮ፡ አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት ያሸነፉ ከሆነ፡ እና (የአጠቃላይ ወይም የCAT) እንዲሁም DHS ይግባኝ ያላለ ከሆነ፡ "(a)(10)" ይጻፉ እና የ I-765 ማመልከቻ ፎርም ወደ Chicago Lockbox Facility መላክ ይኖርብዎታል። የፖስታው አድራሻው እንደሚከተለው ነው፥ የዩኤስ ዘግነት እና የስደተኞች አገልግሎቶች ፖ.ሳ.ቁጥር 805887፡ Chicago፡ IL 60680-4120 ወይም የዩኤስ የፖስታ አገልግሎት (የግል የፖስታ ተላላኪ) የዩኤስ ዘግነት እና የስደተኞች አገልግሎቶች ለ፡ FBASI, 427 S. LaSalle – 3rd Floor, Chicago, IL 60605-1098. የCAT የማስወጣት ሂደት መዘግየት ፍቃድ ከተሰጥዎት ወይም ከDHS ቁጥጥር ነጻ ከወጡ፡ "(c)(18)" ይጻፉና፡ የስራ ፍቃድ የሚለው አጭር ጽሑፍ ያለው መመርያ ይከተሉ።**

**<u>የ I-765 ፎርም እና ከዛ ጋር በመያያዝ የላኩትን በሙሉ ያባዙት</u> እና ለራስዎ አንድ ቅጂ መያዝ አለብዎት፤ ማመልከቻው በፖስታ የሚልኩት ከሆነ፡ በአደራ ደብዳቤ መላክ አለብዎት። በመጀመርያ ጊዜ ለፍቃዱ የሚከፍሉት ምንም ነገር የለም። ለአንድ ዓመት ደግሞ ያገልግላል። በሚያሳድሱበት ጊዜ ግን የሚከፈል ክፍያ አለ።**

**የስራ ፍቃድ ወረቀት እንዲሰጥዎ ወይም እንዳይሰጥዎ ለመወሰን፡ የ30 ቀኖች ያህል ጊዜ ይወስዳል። በ30 ቀኖች ውስጥ ውሳኔ ካልተሰጡ፡ ለጊዜው የሚያገለግል የስራ ፍቃድ ለማግኘት በአከባቢው ወዳለው የDHS ቢሮ መሄድ አለብዎት።**

**• ከእስር ቤት ከወጣሁኝ በኃላ፡ ከአሜርካ አገር ወደ ሌላ አገር መሄድ እችላለሁኝ ወይ?**

**ጉዳይዎን ከመፈጸሙ በፊት <u>አገሩን ለቀው ከሄዱ</u>፡ ወድያውኑ ጉዳይዎ ውድቅ ይሆናል። <u>የመጨረሻ</u> ውሳኔ እስከሚያገኙ ድረስ ከአገሩ መውጣት የለብዎትም። ዳኛው የጥገኝነት ፍቃድ፣ አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት፣ ወይም አገርን እንዳይለቁ ጉዳዩን የማዘገየት መብት ቢሰጥዎትም፡ DHS ይህባኝ ካለ የተሰጠው ውሳኔ ገና የመጨራሻ አይደለም ማለት ነው።**

**የጥገኝነት ፍቃድ ከተሰጡ እና ውሳኔው ደግሞ የመጨረሻ ውሳኔ ከሆነ፡ ቋሚ የመኖርያ ፍቃድ (ግሪን ካርድ) እስከሚያገኙ ድረስ ለአንድ ዓመት ያህል መቆየት አለብዎት፤ ይህም Application to Register Permanent Residence ወይም Adjust Status የሚለውን የ I-485 ፎርም በመሙላት ይሆናል። በዚህ ጊዜ ውስጥ የI-131 ፎርም በመሙላት የጉዞ ፍቃድ ለማግኘት ወይም ደግሞ Advance Parole ለማግኘት በማመልከት ከ DHS ፍቃድ ከተሰጡ፡ ከአገር ወደ አገር ለመጓዝ ይችላሉ፤ ነገር ግን <u>ቋሚ የመኖርያ ፍቃድ ካልተሰጡ በስተቀር ወደ ትውልድ አገርዎ መመለስ የለብዎትም</u>፤ ካልሆነ የተሰጥዎት ሕጋዊ የመኖርያ ፍቃድ ይሻራል። አገርን ለቆ እንዳይወጡ የመከላከል መብት፣ ወይም አገርን እንዳይለቁ ጉዳዩን የማዘገየት መብት የተሰጡ ከሆነ፡ ከአሜሪካ አገር ወደ ሌላ ከመጓዝዎ በፊት፡ ጠበቃዎ ማነጋገር ያስፈልጋል።**

**• <u>ጉዳይዎን በደምብ ያዘጋጁ</u>**

**አንዳንድ ጊዜ፡ አንድ ጉዳይ የማሸነፍ እና የመሸነፍ ነገር፡ ጉዳዩን ለመዘጋጀት ምን ያህል ጊዜ እና ጉልበት እንደተጠቀሙ ይወስናል። በዚህ አጭር ጽሑፍ የተጻፈውን መመርያ ከተከተሉ፡ ጉዳይዎን ለማቅረብ ዝግጁ ይሆናሉ፡ እንዲሁም ለማሸነፍ የበለጠ ዕድል ይኖርዎታል። ጉዳይዎን በተመለከተ መልካም እድል እንመኛለን!**

© የፍሎረንስ የስደተኞች እና የጥገኞች መብቶች ፕሮጀክት (**The Florence Immigrant and Refugee Rights**

**Project, Inc.)፡ ሐምሌ 2002።** የፍሎረንስ ፕሮጀክት ይህንን መረጃ የማባዛት መብት ይሰጣል፡ እንዳለ፡ ለግል ጥቅም ወይም ደግሞ ለDHS በነጻ ለሌሎች እንዲሰጥ፡ በDHS ቁጥጥር ስር ያሉ እስረኞች፡ ወይም እነዚህ እስረኞችን የሚረዱ ማህበሮች። ነገር ግን፡ በዚህ ጽሑፍ ላይ ወይም ማንናውም የዚህ ጽሑፍ ክፍል ላይ ለውጥ ለማድረግ ከተፈለገ፡ በፕሮጀክቱ ሲፈቀድ ብቻ ነው። ይህን ፍቃድ ለመጠየቅ ደዚህ አድራሻ በመጻፍ ይሆናል፡ Director, the Florence Immigrant and Refugee Rights Project, P.O. Box 654, Florence, Arizona 85232. የዚህ ጽሑፍ ወይም ማንኛውም ክፍል መሸጥ፡ የደራሲው መብት መጣስ ነው።

ይህ አጭር ጽሑፍ በኤሊዛበት ዳላም፡ የፍሎረንስ ፕሮጀክት የበፊት ዲረክተር፤ እንደገና ታድሶ የታተመ ሲሆን፡ የተስተካከለው በልይን ማርከስ፡ በአሪዞና ዩኒቨርሲቲ፡ የሕግ አስተማሪ ነው። በፍሮድ ፋውንደሽን የገንዘብ ጉዶማ ተደረበት።የመጀመርያው አጭር ጽሑፍ የተጻፈው በወይዘሮ/ሪት ማርከስ በ1991 ዓ.ም፡ ከማርሻል አሪዞና የገንዘብ እርዳታ ነበር።

ረጂና ጀርመይን፡ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮምሽን ጠበቃ የሆኑ፡ ይህን ጽሑፍ በማዘጋጀት እና ማስተካከል ላይ ስለተባበሩን ምስጋናችን ይድረስዎት። እነዚህ የብሄራዊ ማሳሰብያ ቦርድ አባሎች፡ እነዚህ ጽሑፎችን በማዘጋጀት የረዱን፡ ልናመሰግናቸው እንወዳለን፥ ጂኒ ባተርፊልድ፡ ከአሜሪካ የስደተኞች የጠበቃ ማህበር፣ ዳን ከሰልብረነር ከብሄራዊ የስደተኞች ፕሮጀክት፡ እና የብሄራዊ የጠበቃዎች ጊልድ፤ ሊንተን ጆአኪን ከብሀራዊ የስደተኞች ማእከል፤ ጁዲ ራቢኖቪዝ ከአሜሪካ የሲቪል ነጻነት ማህበር እና የስደተኞች መብት ፕሮጀክት፤ ማርክ ሲልቨርማን ከስደተኞች ሕጋዊ ጽሕፎች ማእከል፡ ካሮል ዎቾክ ከስደተኞች ሕግ እና ወኪል፡ እንዲሁም የአሜሪካ ባር ማህበር። ማንኛውም ስህተት የጸሐፊው ሀላፊነት ነው።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ሀሳቦች ከWinning Asylum Cases፡ በስደተኞች ሕጋዊ ጽሑፎች ማእከል እ.ኤ.አ በ1991 ዓ.ም የታተመ መጽሐፍ የተወሰዱ ናቸው።